

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና መመስረቻ ስምምነት

Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና መመስረቻ ስምምነት

Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area

First printing: March 2020

ማውጫ Contents

ምስጋና v
የዋና የንግድ ተደራዳሪው መልዕክት vi
የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መልዕክት x
Message from the Executive Secretary of the UNECA xii
በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ፀሀፊ መልእክት xiv
PREAMBLE 1
መግቢያ 2
Part 1 DEFINITIONS 5
ክፍል I ትርጓሜዎች 6
PART II ESTABLISHMENT, OBJECTIVES, PRINCIPLES AND SCOPE 9
ክፍል II ስለመመስረት፤ አላማዎች፤መርሆዎችና ወሰን 10
PART III ADMINISTRATION AND ORGANISATION 15
ክፍል III አስተዳደርና አደረጃጀት 16
PART IV TRANSPARENCY 25
ክፍል IV ስለ ግልፅነት 26
PART V CONTINENTAL PREFERENCES 27
ክፍል V አህጉራዊ ልዩ ጥቅሞች 28
PART VI DISPUTE SETTLEMENT 29
ክፍል VI ስለአለመግባባቶች አፈታት 30
PART VII FINAL PROVISIONS 29
ክፍል VII የመጨረሻ ድንጋጌዎች 30

PROTOCOL ON TRADE IN GOODS PREAMBLE 39
የዕቃዎች ንግድ ፕሮቶኮል
መግቢያ 40
PART I DEFINITIONS, OBJECTIVES AND SCOPE 41
ክፍል I ትርጓሜዎች፣ ዓላማዎች እና ወሰን 42
PART II NON-DISCRIMINATION 45
ክፍል II አለማዳላት 46
PART III LIBERALISATION OF TRADE 47
ክፍል III ንግድን ነጻ ስለማድረግ 48

PART IV CUSTOMS COOPERATION, TRADE FACILITATION AND TRANSIT 53
ክፍል IV የጉምሩክ ትብብር፣የንግድ ማሳለጥ እና ማስተላለፍ 54
PART V TRADE REMEDIES 55
ክፍል V የንግድ መፍትሄዎች 56
PART VI PRODUCT STANDARDS AND REGULATIONS 57
ክፍል VI ስለምርቶች ደረጃዎችና ቴክኒካዊ ደንቦች 58
PART VII COMPLEMENTARY POLICIES 57
ክፍል VII ስለደጋፊ ፖሊሲዎች 58
PART VIII EXCEPTIONS 61
ክፍል VIII ልዩ ሁኔታዎች 62
PART IX TECHNICAL ASSISTANCE, CAPACITY BUILDING AND COOPERATION 65
ክፍል IX የቴክኒክ ድጋፍ ፣ አቅም ግንባታ እና ትብብር 66
PART X INSTITUTIONAL PROVISIONS 65
ክፍል X ተቋማዊ ድንጋጌዎች 66

PROTOCOL ON TRADE IN SERVICES PREAMBLE 71
የአገልግሎት ንግድ ፕሮቶኮል
መግቢያ 72
PART I DEFINITIONS 73
ክፍል I ትርጉም 74
PART II SCOPE OF APPLICATION 79
ክፍል II የተፈጻሚነት ወሰን 80
PART III OBJECTIVES 81
ክፍል III ዓላማዎች 82
PART IV GENERAL OBLIGATIONS AND DISCIPLINES 83
ክፍል IV አጠቃላይ ግዴታዎች እና ሥርዓቶች 84
PART V PROGRESSIVE LIBERALISATION 103
ክፍል V ደረጃ በደረጃ ነጻ ማድረግ 104
PART VI INSTITUTIONAL PROVISIONS 113
ክፍል VI ተቋማዊ ድንጋጌዎች 114

PROTOCOL ON RULES AND PROCEDURES ON THE SETTLEMENT OF DISPUTES 121
የአለመግባባቶች መፍቻ ህጎችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮል 122

ምስጋና

ይህ የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና መመስረቻ ስምምነት ወደ አማርኛ እንዲተረጎምና እንዲታተም የፋይናንስ ድጋፍ ላደረገው ለተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ላቅ ያለ ምስጋና ለማቅረብ እንወዳለን፡፡ አስቸጋሪውን የትርጉም ስራ በብቃት፣በጥራትና በሀላፊነት ስሜት ለተወጡት ለዶ/ር ፍቅረማርቆስ መርሶ እንዲሁም የስራውን አስፈላጊነት ከመወጠን አንስቶ ሙሉ ሀላፊነቱን በመውሰድ ወደተግባር እንዲለወጥ ከማድረግ ባሻገር ዝርዝር አስተያየቶችንና እርማቶችን በመስጠት ለስኬታማነቱ ጉልህ አስተዋጽኦ ላበረከቱት አቶ ልሳነወርቅ ጎርፉ እና ዶ/ር ጥላሁን እስማኤል ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን፡፡ በተጨማሪም የትርጉም ስራው የመጨረሻ ረቂቅን በመመልከት ገንቢ አስተያየት ለሰጡትና ስራው ለህትመት እንዲበቃ ያለሳለሰ ድጋፍ ያደረጉልንን ዶ/ር መላኩ ገቦዬ ደስታን ከልብ እናመሰግናለን፡፡ በመጨረሻም ጠቃሚ አስተያየቶችን ለሰጡን እና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በስራው ሂደት ለተሳተፉ በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋና ለማቅረብ እንወዳለን ::

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

የዋና የንግድ ተደራዳሪው መልዕክት

የአፍሪካ አህጉራዊ ውህደት ራዕይ እ.ኤ.አ ከሜይ 1963 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም ጀምሮ የነበረ ሲሆን ምንም እንኳን ውጤታቸው አመርቂ ባይሆንም ይህንን ራዕይ እውን ለማድረግም የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። ከዚህም ባሻገር እ.ኤ.አ. በጁን 1991 ዓ.ም. በተፈረመው የአቡጃ ስምምነት ላይ የአካባቢያዊ ውህደት ለአፍሪካ ልማት ግቦች ቁልፍ እንደሆነ ጎልቶ ቢቀመጥም በተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የተነሳ ግቦቹን ለማሳካት የተደረጉ ጥረቶች ፍሬ ሳያፈሩ ቆይተዋል። የአፍሪካ ሀገራት ይህን ያደረ ዓላማ ለማሳካት በብርቱ በመሰራታቸው እ.ኤ.አ. በማርች 21/2018 ዓ.ም. የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት መሪዎች በሩዋንዳ በመገኘት የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና መመስረቻ ስምምነትን እንዲፈርሙ አስችሏል ።

ስምምነቱን በመፈረም የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት በአብዛኛው እቃዎች ላይ በሂደት ታሪፍን ለማስወገድ፣የአገልግሎት ንግድን በሂደት ክፍት ለማድረግ እና የንግድ መሰናክሎችን ለማስወገድ ተስማምተዋል። ስምምነቱ በውስጡ የማቋቋሚያ ማዕቀፍ፣ የእቃዎች ንግድ፣ የአገልግሎት ንግድና እና የግጭት መፍቻ ህጎችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮሎችን የያዘ ሲሆን እዚህ ደረጃ ላይ ሊደረስ የቻለው በ10 ዙር በተደረጉ ድርድሮች ነው። ስምምነቱ በአህጉራችን የግዙፍ አካባቢያዊ የንግድ ግንኙነቶች አዲስ ምዕራፍ ጅማሬ ማሳያና የአካባቢያዊ ውህደት ጥረት መጠናከር መገለጫ ነው።

የአፍሪካ የነጻ ንግድ ቀጣና መመስረቻ ስምምነት 55 የአፍሪካ ሀገሮችን በአንድ ላይ በማድረግ የነጻ ንግድ ስርአት የፈጠረ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነ ስምምነት ነው። የአፍሪካ መሪዎች እ.ኤ.አ በ2012 ዓ.ም በተካሄደ በ18ኛው መደበኛ ስብሰባቸው ቀጣናው እንዲመሰረት ሲስማሙ እ.ኤ.አ በ2015ም ድርድሩ በይፋ ተጀመረ። ስምምነቱ የመነጨው በአፍሪካ ሀገራት መካካል የሚካሄደው የእርስ በእርስ ንግድ በእጅጉ ዝቅተኛ በመሆኑና አካባቢያዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች የአካባቢያዊ ንግድን ለማጠናከር ቅድሚያ ትኩረት ባለመስጠታቸው ነው። ባለፉት ሀያ አመታት የአፍሪካ የእርስ በእርስ ንግድን ለማሻሻል ጥረቶች ቢደረጉም በአማካይ ከ15 በመቶ በላይ መሆን አልቻለም። አህጉሩ በዋነኛነት በጥሬ እቃዎች ላይ ጥገኛ መሆኑና የኢንዱስትሪው ዘርፍ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በአማካይ 26 በመቶ የአፍሪካ ሀገራት አንድ ወይም ሁለት ሸቀጦች 75 በመቶ የሚሆነውን የወጪ ምርታቸውን ይሸፍናል። 60 በመቶ የሚሆኑት የአፍሪካ ሀገራት ደግሞ በአምስት ሸቀጦች ብቻ ላይ ጥገኛ ናቸው።

ጥልቀት ያለው የአካባቢያዊ ውህደት የንግድ መሰናክሎችን በመቀነስ ውድድርን በመጨመር እና በአህጉሩ ሰፊ ገበያን በመፍጠር አስፈላጊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጥቅሞችን ያመጣል። የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ሲደረግ ሊገኙ የሚችሉ እምቅ ጠቀሜታዎች የተቃለለ የንግድ ህጎችና የጉምሩክ ሂደቶች፣ የተሻሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ በአለም አቀፍ

የእሴት ሰንሰለት ቁርኝት መፈጠር እና የጋራ የደህንነት ደረጃዎች ፣ የሰሪት ሀገር ምንጭ ንግድ እና ታሪፍ ነክ ያልሆኑ መሰናክሎችን ይጨምራል፡፡ ምንም እንኳን ታሪፍን ማስወገድ ለአፍሪካ እርስ በእርስ ንግድ ዋነኛው ግብ ቢሆንም አንዳንዶቹ ጉልህ የወጪ ንግድ እድገትና የደህንነት ከፍተኛ ጠቀሜታዎች የሚመነጩት በንግድ ማሳለጥ እና ታሪፍ ነክ ያልሆኑ የንግድ መሰናክሎችን በማስወገድ ነው፡፡

በዚህ ስምምነት የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት በአብዛኛው እቃዎች ላይ በሂደት ታሪፍን ማስወገድ፣የአገልግሎት ንግድን በሂደት ክፍት ማድረግ እና የንግድ መሰናክሎችን ለማስወገድ ተስማምተዋል፡፡ የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና መፈጠር ዓላማዎቹ ከግምት ወስጥ ሲገባ ታሪካዊና የአፍሪካን ኢኮኖሚ ሂደት ቀያሪ እንደሆነ ይታመናል፡፡ አፍሪካ ከ1.27 ቢሊዮን በ2030 ዓ.ም. ወደ 1.7 ቢሊዮን እና በ2050 ዓ.ም. ወደ 2.5 ቢሊዮን የሚያድግ ህዝብ ይኖራታል፡፡

አፍሪካ ሁለተኛዋ ትልቅ አህጉርና በህዝብ ብዛትም ከአለም ሁለተኛ ነች፡፡ ይህም ትልቅ እምቅ በአህጉሪቱ እንዳለ ያሳያል፡፡ ስለሆነም ይህን ጠቀሜታ አብዛኛው ህዝብ ወጣት ከፍል ለሆነችው አፍሪካ እንዲሆን ማድረግ ያሻል፡፡ ይህ ደግሞ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት፣ስደትና የድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመከላከል ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ የተቀናጀ አህጉራዊ ገበያን ለመፍጠር እና ከሚጨምረው የእርስ በርስ ንግድና ኢንቨስትመንት ፍሬ ተጠቃሚ ለመሆን የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ቀጣይነት ያለው የፖለቲካ ፍላጎትና ቁርጠኝነት እንዲሁም ውጤታማ ትግበራ ወሳኝ ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ ውስብስብ አለምአቀፍ ስምምነት ከትግበራ ቁርጠኝነት ባሻገር የበርካታ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

ይህ የማዕቀፍ ስምምነት አስፈላጊው የፈራሚና አጽዳቂ አገሮች ቁጥር የተገኘና በስምምነቱ መሰረት እ.ኤ.አ ከሜይ 30 ቀን 2019 ዓ.ም. ጀምሮ ወደተግባር የገባና ሀገራችንም የዚሁ አካል ብትሆንም በእቃዎችና በአገልግሎት ዘርፍ ገበያን ለመክፈት እና በሁለተኛው ዙር የሚደረጉ በኢንቨስትመንት፣ በውድድርና በአእምሮአዊ ንብረት መብት ድርድሮችን ጨምሮ በርካታ ስራዎች ይቀራሉ፡፡

ወደ አገራችን ስንመለስ ኢትዮጵያ በፈጣን የኢኮኖሚና ፖለቲካ ለውጥ ላይ ትገኛለች፡፡ የሪፎርም ስራችን ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ለአካባቢያዊ እና አህጉራዊ የንግድ ግንኙነት ልዩ ትኩረት መስጠት ይጠበቅባታል፡፡ የአፍሪካ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት የተሳሰረ እና እርስ በእርስ የተቆራኘ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ውህደት መፍጠር ጉልህ ቦታ አለው።

ሀገራችን በአህጉራዊ የንግድ ትስስር ውስጥ የምታደርገው ተሳትፎ አስተማማኝና ከአድሎ ነፃ የሆነ የገበያ ዕድል ለመፍጠር፣ የንግድ ስርዓቶችን ለማቀላጠፍና የንግድ ስርዓት ላይ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በሃገራት መካከል ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸው ላይ ተፅእኖ በማይፈጥርና ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመፍታት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ሀገራችን ወደ ውጭ ከምትልካቸው ዕቃዎች በአማካይ ከ20 በመቶ የማያንሱት በአብዣኛው ግብርና የሆኑ ምርቶች መዳረሻቸው የአፍሪካ ሃገራት

ሲሆኑ በሌላ በኩል ከአፍሪካ ሃገራት የምታስገባው የውጭ ንግድ መጠን በአማካይ ከ 4 በመቶ ያልበለጠ ነው። ይህም የሚያሳየው ሀገራችን ልትጠቀምበት የምትችለው ሰፊ የገበያ እድል መኖሩን ነው። ስለዚህም ይህንን መልካም አጋጣሚ ከመጠቀምና በቀጣይ ቀሪ ስራዎችን በመስራት ሃገራችን የውጭ ንግዷን ልታሻሽልና አህጉራዊ ተወዳዳሪነት አቅሟን ልታሰፋ የምትችልባቸው ሰፊ እድሎች እንዳሉ ያሳያል።

በተለይም የሀገራችን ወጪ ንግድ እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ በደረሰበት ደረጃ ሰጥቶ በመቀበል መርህ የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጣና አካል መሆን ማለት ወደ መካከለኛ ገቢ በምንሸጋገርበት ወቅት ሊታጡ የሚችሉ የአንድ ወገን የገበያ እድሎች ስጋት ከመቀነስ አኳያ ምቹ እድልና ዘላቂነት ያለው የተረጋገጠ ገበያ ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል።

ከዚህ በተጨማሪም በአህጉራዊ የንግድ ቀጣናው አማካኝነት በሚፈጠረው ትልቅ ገበያ ለሃገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት ማደግ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። ይህም በዋነኛነት በማኑፋክቸሪንግና በወጪ ንግድ መር የተቃኘውን የውጭ ኢንቨስትመንት የመሳብ ስትራቴጂ ከማስፈጸም አንፃር በአካባቢያችን ያሉ የገበያ እድሎችን የማስፋትና የተቀላጠፈ የንግድ አሰራሮችን በመዘርጋት ሰፊ ገበያ የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች ለመካፈል የሚሹ ባለሃብቶችን ከሌሎች የአለማችን ክፍሎች በተሻለ ለመሳብ ያስችላል። ይህም የስራ ዕድሎችን በመፍጠር የስራ አጥነት ችግሮቻችንን ለመፍታት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይታመናል።

በሌላ በኩል በአህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና አባልነት ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ስጋቶች በመቀነስ ረገድ በሃገር ውስጥ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች እና አምራቾች ያልተገባ ጫና እና ጉዳት እንዳይደርሳባቸው በስምምነቱ የምንገባውን ግዴታ መጠን በመገደብ፣ረዘም ባለ የትግበራ ጊዜ በመተግበር፣አገራችን በምትፈልገው መንገድ እና ፍጥነት እንዲሆን እየተሰራ ይገኛል። በዚህም መሰረት ከነፃ የንግድ ቀጣናው የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታችንን እያሰፋን የፖሊሲ ነፃነታችንን በማስፋት በኢኮኖሚያችን ላይ የሚያስከትለውን ጫና መቋቋም የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል።

የአፍሪካ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ሁሉንም ህብረተሰብ ከፍሎችና አጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ ባለው ግንኙነት በእስካሁኑ ሂደት የተለያዩ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከፍሎችን የግንዛቤ ማስጨበጫዎች አቅም በፈቀደ መጠን ተካሂዷል። የግሉ ዘርፍም ለሂደቱ አስተዋጽኦ በማበርከት ፍላጎቱ እንዲካተት እና ተጠቃሚነቱ እንዲያድግ እንዲሁም ስጋቱ እንዲቀነስ የሚያደርጉ ሀሳቦችን ለማካተት ተሞክሯል። በተጨማሪም ስምምነቱ የሚመጣቸው እድሎችን በስፋት ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚያስችሉና ለተወዳዳሪነት ዝግጁ የሚያደርጉና ለቀጣይ ድርድሮች ግብአቶችና ፍላጎቶችን ለማካተት የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችና አሰራሮች ወደፊት በስፋት ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል።

በመጨረሻም በዚህ መልኩ ወደ አማርኛ በማስተርጎም ሲዘጋጅ በአይነቱ ለመጀመሪያ የሆነውን የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና የመመስረቻ ስምምነት ስናቀርብ ሁሉም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በስፋት እንዲጠቀሙበትና ወደፊት የሚወጡ ንግድ ነክ ህጎችም ከዚህ ስምምነት ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑና ከሚያስገኘው መጠነ ሰፊ ጠቀሜታ አንጻር መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ::



አቶ ማሞ አስመለዓለም ምህረቱ

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍተኛ የፖሊሲ ሪፎርም አማካሪ እና
የዓለም ንግድ ድርጅትና የአካባቢያዊ ውህደት ድርድሮች ዋና ተደራዳሪ

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መልዕክት

ንግድ በአስገራሚ ተለዋዋጭነት ሂደት ውስጥ ባለበት ሁኔታና የከልላዊ ውህደት ጠቀሜታ እጅግ አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ላይ ሆነን የአፍሪካ አህጉራዊ የነፃ ንግድ ቀጣና እ.ኤ.አ. በማርች 2018 ዓ.ም. መፈረም ለእኛ አፍሪካውያን አንጸባራቂ ድል ነው። ኢኮኖሚያዊ ውህደት ላይ በመንተራስ አንድ አህጉራዊ ገበያ፣ የሰዎች እና የኢንቨስትመንት ነፃ እንቅስቃሴ ለመፍጠር በማለም የተመሰረተው የአፍሪካ አህጉራዊ የነፃ ንግድ ቀጣና በአህጉሪቱ የትብብር ኃይል ለመፈጠሩ እና ለጋራ ራዕይ ምስክር ነው።

ስምምነቱ በአህጉሪቱ ዜጎች ህይወት ላይ ተጨባጭና ጉልህ ለውጥ የማምጣት አቅም ያለው ሲሆን የአፍሪካ የእርስ በርስ ንግድ እና ዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ የሥራ ፈጠራን የሚያነቃቃ እንዲሁም ጥቃቅን ፣ አነስተኛ እና መካከለኛ መጠን ያላቸው ኢንተርፕራይዞች በኩል የሥራ ዕድል በማመቻቸት አፍሪካን ከድህነት ለማላቀቅ እና የአፍሪካን የእድገት አቅጣጫ ለማሳልበት ይረዳል። እነዚህ ጉዳዮች በዕቃዎች እና በአገልግሎቶች ውስጥ ላይ ያሉ ታሪፎችን እና የታሪፍ ያልሆኑ እንቅፋቶችን ደረጃ በደረጃ በማስወገድ የሚሳኩ ናቸው።

የስምምነቱ ዋነኛ ተጠቃሚ የንግዱ ማህበረሰብ ሲሆን የግሉ ዘርፍ እምቅ ጠቀሜታዎችም እየጨመረ በሚሄድ ጥቅመ ግዝፈት፣ጥሬና በከፊል የተፈበረኩ ዕቃዎችን በርካሽ ማግኘት፣ የአካባቢያዊ የእሴት ሰንሰለት የተሻለ ሁኔታ መፈጠርና ከአለም አቀፉ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ መተሳሰር፣ የአፍሪካ ኢኮኖሚን በከፍተኛ ደረጃ ቴክኖሎጂ እና እውቀት እንዲጠቀም ወደሚያደርግ ሁኔታ መለወጥ፣ የአፍሪካን የእርስ በርስ እና የውጭ የካፒታል ፍሰት ማሳለጥ እና የስራ እድል መፍጠርን ይጨምራል። ስምምነቱ ከዚህም ባሻገር ተጠቃሚዎች መጠነ ሰፊ እቃዎችና አገልግሎቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ያስችላል።

በሀገራችን የግሉ ሴክተር ከአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ተጠቃሚ መሆን እንዲችል የተደረጉትና ወደፊት የሚደረጉትን ድርድሮች ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚያስችሉ ስራዎች በተከታታይነት የሚሰሩ ከመሆኑም ባሻገር መንግስት የንግድ ስምምነቶች በድርድር ላይ እያሉ እና ሲተገብሩ የግሉ ዘርፍ ድምፅ መሰማቱን ያረጋግጣል። ይህንን ለማሳካትም ችግሮቹን ፣ ሊገኙ ስለሚችሉ ጥቅሞች እንዲሁም ከሁሉም በላይ ሊጫወቱት የሚችሉትን ሚና የሚያሳውቁ እርምጃዎችን ይወስዳል።

በዚህ ላይ በመመርኮዝ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአፍሪካ የነጻ ንግድ ቀጣና የመመስረቻ ስምምነትን በአማርኛ ቋንቋ አስተርጉሞ ሲያቀርብ ለሌሎች ስራዎች እንደመንደርደሪያ እንደሚያገለግል በማመን ሲሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት በስራቸው ሂደት ጥቅም ላይ እንዲያውሉት በማስገንዘብ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱም በስምምነቱ የሀገራችንን ተጠቃሚነት ከፍ ለማድረግ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን የሚቀጥል መሆኑን ላረጋግጥ እወዳለሁ፡፡



አምባሳደር ምሰጋኑ አርጋ ሞአች
የንግድ ማስፋፊያ ዘርፍ ሚኒስትር ደኤታ እና
የዓለም ንግድ ድርጅትና የአካባቢያዊ ውህደት ድርድሮች ምክትል ዋና ተደራዳሪ

Message from the Executive Secretary of the UNECA

It gives me great pleasure to see that the original text of the Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area (AfCFTA) has been successfully translated into Amharic, the working language of the Federal Government of Ethiopia.

When Ethiopia signed the AfCFTA Agreement in Kigali on that historic day of 21 March 2018, we all applauded the decision of the Government to assume its rightful place among the leaders of the Continent in the economic field. Exactly a year to the day, on 21 March 2019, the Ethiopian Parliament – the House of People's Representatives (HPR) – ratified the AfCFTA Agreement, a significant landmark in the long history of Ethiopia.

The UNECA has always stood behind the Government of Ethiopia, providing technical support to help inform the Government's decision-making process in every way it can. Unlike a vast majority of African countries, Ethiopia is neither a member of the World Trade Organization (WTO), nor a full participant in the trade liberalization initiatives within the Continent through regional economic communities (RECs). In appreciation of this fact, we at the UNECA have been committed to ensure Ethiopia gets all the technical support it needs to succeed in this area.

That is why the UNECA has continued to engage with, and support, the Government in the post-ratification phase as well. In this context, I am pleased to see the Amharic version of this landmark Agreement published today. As I have been reiterating since the adoption of the AfCFTA Agreement in March 2018, while its universal ratification and entry into force represents a significant step forward on the Continent's

path towards the formation of the African single market, entry into force alone is not enough; the Agreement will deliver on its enormous promises only if it is implemented to its letter and spirit. By making the Agreement accessible to a broader public in Ethiopia, the Amharic translation of the Agreement and its publication in this form will no doubt contribute to the realisation of that goal.

Finally, let me also take this opportunity to thank the European Union whose generous financial support made it possible for us to assist the Government of Ethiopia in producing this publication. My appreciation also goes to colleagues at the Regional Integration and Trade Division of the ECA and the consultants who, I have been assured, have done an excellent job of producing this Amharic version of AfCFTA Agreement.



Dr Vera Songwe
Under-Secretary General of the United Nations
Executive Secretary of the Economic Commission for Africa
Addis Ababa, Ethiopia

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ፀሀፊ መልእክት

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣናን የሚመሰርተውን የስምምነት ዋና ሰነድ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የስራ ቋንቋ ወደሆነው የአማርኛ ቋንቋ በተሳካ ሁኔታ ተተርጉሞ በማየቴ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል።

በዚያች ታሪካዊ ቀን እ.ኤ.አ በማርች 21 ቀን 2018 ዓ.ም. ኢትዮጵያ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና ስምምነትን ኪጋሊ ላይ ስትፈርም በርግጥም ኢትዮጵያ በአህጉሪቱ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የሚገባትን የመሪነት ቦታ ለመቀበል በመወሰኗ ሁላችንም አድናቆታችንን ችረናል። ከዚህ ታሪካዊ እለት አንድ አመት በኋላ እ.ኤ.አ ማርች 21 ቀን 2019 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፓርላማ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና ስምምነትን በማፅደቅ በረዥሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ትልቅ አሻራ አኑሯል።

የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የመንግስት ዉሳኔ አሰጣጥ ስርአት በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን በሚችለው ሁሉ የቴክኒክ እገዛ በማድረግ ሁልጊዜ ከኢትዮጵያ መንግስት ጎንቆሞ ቆይቷል። ከአብዛኛው የአፍሪካ ሀገራት በተለየ መልኩ ኢትዮጵያ የአለም ንግድ ድርጅት አባል ካለመሆኗም በተጨማሪ በአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ማህረሰቦች በተወሰዱት ንግድን ነፃ የማድረግ እንቅስቃሴዎች ሙሉ ተሳታፊ ሳትሆን ቆይታለች። ይህንንም እውነታ በመገንዘብ የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ዉጤታማ እንድትሆን የሚያስችላትን አስፈላጊውን ቴክኒካዊ ድጋፍ እንድታገኝ ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።

ለዚህም ነው የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ከስምምነቱ መፅደቅ በኋላም ከመንግስት ጋር አብሮ መስራቱንና መደገፉን የቀጠለው። ከዚህም አንፃር የዚህን ታሪካዊ ስምምነት የአማርኛ ቅጅ በዛሬው እለት ታትሞ በማየቴ ደስተኛ ነኝ። ስምምነቱ ከተፈረመበት ያለፈው አመት ጀምሮ በተደጋጋሚ እንደገለፅኩት ስምምነቱ በሁሉም ሀገራት መፅደቅና ስራ ላይ መዋል አህጉሩ ወደ አንድ ዉህድ ገበያ ምስረታ ለሚያደርገው ጉዞ ትልቅ እርምጃ ቢሆንም ስምምነቱ ወደ ስራ መግባቱ ብቻውን በቂ አይደለም። ስምምነቱ የያዘዉን ትልቅ እድል ሊያሳካ የሚችለው የስምምነቱ ድንጋጌዎችና መንፈሱ በትክክል ሲተገበሩ ነው። ስምምነቱ ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ የስምምነቱ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ መታተም ለዚህ አላማ ተግባራዊነት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ጥርጥር የለውም።

በመጨረሻም ለዚህ ስራ የኢትዮጵያን መንግስት መርዳት እንችል ዘንድ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልንን የአውሮፓ ህብረትን ለማመስገን እወዳለሁ። በተጨማሪም በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የአካባቢያዊ ውህደትና ንግድ ክፍል ባልደረቦችና የስምምነቱን የአማርኛ ቅጅ በማዘጋጀት እጅግ በጣም ጥሩ ስራ እንደሰሩ ለተነገረኝ ኮንሰልታንቶች አድናቆቴን መግለፅ እወዳለሁ።

ቬራ ሶንግዌ (ዶ/ር)
የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ረዳት ፀሀፊ
በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ፀሀፊ
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area

---

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና መመስረቻ ስምምነት

PREAMBLE

We, Member States of the African Union,

DESIROUS to implement the Decision of the Assembly of Heads of State and Government during its Eighteenth Ordinary Session held in Addis Ababa, Ethiopia from 29th-30th January, 2012 (Assembly/AU/Dec. 394(XVIII) of the Framework, Road Map and Architecture for Fast Tracking the establishment of the African Continental Free Trade Area and the Action Plan for Boosting Intra-African Trade;

COGNISANT of the launch of negotiations for the establishment of the Continental Free Trade Area aimed at integrating Africa's markets in line with the objectives and principles enunciated in the *Abuja Treaty* during the Twenty-Fifth Ordinary Session of the Assembly of Heads of State and Government of the African Union held in Johannesburg, South Africa from 14- 15 June 2015 **(Assembly/AU/Dec. 569(XXV);**

DETERMINED to strengthen our economic relationship and build upon our respective rights and obligations under the *Constitutive Act of the African Union of 2000,* the *Abuja Treaty* and, where applicable, the *Marrakesh Agreement Establishing the World Trade Organization* of 1994;

HAVING REGARD to the aspirations of Agenda 2063 for a continental market with the free movement of persons, capital, goods and services, which are crucial for deepening economic integration, and promoting agricultural development, food security, industrialisation and structural economic transformation;

CONSCIOUS of the need to create an expanded and secure market for the goods and services of State Parties through adequate infrastructure and the reduction or progressive elimination of tariffs and elimination of non-tariff barriers to trade and investment;

ALSO CONSCIOUS of the need to establish clear, transparent, predictable and mutually-advantageous rules to govern Trade in Goods and Services, Competition Policy, Investment and Intellectual Property among State Parties, by resolving the challenges of multiple and overlapping trade regimes to achieve policy coherence, including relations with third parties;

RECOGNISING the importance of international security, democracy, human rights, gender equality and the rule of law, for the development of international trade and economic cooperation;

መግቢያ

እኛ የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት፣

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ምስረታን ለለማፋጠን የሚያስችል ማእቀፍ፤ ፍኖተ ካርታ ፤ ንድፍ እና የአፍሪካ የእርስ በርስ ንግድን ማሳደጊያ የድርጊት መርሀግብርን አስመልከቶ በአውሮፓዊያን አቆጣጠር ከጃንዋሪ 29 እስከ 30 2012 ዓ.ም.** በአዲስ አበባ-ኢትዮጵያ የተካሄደው የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት እና መንግስታት የመሪዎች አስራ ስምንተኛው መደበኛ ጉባኤ ዉሳኔን (Assembly/AU/Dec. 394(XVIII) ተግባራዊ ለማድረግ **በመፈለግ፤**

በአቡጃ ስምምነት ላይ የተቀመጡትን አላማዎች እና መርሆዎች መስመር በመከተል የአፍሪካ ገበያዎችን ማስተሳሰር የሚያስችለውን የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ማቋቋሚያ ስምምነት ድርድር መጀመርን አስመልከቶ ከጁን 14 እስከ 15 2015 ዓ.ም. በጆሃንስበርግ ደቡብ አፍሪካ የተካሄደው የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት እና መንግስታት የመሪዎች ሀያ አምስተኛ መደበኛ ጉባኤ ዉሳኔን **(Assembly/AU/Dec. 569(XXV) በመገንዘብ፤**

የ2000 ዓ.ም.ቱ የአፍሪካ ህብረት ማቋቋሚያ ሰነድ ፤ በአቡጃ ስምምነት እንዲሁም ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ የ1994 ዓ.ም. የአለም ንግድ ድርጅትን ባቋቋመው የማራካሽ ስምምነት ባሉን ሙብቶችና ግዴታዎቻችን ላይ ተንተርሰን የኢኮኖሚ ግንኙነታችንን ለማጠናከር **በመወሰን፤**

ኢኮኖሚያዊ ትስስር ስር እንዲሰድ ለማድረግ እንዲሁም የግብርና ልማትን፣ የምግብ ዋስትናን፣ የኢንዱስትሪ ልማትንና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ወሳኝ የሆነውንና የሰዎች፣ የካፒታል፣ የእቃዎችና አገልግሎቶች ነፃ እንቅስቃሴ የሰፈነበት አህጉራዊ ገበያ ለማምጣት ያለመውን የአጀንዳ 2063ን ከፍተኛ ተስፋዎች **ትኩረት በመስጠት፤**

በበቂ መሰረተ ልማት እንዲሁም ቀረጥን በመቀነስ ወይም ደረጃ በደረጃ በማስወገድ እና ለንግድና ኢንቨስትመንት ማነቆ የሆኑትን ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎችን በማስወገድ በስምምነቱ አባል ሀገራት ዋስትና ያለው የእቃዎችና አገልግሎቶች ገበያ የመፍጠርና ማስፋፋትን አስፈላጊነት **በመገንዘብ፤**

በርካታና ተደራራቢ የንግድ ስርአቶች አባልነት ተግዳሮቶችን በማስወገድ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ያሉትን ግንኙነቶች ጨምሮ የፖሊሲ መጣጣምን ለማምጣት የሚያስችል ግልፅ፣ ተገማችና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ የእቃዎችና የአገልግሎቶች ንግድ፣ የውድድር ፖሊሲ፣ ኢንቨስትመንት እና አዕምሮአዊ ንብረትን የሚገዙ ድንጋጌዎችን በስምምነቱ አባል ሀገራት መካከል መመስረት አስፈላጊነትን **በመገንዘብ፤**

አለም አቀፍ ፀጥታ ፣ ዲሞክራሲ፣ ሰብዓዊ መብቶች፤፣ ፆታዊ እኩልነት እና በህግ ተገዢነት ለአለም አቀፍ ንግድ እድገትና ለኢኮኖሚያዊ ትብብር ያላቸውን አስፈላጊነት **በመረዳት፤**

REAFFIRMING the right of State Parties to regulate within their territories and the State Parties' flexibility to achieve legitimate policy objectives in areas including public health, safety, environment, public morals and the promotion and protection of cultural diversity;

FURTHER REAFFIRMING our existing rights and obligations with respect to each other under other agreements to which we are parties; and

ACKNOWLEDGING the Regional Economic Communities (RECs) Free Trade Areas as building blocs towards the establishment of the African Continental Free Trade Area (AfCFTA),

HAVE AGREED AS FOLLOWS:

የስምምነቱ አባል ሀገራት በግዛቶቻቸው ውስጥ የማስተዳደር መብታቸውን እንዲሁም የህብረተሰብ ጤና፣ ደህንነት፣ አካባቢ ጥበቃ፣ የህዝብ ሞራልና የባህል ብዝሀነትን መጠበቅና ማስተዋወቅን በተመለከተ ተገቢ የፖሊሲ አላማዎችን ለማሳካት ያላቸውን ነጻነት በማረጋገጥ፤

አባል በሆንባቸው ሌሎች ስምምነቶች መሰረት እያንዳንዳችን ለሌሎቻችን ያሉብንን መብቶችና ግዴታዎች **በድጋሚ በማረጋገጥ**፤ እና

የአካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰቦች ነፃ የንግድ ቀጣናዎች ለአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ምስረታ ምሰሶዎች መሆናቸውን እውቅና በመስጠት፤

እንደሚከተለው ተስማምተናል፤

Part 1
DEFINITIONS

Article 1
DEFINITIONS

For the purpose of this Agreement,

(a) **"Abuja Treaty"** means the Treaty Establishing the African Economic Community of 1991;

(b) **"Agreement"** means this Agreement Establishing the African Continental Free Trade Area and its Protocols, Annexes and Appendices which shall form an integral part thereof;

(c) **"Annex"** means an instrument attached to a Protocol, which forms an integral part of this Agreement;

(d) **"Appendix"** means an instrument attached to an Annex which forms an integral part of this Agreement;

(e) **"Assembly"** means the Assembly of Heads of State and Government of the African Union;

(f) **"AU"** means the African Union;

(g) **"AfCFTA"** means the African Continental Free Trade Area;

(h) **"Commission"** means the African Union Commission;

(i) **"Constitutive Act"** means the Constitutive Act of the African Union of 2000;

(j) **"Continental Customs Union"** means the Customs Union at the continental level by means of adopting a common external tariff, as provided by the Treaty Establishing the African Economic Community of 1991;

(k) **"Council of Ministers"** means the Council of African Ministers of State Parties responsible for Trade;

(l) **"Dispute Settlement Body"** means the body established to administer the provisions of the Protocol on Rules and Procedures on the Settlement of Disputes except as otherwise provided in this Agreement;

(m) **"Executive Council"** means the Executive Council of Ministers of the Union;

ክፍል I
ትርጓሜዎች

አንቀፅ 1
ትርጓሜዎች

ለዚህ ስምምነት ሲባል፤

(ሀ) **"የአቡጃ ስምምነት"** ማለት የ 1991 ዓ.ም.ቱ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ማህበረሰብ ማቋቋሚያ ስምምነት ነው፤

(ለ) **"ስምምነት"** ማለት ይህ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና መመስረቻ ስምምነት እና የስምምነቱ አካል የሆኑት ፕሮቶኮሎች፤ አባሪዎችና ተቀጽላዎች ናቸው፤

(ሐ) **"አባሪ"** ማለት ከፕሮቶኮል ጋር የተያያዘና የዚህ ስምምነት አካል የሆነ ሰነድ ነው፤

(መ) **"ተቀጽላ"** ማለት ከአባሪ ጋር የተያያዘና የዚህ ስምምነት አካል የሆነ ሰነድ ነው፤

(ሠ) **"ጉባኤ"** ማለት የአፍሪካ ህብረት ሀገራትና መንግስታት መሪዎች ጉባኤ ነው፤

(ረ) **"አ.ህ."** ማለት የአፍሪካ ህብረት ነው፤

(ሰ) **"አፍ.አ.ነ.ን.ቀ."** ማለት የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ነው፤

(ሸ) **"ኮሚሽን"** ማለት የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ነው፤

(ቀ) **"ማቋቋሚያ ሰነድ"** ማለት የ 2000 ዓ.ም.ቱ የአፍሪካ ህብረት ማቋቋሚያ ሰነድ ነው፤

(በ) **"አህጉራዊ የጉምሩክ ህብረት"** ማለት በ1991 ዓ.ም በአፍሪካ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ማቋቋሚያ ስምምነት እንደተመለከተው አንድ ዓይነት የጋራ የገቢ ንግድ ቀረጥ ስምምነት በማጽደቅ የተፈጠረ አህጉራዊ የጉምሩክ ህብረት ነው፤

(ተ) **"የሚኒስትሮች ምክር ቤት"** ማለት በአባል ሀገራት ለንግድ ጉዳዮች ሀላፊነት የተሰጣቸው የአፍሪካ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፤

(ቸ) **"አለመግባባት መፍቻ አካል"** ማለት በዚህ ስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የአለመግባባቶች መፍቻ ደንቦችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮል ድንጋጌዎችን ለማስተዳደር የተቋቋመ አካል ነው፤

(ኀ) **"የስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት"** ማለት የህብረቱ የሚኒስትሮች የስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት ነው፤

(n) **"GATS"** means the WTO General Agreement on Trade in Services of 1994;

(o) **"GATT"** means the WTO General Agreement on Tariffs and Trade of 1994;

(p) **"Instrument"** unless otherwise specified in this Agreement refers to Protocol, Annex or Appendix;

(q) **"Member States"** means the Member States of the African Union;

(r) **"Non-Tariff Barriers"** means barriers that impede trade through mechanisms other than the imposition of tariffs;

(s) **"Protocol"** means an instrument attached to this Agreement, which forms an integral part of the Agreement;

(t) **"RECs"** means the Regional Economic Communities recognised by the African Union, namely, the Arab Maghreb Union (UMA); the Common Market for Eastern and Southern Africa (COMESA); the Community of Sahel-Saharan States (CEN-SAD); the East African Community (EAC); the Economic Community of Central African States (ECCAS); the Economic Community of West African States (ECOWAS); the Intergovernmental Authority on Development (IGAD) and the Southern African Development Community (SADC);

(u) **"Secretariat"** means the Secretariat established pursuant to Article 13 of this Agreement;

(v) **"State Party"** means a Member State that has ratified or acceded to this Agreement and for which the Agreement is in force;

(w) **"Third Party"** means a State(s) that is not a party to this Agreement except as otherwise defined in this Agreement; and

(x) **"WTO"** means the World Trade Organization, as established in terms of the Marrakesh Agreement Establishing the World Trade Organization of 1994.

(ነ) **"አ.ን.ጠ.ስ."** ማለት 1994 ዓ.ምቱ የአለም ንግድ ድርጅት የአገልግሎት ንግድ አጠቃላይ ስምምነት ነው፤

(ኘ) **"ቀ.ን.ጠ.ስ."** ማለት የ1994ቱ ዓ.ም የአለም ንግድ ድርጅት የቀረጥና ንግድ ጠቅላላ ስምምነት ነው፤

(አ) **"የሀግ ሰነድ"** ማለት በዚህ ስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ፕሮቶኮል፤ አባሪ ወይም ተቀጽላ ነው፤

(ከ) **"አባል ሀገራት"** ማለት የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት ማለት ነው፤

(ኸ) **"ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎች"** ማለት ከቀረጥ ውጭ የሆኑ ንግድን የሚያግዱ መሰናክሎች ናቸው፤

(ወ) **"ፕሮቶኮል"** ማለት ከዚህ ስምምነት ጋር የተያያዘና የዚህ ስምምነት አካል የሆነ ሰነድ ነው፤

(ዐ) **"አ.አ.ማ."** ማለት በአፍሪካ ህብረት እውቅና ያገኙ አካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰቦች ማለትም የአረብ ማግረብ ህብረት ፤ የምስራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ፤ የሳህል ሰሀራ ሀገራት ማህበረሰብ ፤ የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ ፤የማእከላዊ አፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ፤የምእራብ አፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ፤ የበይነ መንግስታት የልማት ባለስልጣን ፤ እና የደቡባዊ አፍሪካ የልማት ማህበረሰብ ናቸው፤

(ዘ) **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በዚህ ስምምነት አንቀፅ 13 መሰረት የተቋቋመው ጽህፈት ቤት ነው፤

(ዠ) **"የስምምነቱ አባል ሀገር"** ማለት ይህንን ስምምነት ያጸደቀ ወይም የተቀበለና ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆንበት አባል ሀገር ነው፤

(የ) **"ሶስተኛ ወገን"** ማለት በዚህ ስምምንት በሌላ ሁኔታ ካልተተረጎመ በስተቀር የስምምነቱ አባል ያልሆነ ሀገር ነው፤ እና

(ደ) **"አ.ን.ድ."** ማለት የ1994 ዓ.ም.ቱ የአለም ንግድ ድርጅትን ባቋቋመው የማራካሽ ስምምነት መሰረት የተቋቋመው የአለም ንግድ ድርጅት ነው።

PART II
ESTABLISHMENT, OBJECTIVES, PRINCIPLES AND SCOPE

Article 2
Establishment of the African Continental Free Trade Area

The African Continental Free Trade Area (hereinafter referred to as "the AfCFTA") is hereby established.

Article 3
General Objectives

The general objectives of the AfCFTA are to:

(a) create a single market for goods, services, facilitated by movement of persons in order to deepen the economic integration of the African continent and in accordance with the Pan African Vision of "An integrated, prosperous and peaceful Africa" enshrined in Agenda 2063;

(b) create a liberalised market for goods and services through successive rounds of negotiations;

(c) contribute to the movement of capital and natural persons and facilitate investments building on the initiatives and developments in the State Parties and RECs;

(d) lay the foundation for the establishment of a Continental Customs Union at a later stage;

(e) promote and attain sustainable and inclusive socio-economic development, gender equality and structural transformation of the State Parties;

(f) enhance the competitiveness of the economies of State Parties within the continent and the global market;

(g) promote industrial development through diversification and regional value chain development, agricultural development and food security; and

(h) resolve the challenges of multiple and overlapping memberships and expedite the regional and continental integration processes.

ክፍል II
ስለመመስረት፤ አላማዎች፤መርሆዎችና ወሰን

አንቀፅ 2
የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ስለመመስረት

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና (ከዚህ በኋላ “የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ስምምነት ተመስርቷል።

አንቀፅ 3
አጠቃላይ ዓላማዎች

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና አጠቃላይ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

(ሀ) በአጀንዳ 2063 ላይ ልዩ ቦታ ተሰጥቶት በተገለፀው “የተሳሰረች፣የበለፀገችና ሰላማዊ አፍሪካ”ን የመፍጠር የፓን አፍሪካ ራዕይ መሰረት የአፍሪካን አህጉር የኢኮኖሚያዊ ዉህደት የሚያስፋፉ በሰዎች ነፃ እንቅስቃሴ የሚታገዝ የእቃዎችና አገልግሎቶች አንድ ውህድ ገበያን መፍጠር፤

(ለ) በተከታታይ በሚደረጉ የድርድር ዙሮች መሰረት ለእቃዎችና አገልግሎቶች ነፃ ገበያን መፍጠር፤

(ሐ) በስምምነቱ አባል ሀገራትና የአፍሪካ ኢኮኖሚ ማህበረሰቦች የተጀመሩ ስራዎች ላይ በመመስረት ለካፒታል እና የተፈጥሮ ሰዎች ነፃ እንቅስቃሴ አስተዋፅኦ ማድረግና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ፤

(መ) ለወደፊቱ አህጉራዊ የጉምሩክ ህብረት ምስረታ መሰረት መጣል፤

(ሠ) የስምምነቱ አባል ሀገራት ቀጣይነት ያለው እና ሁሉን አቀፍ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ የፆታ እኩልነትና መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያገኙ ማስቻል፣

(ረ) በአህጉራዊና አለም አቀፍ ገበያ የስምምነቱ አባል ሀገራት ኢኮኖሚ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ፤

(ሰ) የምርትን መሰረት በማስፋፋት ፣ የአካባቢያዊ የእሴት ሰንሰለት ግንባታን በማጠናከር፤ በግብርና ልማትና የምግብ ዋስትና ላይ ተመስርቶ የኢንዱስትሪ ልማትን ማስፋፋት፤ እና

(ሸ) የበርካታና ተደራራቢ የአካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ አባልነት ተግዳሮቶችን ማስወገድና አካባቢያዊና አህጉራዊ ትስስርን ማፋጠን።

Article 4
Specific Objectives

For purposes of fulfilling and realising the objectives set out in Article 3, State Parties shall:

(a) progressively eliminate tariffs and non-tariff barriers to trade in goods;
(b) progressively liberalise trade in services;
(c) cooperate on investment, intellectual property rights and competition policy;
(d) cooperate on all trade-related areas;
(e) cooperate on customs matters and the implementation of trade facilitation measures;
(f) establish a mechanism for the settlement of disputes concerning their rights and obligations; and
(g) establish and maintain an institutional framework for the implementation and administration of the AfCFTA.

Article 5
Principles

The AfCFTA shall be governed by the following principles:

(a) driven by Member States of the African Union;
(b) RECs' Free Trade Areas (FTAs) as building blocs for the AfCFTA;
(c) variable geometry;
(d) flexibility and special and differential treatment;
(e) transparency and disclosure of information;
(f) preservation of the acquis;
(g) Most-Favoured-Nation (MFN) Treatment;
(h) National Treatment;
(i) reciprocity;
(j) substantial liberalisation;
(k) consensus in decision-making; and
(l) best practices in the RECs, in the State Parties and International Conventions binding the African Union.

አንቀፅ 4
ዝርዝር ዓላማዎች

በአንቀፅ 3 የተዘረዘሩት ዓላማዎች እንዲሟሉና እንዲፈፀሙ ለማድረግ የስምምነቱ አባል ሀገራት የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፤

(ሀ) ቀረጦችንና ለእቃዎች ንግድ ማነቆ የሆኑትን ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎች ደረጃ በደረጃ ማስወገድ፤

(ለ) የአገልግሎቶችን ንግድ ደረጃ በደረጃ ነፃ ማድረግ፤

(ሐ) በኢንቨስትመንት፣ አእምሮአዊ ንብረት መብቶችና በውድድር ፖሊሲ ላይ መተባበር፤

(መ) በሁሉም ንግድ ነክ ጉዳዮች ላይ መተባበር፤

(ሠ) በጉምሩክ ጉዳዮችና በንግድ ማሳለጫ እርምጃዎች ላይ መተባበር፤

(ረ) መብቶቻቸውንና ግዴታዎቻቸውን በሚመለከት የአለመግባባቶችን መፍቻ መንገድ ማቋቋም፤ እና

(ሰ) የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣናን ተግባራዊ ለማድረግና ለማስፈፀም ተቋማዊ ማእቀፍ መመስረትና ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ።

አንቀፅ 5
መርሆዎች

የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፤

(ሀ) በአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት የሚመራ፤

(ለ) የአካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰቦች ነፃ የንግድ ቀጣናዎች ለአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ማቋቋሚያ መሰረቶች መሆናቸው፤

(ሐ) በተለያየ ፍጥነት መዋሀድ፤

(መ) ተለማጭነት እና በተለየ ሁኔታ ማስተናገድ፣

(ሠ) ግልፅነት እና መረጃን ይፋ ማድረግ፤

(ረ) ያለውን ሁኔታ መጠበቅ/ ወደኋላ ያለመመለስ፤

(ሰ) ሁሉንም አገራት ያለልዩነት ማስተናገድ፤

(ሸ) የሀገር ውስጥና ገቢ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ያለልዩነት ማስተናገድ፤

(ቀ) ሰጥቶ መቀበል፤

(በ) አብዛኛውን ንግድ ነጻ ማድረግ፤

(ተ) በሁሉም መስማማት ላይ የተመሰረተ ዉሳኔ አሰጣጥ፤ እና

(ቸ) የአካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰቦች፤ የስምምነቱ አባል ሀገራት እና የአፍሪካ ህብረትን የሚገዙ አለም አቀፍ ስምምነቶች ምርጥ ተሞክሮዎች::

Article 6
Scope

This Agreement shall cover trade in goods, trade in services, investment, intellectual property rights and competition policy.

Article 7
Phase II Negotiations

1. In pursuance of the objectives of this Agreement, Member States shall enter into Phase II negotiations in the following areas:
   (a) intellectual property rights;
   (b) investment; and
   (c) competition policy.
2. The negotiations referred to in paragraph 1 of this Article shall commence after the adoption of this Agreement by the Assembly and shall be undertaken in successive rounds.

Article 8
Status of the Protocols, Annexes and Appendices

1. The Protocols on Trade in Goods, Trade in Services, Investment, Intellectual Property Rights, Competition Policy, Rules and Procedures on the Settlement of Disputes and their associated Annexes and Appendices shall, upon adoption, form an integral part of this Agreement.
2. The Protocols on Trade in Goods, Trade in Services, Investment, Intellectual Property Rights, Competition Policy, Rules and Procedures on the Settlement of Disputes and their associated Annexes and Appendices shall form part of the single undertaking, subject to entry into force.
3. Any additional instruments, within the scope of this Agreement, deemed necessary, shall be concluded in furtherance of the objectives of the AfCFTA and shall, upon adoption, form an integral part of this Agreement.

አንቀፅ 6
የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ስምምነት የእቃዎችን ንግድ፣ የአገልግሎቶችን ንግድ፣ ኢንቨስትመንት፣ የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች እና የውድድር ፖሊሲን ያካትታል።

አንቀፅ 7
ደረጃ ሁለት ድርድሮች

1. በዚህ ስምምነት ዓላማዎች መሰረት አባል ሀገራት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የደረጃ ሁለት ድርድሮችን ማካሄድ አለባቸው፤

   (ሀ) የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች፤

   (ለ) ኢንቨስትመንት፤ እና

   (ሐ) የውድድር ፖሊሲ።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ነ ላይ የተመለከቱት ድርድሮች ይህ ስምምነት በጉባኤው ከፀደቀ በኋላ በመጀመር በተከታታይ ዙሮች መከናወን ይኖርበታል።

አንቀፅ 8
የፕሮቶኮሎች፣ አባሪዎችና ተቀጽላዎች ደረጃ

1. የእቃዎች ንግድ፣ የአገልግሎቶች ንግድ፣ ኢንቨስትመንት፣ የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች፣ የውድድር ፖሊሲ፣ የአለመግባባቶች መፍቻ ድንጋጌዎችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮሎች እና የእነዚሁ አባሪዎችና ተቀጽላዎች ከፀደቁ በኋላ የዚህ ስምምነት አካል ይሆናሉ።

2. የእቃዎች ንግድ፣ የአገልግሎቶች ንግድ፣ ኢንቨስትመንት፣ የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች፣ የውድድር ፖሊሲ፣ የአለመግባባቶች መፍቻ ድንጋጌዎችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮሎች እና አባሪዎቻቸውና ተቀጽላዎቻቸው ተግባራዊ ከሆኑ በኋላ ባልተነጣጠለ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

3. በዚህ ስምምነት ወሰን ውስጥ የሆነ ተጨማሪ የህግ ስነድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዚህን ስምምነት ዓላማዎች ለማራመድ ሲባል ስምምነት ይደረግበታል፤ ሲፀድቅም የዚህ ስምምነት አካል ይሆናል።

PART III
ADMINISTRATION AND ORGANISATION

Article 9
Institutional Framework for the Implementation of the AfCFTA

The institutional framework for the implementation, administration, facilitation, monitoring and evaluation of the AfCFTA shall consist of the following:

(a) the Assembly;
(b) the Council of Ministers;
(c) the Committee of Senior Trade Officials; and
(d) the Secretariat.

Article 10
The Assembly

1. The Assembly, as the highest decision-making organ of the AU, shall provide oversight and strategic guidance on the AfCFTA, including the Action Plan for Boosting Intra-African Trade (BIAT).
2. The Assembly shall have the exclusive authority to adopt interpretations of this Agreement on the recommendation of the Council of Ministers. The decision to adopt an interpretation shall be taken by consensus.

Article 11
The Composition and Functions of the Council of Ministers

1. The Council of Ministers is hereby established and shall consist of the Ministers responsible for Trade or such other ministers, authorities, or officials duly designated by the State Parties.
2. The Council of Ministers shall report to the Assembly through the Executive Council.
3. The Council of Ministers shall within its mandate:
    (a) take decisions in accordance with this Agreement;
    (b) ensure effective implementation and enforcement of the Agreement;

ክፍል III
አስተዳደርና አደረጃጀት

አንቀፅ 9
የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን ተግባራዊ ለማድረግ ስለሚኖር ተቋማዊ አደረጃጀት

የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን ስራ ላይ ለማዋል፣ለማስተዳደር፣ ለማሳለጥ፣ ለመተግበር፣ ለመከታተልና ለመገምገም የሚከተለው ተቋማዊ አደረጃጀት ይኖራል፤

1. ጉባኤ፤
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤
3. የከፍተኛ የንግድ ባለስልጣናት ኮሚቴ፤ እና
4. ጽህፈት ቤት።

አንቀፅ 10
ጉባኤ

1. ጉባኤው እንደ የአፍሪካ ህብረት ከፍተኛ ዉሳኔ ሰጭ አካል የአፍሪካን የእርስ በርስ ንግድን ማሳደጊያ የድርጊት መርሀ ግብርን ጨምሮ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን ይከታተላል፤ ስትራቴጅካዊ አቅጣጫ ይሰጣል።
2. ጉባኤው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያቀርበው የዉሳኔ ሀሳብ መሰረት የዚህን ስምምነት ትርጉሞች የማፅደቅ ብቸኛ ስልጣን አለው። ትርጉምን ማፅደቅ በሁሉም ስምምነት የሚወሰን ይሆናል።

አንቀፅ 11
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥንቅር እና ተግባራት

1. ንግድን እንዲመሩ ሀላፊነት የተሰጣቸው ሚኒስትሮችን ወይም በስምምነቱ አባል ሀገራት የሚሰየሙ ሌሎች ሚኒስትሮችን ወይም ባለስልጣናትን ወይም ሃላፊዎችን ያካተተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቋቁሟል።
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በስራ አስፈፃሚው ምክር ቤት በኩል ለጉባኤው ሪፖርት ያደርጋል።
3. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተሰጠው ስልጣን መሰረት፤

   (ሀ) በዚህ ስምምነት መሰረት ውሳኔዎችን ይሰጣል፤

   (ለ) ስምምነቱ በተገቢው ሁኔታ ስራ ላይ መዋልና መፈፀም ያረጋግጣል፤

(c) take measures necessary for the promotion of the objectives of this Agreement and other instruments relevant to the AfCFTA;

(d) work in collaboration with the relevant organs and institutions of the African Union;

(e) promote the harmonisation of appropriate policies, strategies and measures for the effective implementation of this Agreement;

(f) establish and delegate responsibilities to ad hoc or standing committees, working groups or expert groups;

(g) prepare its rules of procedure and those of its subsidiary bodies created for the implementation of the AfCFTA and submit them to the Executive Council for approval;

(h) supervise the work of all committees and working groups it may establish pursuant to this Agreement;

(i) consider reports and activities of the Secretariat and take appropriate actions;

(j) make regulations, issue directives and make recommendations in accordance with the provisions of this Agreement;

(k) consider and propose for adoption by the Assembly, the staff and financial regulations of the Secretariat;

(l) consider the organisational structure of the Secretariat and submit for adoption by the Assembly through the Executive Council;

(m) approve the work programs of the AfCFTA and its institutions;

(n) consider the budgets of the AfCFTA and its institutions and submit them to the Assembly through the Executive Council;

(o) make recommendations to the Assembly for the adoption of authoritative interpretation of this Agreement; and

(p) perform any other function consistent with this Agreement or as may be requested by the Assembly.

4. The Council of Ministers shall meet twice a year in ordinary session and may meet as and when necessary in extraordinary sessions.

5. Decisions taken by the Council of Ministers, while acting within its mandate, shall be binding on State Parties. Decisions that have legal, structural or financial implications shall be binding on State Parties upon their adoption by the Assembly.

(ሐ) የዚህ ስምምነትን እና ለአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ጠቃሚ የሆኑ ሌሎች የህግ ሰነዶችን ዓላማዎች ለማስተዋወቅ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

(መ) አግባብነት ካላቸው የአፍሪካ ህብረት አካላትና ተቋማት ጋር ተባብሮ ይሰራል፤

(ሠ) ለዚህ ስምምነት ዉጤታማ ትግበራ አግባብነት ያላቸው ፖሊሲዎች፤ ስትራቴጅዎችና እርምጃዎች እንዲጣጣሙ ያበረታታል፤

(ረ) ጊዚያዊ ወይም ቋሚ ኮሚቴዎችን፣ የስራ ቡድኖችን ወይም የኤክስፐርት ቡድኖችን ያቋቁማል፤ በውክልና ሀላፊነቶችን ይስጣል፤

(ሰ) የራሱን እና የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን ስራ ላይ ለማዋል የተቋቋሙ ሌሎች አካላትን የአሰራር ስነስርዓት በማዘጋጀት እንዲፀድቁ ለስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት ያቀርባል፤

(ቀ) በዚህ ስምምነት መሰረት ያቋቋማቸውን ሁሉንም ኮሚቴዎችና የስራ ቡድኖች ስራ ይቆጣጠራል፤

(በ) የጽህፈት ቤቱን ሪፖርቶችና ስራዎች በመገምገም አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

(ተ) በዚህ ስምምነት ድንጋጌዎች መሰረት ደንቦችን ያዘጋጃል፤ መመሪያዎችን ያወጣል እንዲሁም የውሳኔ ሀሳቦችን ያዘጋጃል፤

(ቸ) የጽህፈት ቤቱን የስራተኛና የፋይናንስ ደንብ በመመርመር በጉባኤው እንዲፀድቅ ሀሳብ ያቀርባል፤

(ኀ) የጽህፈት ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር በመመርመር በስራ አስፈፃሚ ምክር ቤቱ በኩል በጉባኤው እንዲፀድቅ ያቀርባል፤

(ነ) የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን እና በስሩ ያሉ ተቋማትን የስራ መርሀ ግብር ያፀድቃል፤

(ኘ) የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን እና በስሩ ያሉ ተቋማትን በጀት በመመርመር በስራ አስፈፃሚ ምክር ቤቱ በኩል በጉባኤው እንዲፀድቅ ያቀርባል፤

(አ) የዚህን ስምምነት ግቹ ትርጉም እንዲያፀድቅ ለጉባኤው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ እና

(ከ) ከዚህ ስምምነት ጋር የሚጣጣሙ ወይም በጉባኤው የተጠየቁ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

4. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመደበኛነት በአመት ሁለት ጊዜ እና እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል።

5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚሰጣቸው ዉሳኔዎች በዚህ ስምምነት አባል ሀገራት ላይ ተፈፃሚ ናቸው። የህግ፣ መዋቅራዊ ወይም የገንዘብ እንድምታዎች ያሏቸው ውሳኔዎች በአባል ሀገራት ላይ ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በጉባኤው ሲጸድቁ ነው።

6. The State Parties shall take such measures as are necessary to implement the decisions of the Council of Ministers.

Article 12
Committee of Senior Trade Officials

1. The Committee of Senior Trade Officials shall consist of Permanent or Principal Secretaries or other officials designated by each State Party.
2. The Committee of Senior Trade Officials shall:
   (a) implement the decisions of the Council of Ministers as may be directed;
   (b) be responsible for the development of programmes and action plans for the implementation of the Agreement;
   (c) monitor and keep under constant review and ensure proper functioning and development of the AfCFTA in accordance with the provisions of this Agreement;
   (d) establish committees or other working groups as may be required;
   (e) oversee the implementation of the provisions of this Agreement and for that purpose, may request a Technical Committee to investigate any particular matter;
   (f) direct the Secretariat to undertake specific assignments; and
   (g) perform any other function consistent with this Agreement or as may be requested by the Council of Ministers.
3. Subject to directions given by the Council of Ministers, the Committee of Senior Trade Officials shall meet at least twice a year and shall operate in accordance with the rules of procedures as adopted by the Council of Ministers.
4. The Committee shall submit its report, which may include recommendations, to the Council of Ministers following its meetings.
5. The RECs shall be represented in the Committee of Senior Trade Officials, in an advisory capacity.

6. የዚህ ስምምነት አባል ሀገራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔዎችን ስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መዉሰድ አለባቸው።

አንቀፅ 12
ከፍተኛ የንግድ ባለስልጣናት ኮሚቴ

1. ከፍተኛ የንግድ ባለስልጣናት ኮሚቴ ቋሚ ወይም ዋና ፀሀፊዎችን ወይም በእያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣናትን ያካትታል።

2. ከፍተኛ የንግድ ባለስልጣናት ኮሚቴ፤

   (ሀ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔዎችን በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ስራ ላይ ያውላል፤

   (ለ) ይህንን ስምምነት ስራ ላይ ለማዋል ፕሮግራሞችንና የድርጊት መርሐ ግብሮችን የማዘጋጀት ሃላፊነት ተጥሎበታል፤

   (ሐ) በዚህ ስምምነት ድንጋጌዎች መሰረት የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናን ይከታተላል፤ በቋሚነት ይገመግማል፤ በአግባቡ መስራቱንና መሻሻሉን ያረጋግጣል፤

   (መ) እንደ አስፈላጊነቱ ኮሚቴዎችን ወይም የስራ ቡድኖችን ያቋቁማል፤

   (ሠ) የዚህን ስምምነት ስራ ላይ መዋል ይቆጣጠራል፤ ከዚህ ጋር በተገናኘም አንድ የተለየ ጉዳይ በቴክኒክ ኮሚቴ እንዲመረመር ሊጠይቅ ይችላል፤

   (ረ) ጽህፈት ቤቱ የተለዩ ስራዎችን እንዲሰራ አቅጣጫ ይሰጣል፤ እና

   (ሰ) ከዚህ ስምምነት ጋር የሚጣጣሙ ወይም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጠየቁ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

3. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚሰጡት አቅጣጫዎች እንደተጠበቁ ሆነው የከፍተኛ ንግድ ባለስልጣናት ኮሚቴ ቢያንስ በአመት ሁለት ጊዜ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በፀደቀው የአሰራር ስነስርዓት መሰረትም ስራውን ማከናወን አለበት።

4. ኮሚቴዉ ከስብሰባው በኋላ የዉሳኔ ሀሳቦችን ሊጨምር የሚችል ሪፖርቱን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቅረብ ይኖርበታል።

5. አካባቢያዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች በአማካሪነት ደረጃ በከፍተኛ የንግድ ሃላፊዎች ኮሚቴ መወከል አለባቸው።

Article 13
The Secretariat

1. The Assembly shall establish the Secretariat, decide on its nature, location and approve its structure and budget.
2. The Commission shall be the interim Secretariat, until it is fully operational;
3. The Secretariat shall be a functionally autonomous institutional body within the African Union system with an independent legal personality;
4. The Secretariat shall be autonomous of the African Union Commission;
5. The Funds of the Secretariat shall come from the overall annual budgets of the African Union;
6. The roles and responsibilities of the Secretariat shall be determined by the Council of Ministers of Trade.

Article 14
Decision-Making

1. Decisions of the AfCFTA institutions[1] on substantive issues shall be taken by consensus.
2. Notwithstanding paragraph 1, the Committee of Senior Trade Officials shall refer, for consideration by the Council of Ministers, matters on which it has failed to reach consensus. The Council of Ministers shall refer the matters to the Assembly where consensus could not be reached.
3. Decisions on questions of procedure shall be taken by a simple majority of State Parties, eligible to vote.
4. Decisions on whether or not a question is one of procedure shall also be determined by a simple majority of State Parties, eligible to vote.
5. Abstention by a State Party eligible to vote shall not prevent the adoption of decisions.

አንቀፅ 13
ጽህፈት ቤት

1. ጉባኤው ጽህፈት ቤት ያቋቁማል፤ዓይነቱን እና መቀመጫውን ይወስናል እንዲሁም አወቃቀሩን እና በጀቱን ያፀድቃል።
2. ጽህፈት ቤቱ ሙሉ ለሙሉ ስራ እስኪጀምር ድረስ ኮሚሽኑ በጊዜያዊነት ፅህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል።
3. ጽህፈት ቤቱ በአፍሪካ ህብረት አደረጃጀት ውስጥ ሆኖ በአሰራሩ ነፃ የሆነና ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም መሆን አለበት።
4. ጽህፈት ቤቱ ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ውጭ ራሱን የቻለ መሆን አለበት።
5. የጽህፈት ቤቱ ገንዘብ ከአፍሪካ ህብረት ጠቅላላ አመታዊ በጀት የሚገኝ ይሆናል።
6. የጽህፈት ቤቱ ሚና እና ሃላፊነቶች በንግድ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወሰናል።

አንቀፅ 14
ዉሳኔ አሰጣጥ

1. የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ተቋማት[1] ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ዉሳኔዎች በሁሉም መስማማት ላይ መመስረት አለባቸው።
2. ንኡስ አንቀጽ ነ ቢኖርም የከፍተኛ ንግድ ሃላፊዎች ኮሚቴ መግባባት ላይ ሊደርስባቸው ያልቻላቸውን ጉዳዮች ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ማስተላለፍ አለበት። የሚኒስትሮች ምክር ቤት መግባባት ያልቻለባቸውን ጉዳዮች ለጉባኤው ማስተላለፍ አለበት።
3. የስነስርዓት ጥያቄዎች ድምፅ ለመስጠት በሚችሉ የስምምነቱ አባል ሀገራት በድምፅ ብልጫ የሚወሰኑ ይሆናል።
4. የቀረበው ጥያቄ የስነስርዓት መሆን ያለመሆኑ ድምፅ ለመስጠት በሚችሉ የስምምነቱ አባል ሀገራት በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ይሆናል።
5. ድምፅ ለመስጠት በሚችል የስምምነቱ አባል ሀገር የሚደረግ ድምፀ ተአቅቦ ውሳኔ ለመስጠት የሚከለክል አይሆንም።

Article 15
Waiver of Obligations

1. In exceptional circumstances, the Council of Ministers may waive an obligation imposed on a State Party to this Agreement, upon request by a State Party, provided that any such decision shall be taken by three fourths[2] of the States Parties, in the absence of consensus.
2. A request for a waiver from a State Party concerning this Agreement shall be submitted to the Council of Ministers for consideration pursuant to the practice of decision-making by consensus. The Council of Ministers shall establish a time period, which shall not exceed ninety (90) days, to consider the request. If consensus is not reached during the time period, any decision to grant a waiver shall be taken by three fourths of the State Parties.
3. A decision by the Council of Ministers granting a waiver shall state the exceptional circumstances justifying the decision, the terms and conditions governing the application of the waiver, and the date on which the waiver shall terminate. Any waiver granted for a period of more than one (1) year shall be reviewed by the Council of Ministers not later than one (1) year after it is granted, and thereafter annually until the waiver terminates. In each review, the Council of Ministers shall examine whether the exceptional circumstances justifying the waiver still exist and whether the terms and conditions attached to the waiver have been met. The Council of Ministers, on the basis of the annual review, may extend, modify or terminate the waiver.

አንቀፅ 15
ግዴታዎችን ስለማንሳት

1. የተለዩ ሁኔታዎች ያጋጠሙት የስምምነቱ አባል ሀገር ጥያቄ ሲያቀርብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ ወይም ይህ ካልተቻለ ሶስት አራተኛ ድምፅ[2] በስምምነቱ አባል ሀገር ላይ የተጣለን ግዴታን ሊያነሳ ይችላል፡፡

2. በአንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ይህን ስምምነት በተመለከተ የሚቀርብ የግዴታ ይነሳልኝ ጥያቄ በስምምነት ዉሳኔ አሰጣጥ ልማድ መሰረት እንዲታይ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት መቅረብ ይኖርበታል። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥያቄውን የሚያይበት ከ 90 ቀናት የማይበልጥ የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ አለበት። በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ስምምነት መድረስ ካልተቻለ ግዴታን የማንሳት ዉሳኔ በስምምነቱ አባል ሀገራት ሶስት አራተኛ ድምፅ መደገፍ አለበት።

3. ግዴታን ለማንሳት የሚደረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዉሳኔ፣ ለውሳኔው አሳማኝ የሆኑ የተለዩ ሁኔታዎችን፤ ግዴታ ማንሳቱ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች እና ግዴታ ማንሳቱ የሚያበቃበትን ቀን መግለፅ አለበት። ከአንድ አመት በላይ ለሆነ ጊዜ የተሰጠ የግዴታ ማንሳት፣ ዉሳኔው በተሰጠ በአንድ አመት ጊዜ ዉስጥና እስከሚያበቃ ድረስ በየአመቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መገምገም አለበት። በየእያንዳንዱ ግምገማ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔው አሳማኝ የሆኑ የተለዩ ሁኔታዎች አሁንም መኖራቸውንና ግዴታ ማንሳቱ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች መሟላታቸውን መመርመር አለበት። በአመታዊው ግምገማ መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የግዴታ ማንሳቱን ሊያራዝም፣ ሊያሻሽል ወይም ሊያቋርጥ ይችላል።

PART IV
TRANSPARENCY

Article 16
Publication

1. Each State Party shall promptly publish or make publicly available through accessible mediums[3] its laws, regulations, procedures and administrative rulings of general application as well as any other commitments under an international agreement relating to any trade matter covered by this Agreement.
2. The provisions of this Agreement shall not require any State Party to disclose confidential information which would impede law enforcement or otherwise be contrary to public interest or will prejudice the legitimate commercial interest of particular enterprises, public or private.

Article 17
Notification

1. Laws, regulations, procedures and administrative rulings of general application as well as any other commitments under an international agreement relating to any trade matter covered by this Agreement adopted after the entry into force of this Agreement shall be notified by State Parties in one (1) of the African Union working languages to other State Parties through the Secretariat.
2. Each State Party shall notify, through the Secretariat, in accordance with this Agreement, the other State Parties of any actual or proposed measure that the State Party considers might materially affect the operation of this Agreement or otherwise substantially affect the other State Party's interests under this Agreement.
3. At the request of another State Party, a State Party, through the Secretariat, shall promptly provide information and respond to questions pertaining to an actual or proposed measure, irrespective of whether or not the other State Party was previously notified of that measure.

ክፍል IV
ስለ ግልፅነት

አንቀፅ 16
ይፋ ስለማድረግ

1. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር ህጎቹን፣ ደንቦቹን፣ ጠቅላላ ተፈፃሚነት ያላቸውን ስነስርዐቶችና አስተዳደራዊ ዉሳኔዎች እንዲሁም በዚህ ስምምነት በተሸፈኑ የንግድ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ በሌሎች አለም አቀፍ ስምምነቶች የተገቡ ግዴታዎችን ይፋ ማድረግ/ማሳተም ወይም ህዝብ ሊያገኛቸው በሚችሉ ማሰራጫ መንገዶች[3] እንዲገኙ ማድረግ አለበት።

2. የዚህ ስምምነት ድንጋጌዎች ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር የህግ አፈፃፀምን የሚገድብ ወይም ለህዝብ ጥቅም ተፃራሪ የሆነን ወይም የህዝብም ይሁን የግል የንግድ ተቋምን ተገቢ የሆነ የንግድ ጥቅምን የሚፃረር ሚስጥራዊ መረጃን ይፋ እንዲያደርጉ አያስገድዱም።

አንቀፅ 17
ስለማሳወቅ

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት ይህ ስምምነት ስራ ላይ ከዋለ በኋላ የሚወጡ ህጎች፣ ደንቦች፣ ስነስርዐቶችና ጠቅላላ ተፈፃሚነት ያላቸው አስተዳደራዊ ዉሳኔዎች እንዲሁም በዚህ ስምምነት ከተሸፈኑ የንግድ ጉዳዮች ጋር የተገናኙ በሌሎች አለም አቀፍ ስምምነቶች የተገቡ ግዴታዎችን በአንዱ የአፍሪካ ህብረት የስራ ቋንቋ በጽህፈት ቤቱ በኩል ለሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት ማስታወቅ አለባቸው።

2. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር የወሰደውን ወይም ሊወስደው ያቀደውን እርምጃ በዚህ ስምምነት አተገባበር ላይ ትርጉም ያለው ተፅእኖ ይኖረዋል ብሎ ሲያስብ ወይም ሌሎች አባል ሀገራት በዚህ ስምምነት ባላቸው ጥቅሞች ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ይኖረዋል ብሎ ሲያስብ በዚህ ስምምነት መሰረት በጽህፈት ቤቱ በኩል ለሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት ማሳወቅ ይኖርበታል።

3. የስምምነቱ አባል ሀገር በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ሲጠየቅ የወሰደውን ወይም ሊወስደው ያቀደውን እርምጃ በተመለከተ ጠያቂው ቀደም ብሎ እንዲያውቀው የተደረገ ቢሆንም በጽህፈት ቤቱ በኩል ፈጣን መረጃ መስጠትና ለሚቀርብለት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።

4. Any notification or information provided pursuant to this Article is without prejudice to whether the measure is consistent with this Agreement.

PART V
CONTINENTAL PREFERENCES

Article 18
Continental Preferences

1. Following the entry into force of this Agreement, State Parties shall, when implementing this Agreement, accord each other, on a reciprocal basis, preferences that are no less favourable than those given to Third Parties.

2. A State Party shall afford opportunity to other State Parties to negotiate preferences granted to Third Parties prior to entry into force of this Agreement and such preferences shall be on a reciprocal basis. In the case where a State Party is interested in the preferences in this paragraph, the State Party shall afford opportunity to other State Parties to negotiate on a reciprocal basis, taking into account levels of development of State Parties.
3. This Agreement shall not nullify, modify or revoke rights and obligations under pre-existing trade agreements that State Parties have with Third Parties.

Article 19
Conflict and Inconsistency with Regional Agreements

1. In the event of any conflict and inconsistency between this Agreement and any regional agreement, this Agreement shall prevail to the extent of the specific inconsistency, except as otherwise provided in this Agreement.
2. Notwithstanding the provisions of Paragraph 1 of this Article, State Parties that are members of other regional economic communities, regional trading arrangements and custom unions, which have attained among themselves higher levels of regional integration than under this Agreement, shall maintain such higher levels among themselves.

4. ማንኛውም በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚሰጥ ማስታወቂያ ወይም መረጃ እርምጃው ከዚህ ስምምነት ጋር መጣጣሙ ወይም አለመጣጣሙን የሚወስን አይሆንም።

ክፍል V
አህጉራዊ ልዩ ጥቅሞች

አንቀፅ 18
አህጉራዊ ልዩ ጥቅሞች

1. ይህ ስምምነት በስራ ላይ ከዋለ በኋላ የስምምነቱ አባል ሀገራት ስምምነቱን ሲተገብሩ ለሶስተኛ ሀገራት ከሚሰጡት ያላነስ ልዩ ጥቅሞችን በሰጥቶ መቀበል መሰረት አርስ በአርሳቸው መሰጣጠት አለባቸው።

2. ስምምነቱ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለሶስተኛ ሀገር ልዩ ጥቅም የሰጠ የስምምነቱ አባል ሀገር ሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገሮች ልዩ ጥቅሙን ለማግኘት መደራደር እንዲችሉ እድል ይሰጣቸዋል፤ ልዩ ጥቅሙም በሰጥቶ መቀበል ላይ ይመሰረታል። አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር በዚህ ንኡስ አንቀጽ በተጠቀሱት ልዩ ጥቅሞች ላይ ፍላጎት ያላቸው ሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት የእድገት ደረጃቸውን ግምት ውስጥ በሚያስገባ መንገድ በሰጥቶ መቀበል መሰረት እንዲደራደሩ እድል ይሰጣል።

3. ይህ ስምምነት የስምምነቱ አባል ሀገራት ከሶስተኛ ሀገሮች ጋር ቀደም ብለው ባደረጓቸው ስምምነቶች ያላቸውን መብቶችና ግዴታዎች ዉጤት አልባ የሚያደርግ፤ የሚያሻሽል ወይም የሚሰርዝ አይሆንም።

አንቀፅ 19
ከአካባቢያዊ ስምምነቶች ጋር ስለመጋጨትና ስለአለመጣጣም

1. በዚህ ስምምነት እና በማንኛዉም አካባቢያዊ ስምምነት መካከል ግጭት ወይም አለመጣጣም ሲኖር በዚህ ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር ባለው አለመጣጣም ልክ ይህ ስምምነት የበላይነት ይኖረዋል።

2. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ፣ ቢኖርም የሌሎች አካባቢያዊ ኢኮኖሚ ማህበረሰቦች፤ አካባቢያዊ የንግድ አደረጃጀቶችና የጉምሩክ ዉህደቶች አባል የሆኑ እና በመካከላቸው ከዚህ ስምምነት በላይ የሆነ የአካባቢያው ዉህደት ላይ የደረሱ አባል ሀገራት ይህንኑ ከፍተኛ ዉህደት በመካከላቸው መቀጠል አለባቸው።

PART VI
DISPUTE SETTLEMENT

Article 20
Dispute Settlement

1. A Dispute Settlement Mechanism is hereby established and shall apply to the settlement of disputes arising between State Parties.
2. The Dispute Settlement Mechanism shall be administered in accordance with the Protocol on Rules and Procedures on the Settlement of Disputes.
3. The Protocol on Rules and Procedures on the Settlement of Disputes shall establish, inter alia, a Dispute Settlement Body.

PART VII
FINAL PROVISIONS

Article 21
Exceptions

No provision of this Agreement shall be interpreted as derogating from the principles and values contained in other relevant instruments for the establishment and sustainability of the AfCFTA, except as otherwise provided for in the Protocols to this Agreement.

Article 22
Adoption, Signature, Ratification and Accession

1. This Agreement shall be adopted by the Assembly.
2. This Agreement shall be open for signature and ratification or accession by the Member States, in accordance with their respective constitutional procedures.

ክፍል VI
ስለአለመግባባቶች አፈታት

አንቀፅ 20
አለመግባባቶችን ስለመፈታት

1. በዚህ ስምምነት አባል ሀገራት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያገለግል የአለመግባባት መፍቻ መንገድ ተቋቁሟል።
2. የአለመግባባት መፍቻ መንገዱ በአለመግባባቶች መፍቻ ደንቦችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮል መሰረት ይተዳደራል።
3. የአለመግባባቶች መፍቻ ደንቦችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮል ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ የአለመግባባቶች መፍቻ አካል ማቋቋም አለበት።

ክፍል VII
የመጨረሻ ድንጋጌዎች

አንቀፅ 21
ልዩ ሁኔታዎች

በዚህ ስምምነት ፕሮቶኮሎች ካልተገለፀ በስተቀር የዚህ ስምምነት ድንጋጌ በሌሎች የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ስምምነትን ለማቋቋም ወይም ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ከወጡ የህግ ሰነዶች መርሆችና እሴቶች ያፈነገጡ ተደርገው መተርጎም የለባቸውም።

አንቀፅ 22
ስለማፅደቅ፤ ስለመፈረም፤ ስለመቀበል እና ስለመቀላቀል

1. ይህ ስምምነት በጉባኤው መፅደቅ ይኖርበታል
2. ይህ ስምምነት ለአባል ሀገራት በህገመንግስታዊ ስርአታቸው መሰረት እንዲፈርሙና እንዲቀበሉ ወይም እንዲቀላቀሉ ክፍት መሆን አለበት።

Article 23
Entry into Force

1. This Agreement and the Protocols on Trade in Goods, Trade in Services, and Protocol on Rules and Procedures on the Settlement of Disputes shall enter into force thirty (30) days after the deposit of the twenty second (22nd) instrument of ratification.
2. The Protocols on Investment, Intellectual Property Rights, Competition Policy and any other Instrument within the scope of this Agreement deemed necessary, shall enter into force thirty (30) days after the deposit of the twenty second (22nd) instrument of ratification.
3. For any Member State acceding to this Agreement, the Protocols on Trade in Goods, Trade in Services, and the Protocol on Rules and Procedures on the Settlement of Disputes shall enter into force in respect of that State Party on the date of the deposit of its instrument of accession.
4. For Member States acceding to the Protocols on Investment, Intellectual Property Rights, Competition Policy, and any other Instrument within the scope of this Agreement deemed necessary, shall enter into force on the date of the deposit of its instrument of accession.
5. The Depositary shall inform all Member States of the entry into force of this Agreement and its Annexes.

Article 24
Depositary

1. The Depositary of this Agreement shall be the Chairperson of the Commission.
2. This Agreement shall be deposited with the Depositary, who shall transmit a certified true copy of the Agreement to each Member State.
3. A Member State shall deposit an instrument of ratification or accession with the Depositary.
4. The Depositary shall notify Member States of the deposit of the instrument of ratification or accession.

Article 25
Reservation

No reservations shall be made to this Agreement.

አንቀፅ 23
የሚፀናበት ጊዜ

1. ይህ ስምምነት እና የእቃዎች ንግድ ፕሮቶኮል፣ የአገልግሎቶች ንግድ ፕሮቶኮል እና የአለመግባባቶች መፍቻ ህጎችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮል ሀያ ሁለተኛው (22ኛው) የማፅደቂያ ሰነድ ገቢ በሆነ ከ 30 ቀናት በኋላ የፀና ይሆናል።

2. የኢቨስትመንት፣ የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች፣ የውድድር ፖሊሲ ፕሮቶኮሎች እና በዚህ ስምምነት ማእቀፍ ዉስጥ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ ማናቸውም ሌላ የህግ ሰነድ ሀያ ሁለተኛው (22ኛው) የማፅደቂያ ሰነድ ገቢ በሆነ ከ 30 ቀናት በኋላ የፀና ይሆናል።

3. ይህንን ስምምነት ለሚቀላቀል አባል ሀገር የእቃዎችና የአገልግሎቶች ንግድ ፕሮቶኮሎች እና የአለመግባባቶች መፍቻ ህጎችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮል የስምምነቱ አባል ሀገርን በተመለከተ የመቀላቀያ ማፅደቂያ ሰነዱ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

4. የኢንቨስትመንት፣ የአእምሮአዊ ንብረት መብቶች፣ የውድድር ፖሊሲ ፕሮቶኮሎች እና በዚህ ስምምነት ማእቀፍ ዉስጥ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ ማናቸውም ሌላ የህግ ሰነድ ለሚቀላቀል አባል ሀገር የማፅደቂያ ሰነዱ ገቢ ከሆነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

5. ባለአደራው ይህ ስምምነትና አባሪዎቹ የፀኑ መሆናቸውን ለአባል ሀገራት ማሳወቅ አለበት።

አንቀፅ 24
ባለአደራ

1. የኮሚሽኑ ሊቀመንበር የዚህ ስምምነት ሰነድ ባለአደራ ይሆናል።

2. ይህ ስምምነት ለባለአደራው ገቢ መደረግ የሚኖርበት ሲሆን ባለአደራውም የስምምነቱን የተረጋገጠና እውነተኛ ቅጅ ለእያንዳንዱ አባል ሀገር መላክ አለበት።

3. አባል ሀገራት የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለባለአደራው ገቢ ማድረግ አለባቸው።

4. ባለአደራው ገቢ የማፅደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ገቢ መደረጉን ለአባል ሀገራት ማሳወቅ ይኖርበታል።

አንቀፅ 25
የልዩነት ሀሳብ

በዚህ ስምምነት ላይ የልዩነት ሀሳብ ማቅረብ አይቻልም።

Article 26
Registration and Notification

1. The Depositary shall upon the entry into force of this Agreement, register it with the United Nations Secretary General in conformity with Article 102 of the Charter of the United Nations.
2. State Parties shall, where applicable notify this Agreement to the WTO individually or collectively.

Article 27
Withdrawal

1. After five (5) years from the date of entry into force in respect of a State Party, a State Party may withdraw from this Agreement by giving written notification to State Parties through the Depositary.
2. Withdrawal shall be effective two (2) years after receipt of notification by the Depositary, or on such later date as may be specified in the notification.
3. Withdrawal shall not affect any pending rights and obligations of the withdrawing State Party prior to the withdrawal.

Article 28
Review

1. This Agreement shall be subject to review every five (5) years after its entry into force, by State Parties, to ensure effectiveness, achieve deeper integration, and adapt to evolving regional and international developments.
2. Following the process of review, State Parties may make recommendations for amendments, in accordance with Article 29 taking into account experience acquired and progress achieved during the implementation of this Agreement.

Article 29
Amendments

1. Any State Party may submit proposal(s) for amendment to this Agreement to the Depositary.
2. The Depositary shall within thirty (30) days of receipt of the proposal, circulate the proposal to State Parties and the Secretariat.

አንቀፅ 26
ስለምዝገባና ማሳወቅ

1. ባለአደራው ይህ ስምምነት በሚፀናበት ጊዜ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀፅ 102 ድንጋጌ መሰረት በተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሀፊ ማስመዝገብ አለበት።
2. የዚህ ስምምነት አባል ሀገራት እንደአስፈላጊነቱ በተናጠል ወይም በጋራ ይህን ስምምነት ለዓለም ንግድ ድርጅት ማስታወቅ አለባቸው።

አንቀፅ 27
ስለ መውጣት

1. አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ስምምነቱ በእርሱ ላይ ከፀናበት ጊዜ አንስቶ ከአምስት አመት በኋላ በባለአደራው በኩል ለስምምነቱ አባል ሀገራት የፅሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ከዚህ ስምምነት ሊወጣ ይችላል።
2. ከስምምነት መውጣቱ የፀና የሚሆነው ማስታወቂያው ለባለአደራው ከደረሰ ከሁለት አመት በኋላ ወይም በማስታወቂያው ከተገለፀው ሌላ የኋላ ቀን ጀምሮ ነው።
3. የስምምነቱ አባል ሀገር ከስምምነት መዉጣት፣ ከመዉጣቱ በፊት በእንጥልጥል ላይ የነበሩ ሙብቶቹና ግዴታዎቹ ላይ የሚያመጣው ተፅእኖ አይኖርም።

አንቀፅ 28
ስለመከለስ

1. ይህ ስምምነት ከፀና በኋላ በየአምስት አመቱ ዉጤታማነቱን ለማረጋገጥ፤ጥልቀት ያለው ዉህደት ለማምጣት እና ከአካባቢያዊና አለምአቀፋዊ አዲስ ሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣም በስምምነቱ አባል ሀገራት ለመከለስ መታየት አለበት።
2. በሚደረገው የመከለስ ስርአት የስምምነቱ አባል ሀገራት ስምምነቱ በተተገበረበት ወቅት የተገኘውን ልምድና ዉጤት ግምት ዉስጥ በማስገባት በአንቀፅ 29 መሰረት የማሻሻያ ሀሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

አንቀፅ 29
ስለማሻሻል

1. ማንኛዉ የዚህ ስምምነት አባል ሀገር በባለአደራው በኩል ይህን ስምምነት ለማሻሻል ሀሳቦች ሊያቀርብ ይችላል።
2. ባለአደራው የማሻሻያ ሀሳቡን በተቀበል በ30 ቀናት ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ ለስምምነቱ አባል ሀገራት እና ለጽህፈት ቤቱ ማሰራጨት አለበት።

3. A State Party that wishes to comment on the proposal may do so within sixty (60) days from the date of circulation and submit the comments to the Depositary and the Secretariat.
4. The Secretariat shall circulate the proposal and comments received to members of the appropriate AfCFTA committees and sub-committees for consideration.
5. The relevant committees and sub-committees shall present, through the Secretariat, recommendations to the Council of Ministers, for consideration, following which a recommendation may be made to the Assembly through the Executive Council.
6. Amendments to the Agreement shall be adopted by the Assembly.
7. The amendments to this Agreement shall enter into force in accordance with Article 23 of this Agreement.

Article 30
Authentic Texts

This Agreement is drawn up in four (4) original texts in the Arabic, English, French and Portuguese languages, all of which are equally authentic.

3. በቀረበው ሀሳብ ላይ አስተያየት መስጠት የሚፈልግ የዚህ ስምምነት አባል ሀገር ሀሳቡ በተሰራጨ በስድሳ (60) ቀናት ዉስጥ አስተያየቱን ለባለአደራው እና ለጽህፈት ቤቱ ማቅረብ ይችላል።
4. ጽህፈት ቤቱ የቀረበውን ሀሳብና አስተያየት ለሚመለከታቸው የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ አባላት እንዲመረምሩት ማስተላለፍ አለበት።
5. የሚመለከታቸው ኮሚቴዎች እና ንዑስ ኮሚቴዎች የውሳኔ ሀሳባቸውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲመለከተው በጽህፈት ቤቱ በኩል ያቀርባሉ። የሚኒስትሮች ምክር ቤት የዉሳኔ ሀሳቦችም በስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት በኩል ለጉባኤው ሊቀርቡ ይችላሉ።
6. በዚህ ስምምነት ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች በጉባኤው መፅደቅ ይኖርባቸዋል።
7. በዚህ ስምምነት ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች በዚህ ስምምነት አንቀፅ 23 መሰረት የሚፀኑ ይሆናል።

አንቀፅ 30
ገዢ የስምምነቱ ሰነዶች

ይህ ስምምነት በአረብኛ፤ በእንግሊዝኛ፤በፈረንሳይኛ እና በፖርቱጋልኛ በአራት ዋና ሰነዶች የተዘጋጀ ሲሆን ሁሉም በእኩል ደረጃ ገዢነት አላቸው።

PROTOCOL ON TRADE IN GOODS

የዕቃዎች ንግድ ፕሮቶኮል

PROTOCOL ON TRADE IN GOODS

PREAMBLE

We, Member States of the African Union,

DESIROUS to implement the Decision of the Assembly of Heads of State and Government during its Eighteenth Ordinary Session held in Addis Ababa, Ethiopia from 29th-30th January, 2012 (Assembly/AU/Dec. 394(XVIII) of the Framework, Road Map and Architecture for Fast Tracking the establishment of the African Continental Free Trade Area and the Action Plan for Boosting Intra-African Trade;

COGNISANT of the launch of negotiations for the establishment of the Continental Free Trade Area aimed at integrating Africa's markets in line with the objectives and principles enunciated in the *Abuja Treaty* during the Twenty-Fifth Ordinary Session of the Assembly of Heads of State and Government of the African Union held in Johannesburg, South Africa from 14- 15 June 2015 **(Assembly/AU/Dec. 569(XXV);**

DETERMINED to take the necessary measures for reducing the cost of doing business and creating a conducive environment for private sector development and thereby boosting intra-African trade;

RESOLVED to enhance competitiveness at the industry and enterprise level through exploiting opportunities for economies of scale, continental market access and an efficient allocation of resources;

CONFIDENT that a comprehensive Protocol on Trade in Goods will deepen economic efficiency and linkages, improve social welfare, progressively eliminate trade barriers, increase trade and investment with greater opportunities for economies of scale for the businesses of State Parties;

COMMITTED to expanding intra-African trade through the harmonisation, coordination of trade liberalisation and implementation of trade facilitation instruments across Africa, and cooperation in the area of quality infrastructure, science and technology, the development and implementation of trade related measures; and

RECOGNISING the different levels of development among the State Parties and the need to provide flexibilities, special and differential treatment and technical assistance to State Parties with special needs,

HAVE AGREED AS FOLLOWS:

የዕቃዎች ንግድ ፕሮቶኮል

መግቢያ

እኛ የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት፣

የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ማቋቋምን ለማፋጠን እና አህጉራዊ ንግድን ለማሳደግ የሚያስችል ማእቀፍ፤ፍኖተ ካርታ እና ንድፍን እና አህጉራዊ ንግድን ማሳደጊያ የድርጊት መርሀግብር አስመልክቶ በአውሮፓዊያን አቆጣጠር ከጃንዋሪ 29 እስከ 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ የተካሄደው የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት እና መንግስታት የመሪዎች አስራ ስምንተኛው መደበኛ ጉባኤ ዉሳኔን (Assembly/AU/Dec. 394(XVIII) ተግባራዊ ለማድረግ **በመፈለግ፤**

በአቡጃ ስምምነት አላማዎች እና መርሆዎች በተገለጸው ላይ ተመስርቶ የአፍሪካ ገበያዎችን ማስተሳሰር የሚያስችለውን የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ማቋቋሚያ ስምምነት ድርድር መጀመርን አስመልክቶ ከጁን 14 እስከ 15/ 2015 ዓ.ም በጆሃንስበርግ ደቡብ አፍሪካ የተካሄደው የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት እና መንግስታት የመሪዎች ሀያ አምስተኛ መደበኛ ጉባኤ ዉሳኔን **(Assembly/AU/Dec. 569(XXV) በመረዳት፤**

የቢዝነስ ወጪዎችን ለመቀነስ የሚያስችሉ አስፈላጊ አርምጃዎችን በመውሰድ እና ለግሉ ዘርፍ እድገት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር አህጉራዊ የንግድ ትስስርን ለማሳደግ **በመወሰን፣**

በጥቅመ ግዝፈት ፣አህጉራዊ የገበያ እድል እና የኢኮኖሚ ግብአቶችን በአግባቡ መጠቀም የሚያስገኙትን ጥቅሞች በመጠቀም የአጠቃላይ በኢንዱስትሪና በኢንተርፕራይዝ ደረጃ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት **በመወሰን፣**

አጠቃላይ የዕቃዎች ንግድ ፕሮቶኮል ኢኮኖሚያዊ ቅልጥፍና እና ትስስሮች ስር እንዲሰዱ በማድረግ፣ ማህበራዊ ደህነትን በማሻሻል፣ ደረጃ በደረጃ የንግድ መሰናክሎችን በማስወገድ፣ ንግድና ኢንቨስትመንት በማሳደግ የስምምነቱ አባል ሀገራት ቢዝነሶች በጥቅመ ግዝፈት ለመስራት የሚችሉበትን የተሻለ እድል እንደሚፈጥር **በመተማመን፣**

በአህጉራዊ የነፃ ንግድ ማስፋፋፊያና ማሳለጫ ስርዓቶች ትግበራ መካከል መጣጣምና ቅንጅት በመፍጠር፣ በጥራት መሰረተ ልማት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ እና በሌሎች ንግድ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ፈጠራና/ልማትና ትግበራ ላይ በመስራት አህጉራዊ የንግድ ትስስርን ለማስፋፋት **በመወሰን፣** እና

በስምምነቱ አባል ሀገራት መካከል ያለውን የእድገት ደረጃ ልዩነት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸውን የስምምነቱ አባል ሀገራት የተለማጭነት፣በተለየ ሁኔታ ማስተናገድና የቴክኒክ ድጋፎች አስፈላጊነትን **አውቅና በመስጠት፣**

እንደሚከተለዉ ተስማምተናል፤

PART I
DEFINITIONS, OBJECTIVES AND SCOPE

Article 1
Definitions

For purposes of this Protocol, the following definitions shall apply:

(a) **"Anti-dumping Agreement"** means the WTO Agreement on the implementation of Article VI of the GATT 1994;

(b) **"Committee"** means the Committee for Trade in Goods established in Article 31 of this Protocol;

(c) **"Customs duty"** means a duty or charge of any kind imposed on or in connection with the importation or exportation of a good, including any form of surtax or surcharge imposed on or in connection with such importation or exportation;

(d) **"Harmonised System"** means the Harmonised Commodity Description and Coding System established by the International Convention on the Harmonised Commodity Description and Coding System;

(e) **"Non-Tariff Barriers"** means barriers that impede trade through mechanisms other than the imposition of tariffs;

(f) **"Originating products"** means goods that qualify as originating products under the rules of origin set out in Annex 2 on Rules of Origin;

(g) **"Preferential Trade Arrangements"** means any trade arrangement by which a State Party grants preferences to imports from another State Party or a Third Party and includes non- reciprocal preferential scheme granted by way of waiver;

(h) **"Safeguards Agreement"** means the WTO Agreement on Safeguards;

(i) **"Schedule of tariff concessions"** means a list of negotiated specific tariff concessions and commitments by each State Party. It sets out, transparently, the terms, conditions and qualifications under which goods may be imported under the AfCFTA;

ክፍል I
ትርጓሜዎች፣ ዓላማዎች እና ወሰን

አንቀጽ 1
ትርጓሜዎች

ለዚህ ፕሮቶኮል ዓላማ ሲባል የሚከተሉት ትርጓሜዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

(ሀ) **"አቃዎች በማራገፊያ ዋጋ ሲጣሉ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች የሚደነግግ ስምምነት"** ማለት የ1994 ዓ.ምቱ የዓለም የንግድ ድርጅት የቀረጥና እና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ VI ማስፈጸሚያ ስምምነት ነው፡፡

(ለ) **"ኮሚቴ"** ማለት በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 31 መሠረት የተቋቋመ የእቃዎች ንግድ ኮሚቴ ነው፡፡

(ሐ) **"የጉምሩክ ቀረጥ"** ማለት በማንኛውም ወደ ሀገር በሚገቡ ወይም በሚወጡ እቃዎች ላይ የሚጣል ቀረጥ ወይም ክፍያ ጨምሮ ሱር ታክስ ወይም ተጨማሪ ክፍያን ያጠቃልላል፡፡

(መ) **"የተቀናጀ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ"** ማለት በዓለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየም እና አመዳደብ ስምምነት መሠረት የተቀናጀ የሸቀጦች አመዳደብ ሥርዓት ነው፡፡

(ሠ) **"ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎች"** ማለት ከቀረጥ ውጭ የሆኑና ንግድን የሚያግዱ መሰናክሎች ናቸው፤

(ረ) **"ከስምምነቱ አባል ሀገራት የመነጩ እቃዎች"** ማለት በአባሪ 2 በተገለጸው የስሪት ሀገር ምንጭ ደንብ መሰረት ከስምምነቱ ከአባል ሀገራት የመነጩ ተብለው የሚወሰዱ እቃዎች ማለት ነው፤

(ሸ) **"የልዩ ጥቅም የንግድ አደረጃጀቶች"** ማለት አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ከሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ወይም ከሦስተኛ ሀገር ለሚገቡ እቃዎች ልዩ ጥቅም ለመስጠት የሚደረግ አደረጃጀት ሲሆን የሰጥቶ መቀበል መርህን መሠረት ያላደረጉ ግዴታን በማንሳት መልኩ ልዩ ጥቅም የመስጠት ዘዴዎችን ይጨምራል፤

(ቀ) **"የንግድ መከላከያ እርምጃዎች ስምምነት"** ማለት የዓለም ንግድ ድርጅት የንግድ መከላከያ እርምጃዎች ስምምነት ማለት ነው፤

(በ) **"ስምምነት የተደረሰበት የቀረጥ ሰንጠረዥ"** ማለት የእያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር በድርድር የተስማማውና ግዴታ የገባበት ዝርዝር የቀረጥ ሠንጠረዥ ነው፡፡ ሠንጠረዡም በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ውስጥ የሚገቡ እቃዎችን የመፈጸሚያ ጊዜ፣ ቅድመ ሁኔታና መመዘኛዎችን በግልፅ የያዘ ነው፡፡

(j) **"TBT"** means Technical Barriers to Trade; and

(k) **"TBT Agreement"** means the WTO Agreement on Technical Barriers to Trade.

Article 2
Objectives

1. The principal objective of this Protocol is to create a liberalised market for trade in goods in accordance with Article 3 of the Agreement.
2. The specific objective of this Protocol is to boost intra-African trade in goods through:
   (a) progressive elimination of tariffs;
   (b) progressive elimination of non-tariff barriers;
   (c) enhanced efficiency of customs procedures, trade facilitation and transit;
   (d) enhanced cooperation in the areas of technical barriers to trade and sanitary and phytosanitary measures;
   (e) development and promotion of regional and continental value chains; and
   (f) enhanced socio-economic development, diversification and industrialisation across Africa.

Article 3
Scope

1. The provisions of this Protocol shall apply to trade in goods between the State Parties.
2. Annex 1 on Schedules of Tariff Concessions, Annex 2 on Rules of Origin, Annex 3 on Customs Cooperation and Mutual Administrative Assistance, Annex 4 on Trade Facilitation, Annex 5 on Non-Tariff Barriers, Annex 6 on Technical Barriers to Trade, Annex 7 Sanitary and Phytosanitary Measures, Annex 8 on Transit and Annex 9 on Trade Remedies shall, upon adoption form an integral part of this Protocol.

(ተ) **"የንግድ ቴክኒካዊ እንቅፋቶች"** ማለት በንግድ ላይ የሚደረግ ቴክኒካዊ እንቅፋት ማለት ነው፡፡

(ቸ) **"ቴክኒካዊ የንግድ እንቅፋቶች ስምምነት"** ማለት የዓለም ንግድ ድርጅት ቴክኒካዊ የንግድ እንቅፋቶች ስምምነት ማለት ነው፡፡

አንቀጽ 2
አላማዎች

1. የዚህ ፕሮቶኮል ዋነኛ ዓላማ በዚህ ስምምነት አንቀጽ 3 መሠረት የእቃዎች ንግድ ነፃ ገበያ መፍጠር ነው፡፡

2. የዚህ ፕሮቶኮል ዝርዝር ዓላማ በአፍሪካ ውስጥ ፣

   (ሀ) ቀረጦችን ደረጃ በደረጃ በማስወገድ፣

   (ለ) ቀረጥ ያልሆኑ እንዳዎችን ደረጃ በደረጃ በማስወገድ፣

   (ሐ) የጉምሩክ ሥነሥርዐቶች ፣የንግድ ማሳለጥ እና የማስተላለፍ ብቃትን በማሳደግ ፣

   (መ) የሰው፣ የእንስሳትና እና የእፅዋት ንጽህናና ጤንነት እና የንግድ ቴክኒካዊ እንቅፋቶች ረገድ ትብብሮችን በማሳደግ፣

   (ሠ) አካባቢያዊ እና አህጉራዊ የእሴት ትስስሮችን ማሳደግ እና በማበረታታት፣ እና

   (ረ) በአፍሪካ የማህበራዊና ኢኮኖሚ እድገትን፣ ኢንዱስትሪ ልማትና ኢኮኖሚያዊ መዋቅርን በማስፋፋት፣

   የእቃዎች ንግድ ማሳደግ ነው፡፡

አንቀጽ 3
የተፈጻሚነት ወሰን

1. የዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎች በስምምነቱ አባል ሀገራት መካከል በሚደረጉ የእቃዎች ንግድ ላይ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

2. አባሪ 1 የቀረጥ ስምምነት ሠንጠረዥ ፣ አባሪ 2 የስሪት ሀገር ምንጭ ደንብ ፣ አባሪ 3 የጉምሩክ እና የጋራ አስተዳደር ትብብር ፣ አባሪ 4 የንግድ ማሳለጥ ፣ አባሪ 5 ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎች፣ አባሪ 6 የንግድ ቴክኒካዊ ገደቦች ፣ አባሪ 7 የሰው፣ የእንስሳትና የእፅዋት ንጽህናና ጤናን ለመጠበቅ የሚወሰዱ እርምጃዎች፣ አባሪ 8 ማስተላለፍ እና አባሪ 9 የንግድ መፍትሄዎች ከጸደቁ በኋላ የዚህ ፕሮቶኮል አካል ይሆናሉ፡፡

PART II
NON-DISCRIMINATION

Article 4
Most-Favoured-Nation Treatment

1. State Parties shall accord Most-Favoured-Nation Treatment to one another in accordance with Article 18 of the Agreement.
2. Nothing in this Protocol shall prevent a State Party from concluding or maintaining preferential trade arrangements with Third Parties, provided that such trade arrangements do not impede or frustrate the objectives of this Protocol, and that any advantage, concession or privilege granted to a Third Party under such arrangements is extended to other State Parties on a reciprocal basis.
3. Nothing in this Protocol shall prevent two or more State Parties from extending to one another preferences which aim at achieving the objectives of this Protocol among themselves, provided that such preferences are extended to the other State Parties on a reciprocal basis.
4. Notwithstanding the provisions of paragraphs 2 and 3 of this Article, a State Party shall not be obliged to extend to another State Party, trade preferences extended to other State Parties or Third Parties before the entry into force of the Agreement. A State Party shall afford opportunity to the other State Parties to negotiate the preferences granted therein on a reciprocal basis, taking into account levels of development of State Parties.

Article 5
National Treatment

A State Party shall accord to products imported from other State Parties treatment no less favourable than that accorded to like domestic products of national origin, after the imported products have been cleared by customs. This treatment covers all measures affecting the sale and conditions for sale of such products in accordance with Article III of GATT 1994.

ክፍል II
አለማዳላት

አንቀጽ 4
ለአንድ ሀገር የተሰጠን የተሻለ ጥቅም ለሁሉም ስለመስጠት

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት በዚህ ስምምነት አንቀጽ 18 በተደነገገው መሠረት ለአንድ ሀገር የተሠጠን የተሻለ ጥቅም ለሁሉም መስጠት አለባቸው፡፡

2. ይህ ፕሮቶኮል ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ከሦስተኛ ወገን ጋር የተለየ ጥቅም የሚያስጥ የንግድ ስምምነት ከመፈጸም ወይም ያለውን ከመቀጠል አይከለክልም ሆኖም በዚህ መልኩ የሚደረግ ማንኛውም የንግድ ስምምነት የዚህን ፕሮቶኮል ዓላማዎች የሚያደናቅፍ ወይም የሚያጨናግፍ መሆን የለበትም፡፡ በድርድር ለሦስተኛ ወገን የተሰጠ ማንኛውም ጥቅም፣ ፈቃድ ወይም ልዩ መብት በሰጥቶ መቀበል መርህ ለሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት መሰጠት ይኖርበታል፡፡

3. ይህ ፕሮቶኮል ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የስምምነቱ አባል ሀገራት የዚህን ፕሮቶኮል ዓላማዎች ለማሳካት ያለሙ ልዩ የንግድ ጥቅሞችን አንዱ ለሌላው እንዳይሰጥ አይከለክልም፡፡ ሆኖም እነዚህ ልዩ ጥቅሞች በሰጥቶ መቀበል መርህ ለሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት መሰጠት ይኖርባቸዋል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ቢኖርም አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ይህ ስምምነት ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ለሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ወይም ለሦስተኛ ወገን የሰጣቸውን ልዩ የንግድ ጥቅሞች ለሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት እንዲሰጥ አይገደድም፡፡ አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር የሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራትን የእድገት ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በእነዚህ ልዩ የንግድ ጥቅሞች ላይ በሰጥቶ መቀበል መርህ ድርድር ማድረግ እንዲችሉ እድሉን ክፍት ማድረግ አለበት፡፡

አንቀጽ 5
ገቢ እቃዎችን በሀገር ውስጥ ከተመረቱ ተመሳሳይ ምርቶች ባላነሰ ሁኔታ ማስተናገድ

አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ከሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች የጉምሩክ ሥነ ሥርዐት ከተፈፀመባቸው በኋላ በሀገር ውስጥ ከተመረቱ ተመሳሳይ ምርቶች ባላነሰ ሁኔታ ማስተናገድ አለበት፡፡ይህ መስተንግዶ በ1994ቱ የቀረጥና የንግድ ጠቅላላ ስምምነት አንቀጽ III መሠረት የእነዚህኑ ምርቶች ሽያጭ እና የሽያጭ ቅድመ ሁኔታዎች የሚመለከቱ ሁሉንም እርምጃዎች ያካትታል፡፡

Article 6
Special and Differential Treatment

In conformity with the objective of the AfCFTA in ensuring comprehensive and mutually beneficial trade in goods, State Parties shall, provide flexibilities to other State Parties at different levels of economic development or that have individual specificities as recognised by other State Parties. These flexibilities shall include, among others, special consideration and an additional transition period in the implementation of this Agreement, on a case by case basis.

PART III
LIBERALISATION OF TRADE

Article 7
Import Duties

1. State Parties shall progressively eliminate import duties or charges having equivalent effect on goods originating from the territory of any other State Party in accordance with their Schedules of Tariff Concessions contained in Annex 1 to this Protocol.
2. For products subject to liberalisation, State Parties shall not impose any new import duties or charges having equivalent effect on goods originating from the territory of any other State Party, except as provided for under this Protocol.
3. An import duty shall include any duty or charge of any kind imposed on or in connection with the importation of goods consigned from any State Party to a consignee in another State Party, including any form of surtax or surcharge, but shall not include any:
    (a) charges equivalent to internal taxes imposed consistently with Article III(2) of GATT 1994 and its interpretative notes in respect of like or directly competitive or substitutable goods of the State Party or in respect of goods from which imported goods have been manufactured or produced in whole or in part;

አንቀጽ 6
ልዩ መስተንግዶ

የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ሁሉን አቀፍና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ የእቃዎች ንግድ ስርአት የሚፈጥር ዓላማ ጋር በሚጣጣም መልኩ የስምምነቱ አባል ሀገራት በተለያየ የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት ወይንም በሌሎች አባል ሀገራት እውቅና የተሠጠው የተለየ ሁኔታን ምክንያት በማድረግ ልዩ መስተንግዶ ሊሰጡ ይችላሉ። እነዚህ ተለማጭነቶች ከሌሎች በተጨማሪ እንደየጉዳዩ ሁኔታ ልዩ እሳቢዎችን እና ይህንን ስምምነት ለማስፈፀም ተጨማሪ የመሸጋገሪያ ጊዜ ሊያካትት ይገባል።

ክፍል III
ንግድን ነጻ ስለማድረግ

አንቀጽ 7
የገቢ ቀረጥ

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት በዚህ ፕሮቶኮል አባሪ ነ በተመለከተው የየራሳቸው የቀረጥ ሠንጠረዥ መሠረት ከስምምነቱ አባል ሀገራት የሚመነጩ ዕቃዎች ላይ የሚጥሏቸውን ቀረጦችና ተመሳሳይ ውጤት የሚያስከትሉ ሌሎች ክፍያዎች ደረጃ በደረጃ ማስወገድ አለባቸው።

2. ነጻ ለማድረግ የተወሰኑ ምርቶችን በተመለከተ፣ በዚህ ፕሮቶኮል በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር፣የስምምነቱ አባል ሀገራት ከሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት የሚመነጩ ዕቃዎች ላይ ማንኛውንም አይነት አዲስ የገቢ ቀረጥ ወይም ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ሌሎች ክፍያዎችን መጣል አይችሉም።

3. የገቢ ቀረጥ ማለት ከማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ወደሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ወደሚገኝ ተቀባይ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ወይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚጣል ቀረጥና ተመሳሳይ ሌሎች ክፍያዎችና ማንኛውንም የሱር ታክስ ወይም ተጨማሪ ክፍያን የሚይዝ ሲሆን የሚከተሉትን አያካትትም፤

   (ሀ) በ1994ቱ የቀረጥና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ III (2) እና የትርጉም መግለጫዎች መሰረት ተመሳሳይ ወይም በቀጥታ ተወዳዳሪ ወይም የሚተካኩ ወይም ገቢ እቃዎች በሙሉ ወይም በከፊል የተፈበረኩበት ወይም የተመረቱበት የስምምነቱ አባል ሀገራት እቃዎችን በተመለከተ፣ ከሀገር ውስጥ ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ የሚፈጸም ከሆነ፣

(b) antidumping or countervailing duties imposed in accordance with Articles VI, and XVI of GATT 1994 and the WTO Agreement on Subsidies and Countervailing Measures and Article 17 of this Protocol;

(c) duties or levies imposed in relation to safeguards, in accordance with Articles XIX of GATT 1994, the WTO Agreement on Safeguards and Articles 18 and 19 of this Protocol; and

(d) other fees or charges imposed consistently with Article VIII of GATT 1994.

Article 8
Schedules of Tariff Concessions

1. Each State Party shall apply preferential tariffs to imports from other State Parties in accordance with its Schedule of Tariff Concessions contained in Annex 1 to this Protocol and in conformity with the adopted tariff modalities. The Schedules of Tariff Concessions, the adopted tariff modalities and outstanding work on tariff modalities to be negotiated and adopted, shall be an integral part of this Protocol.
2. Notwithstanding the provisions of this Protocol, State Parties that are members of other RECs, which have attained among themselves higher levels of elimination of customs duties and trade barriers than those provided for in this Protocol, shall maintain, and where possible improve upon, those higher levels of trade liberalisation among themselves.

Article 9
General Elimination of Quantitative Restrictions

The State Parties shall not impose quantitative restrictions on imports from or exports to other State Parties except as otherwise provided for in this Protocol, its Annexes and Article XI of GATT 1994 and other relevant WTO Agreements.

Article 10
Export Duties

1. State Parties may regulate export duties or charges having equivalent effect on goods originating from their territories.

(ለ) በ1994ቱ በዓለም ንግድ ድርጅት የቀረጥና ንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ VI እና አንቀጽ XVI እና የዓለም ንግድ ድርጅት የድጎማና አጸፋዊ እርምጃዎች ስምምነት መሰረት እና በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 17 መሠረት በማራገፊያ ዋጋ በገቢ እቃዎች ላይና ለአጸፋዊ እርምጃዎች የሚጣሉ ቀረጦች፣

(ሐ) በ1994ቱ የዓለም የንግድ ድርጅት የቀረጥና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ XIX፣ የንግድ መከላከያ እርምጃዎች ስምምነት እና በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 18 እና 19 መሠረት የሚጣሉ ቀረጦች ወይም ክፍያዎች፣

(መ) ከ1994ቱ የቀረጥና የንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ VIII ጋር በተጣጣመ መልኩ የሚጣሉ ሌሎች ክፍያዎች፣

አንቀጽ 8
ስምምነት የተደረገበት የቀረጥ ሠንጠረዥ

1. እያንዳንዱ የዚህ ስምምነት አባል ሀገር ከሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት በሚመነጩ ዕቃዎች ላይ በዚህ ፕሮቶኮል አባሪ 1. በተያያዘው ስምምነት የተደረገበት የቀረጥ ሠንጠረዥና ከፀደቀው የቀረጥ ሞዳሊቲ ጋር የሚጣጣም ልዩ ጥቅም የሚያስገኝ ቀረጥ ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡ ስምምነት የተደረገበት የቀረጥ ሠንጠረዦችና ፣ የቀረጥ ሞዳሊቲዎች እና ሌሎች በድርድርና ላይ ያሉና የሚጸድቁ ቀሪ የቀረጥ ሞዳሊቲዎች የዚህ ፕሮቶኮል አንድ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ።

2. የዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎች ቢኖሩም የሌላ አካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰቦች አባል የሆኑ የስምምነቱ አባል ሀገራት በዚህ ፕሮቶኮል ከተደነገገው በተሻለ ሁኔታ የጉምሩክ ቀረጥ እና የንግድ ክልከላዎችን ያስወገዱ እንደሆነ ይህንኑ ከፍ ያለ ነፃ የንግድ ስርዓት ማስቀጠልና ከተቻለም አጠናክረው መቀጠል ይችላሉ፡፡

አንቀጽ 9
አጠቃላይ የመጠን እገዳ ስለመከልከሉ

በዚህ ፕሮቶኮልና በአባሪዎቹ፣ በ1994ቱ የቀረጥና ንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ XI፣እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች የዓለም የንግድ ድርጅት ስምምነቶች በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የስምምነቱ አባል ሀገራት ከሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ወይም ወደ ሌላ የስምምነቱ አባል ሀገራት በሚላኩ ዕቃዎች ላይ የመጠን እገዳ ማድረግ የለባቸውም።

አንቀጽ 10
በወጪ ዕቃዎች ላይ ስለሚጣል ቀረጥ

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት ከራሳቸው ግዛት የሚመነጩ የወጪ እቃዎች ቀረጥ ወይም ተመጣጣኝ ውጤት ያላቸውን ክፍያዎች ሊወስኑ ይችላሉ።

2. Any export duties or taxes, imposed on or in connection with, the exportation of goods, applied pursuant to this Article shall be applied to goods exported to all destinations on a non-discriminatory basis.
3. A State Party that introduces export duties or taxes on, or in connection with, the exportation of goods in accordance with paragraph 2 of this Article, shall notify the Secretariat ninety (90) days from the introduction of the said export duties or taxes.

Article 11
Modification of Schedules of Tariff Concessions

1. In exceptional circumstances, a State Party may request for modification of its Schedules of Tariff Concessions.

2. In such exceptional circumstances, a State Party (hereinafter referred to as the "modifying State Party") shall submit to the Secretariat, a written request, together with evidence of the exceptional circumstances for such a request.
3. Upon receipt of the request, the Secretariat shall immediately circulate the request to all State Parties.
4. Where a State Party considers that it has a substantial interest (hereinafter referred to as the "State Party with substantial interest") in the tariff schedule of the modifying State Party, it should communicate in writing, with supporting evidence, to the modifying State Party through the Secretariat within thirty (30) days. The Secretariat shall immediately circulate all such requests to all State Parties.
5. The modifying State Party and any State Party with substantial interest, as determined under paragraph 3, shall enter into negotiations to be coordinated by the Secretariat with a view to reaching an agreement on any necessary compensatory adjustment. In such negotiations and agreement, the State Parties shall maintain a general level of commitments not less favourable than the initial commitments.
6. The outcome of the negotiations and the subsequent modification of the tariff schedule and any compensation thereof, shall only be effected upon approval by State Parties with substantial interest and notification to the Secretariat which shall transmit to other State Parties. The compensatory adjustments shall be made in accordance with Article 4 of this Protocol.

2. በዚህ አንቀጽ መሠረት በወጪ ዕቃዎች ላይ ወይም ከእቃዎች መውጣት ጋር በተገናኘ የሚጣል ቀረጥ ወይም ግብር አድልዎ በማያደርግ መልኩ ወደሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት በሚሄዱ እቃዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ መሆን አለበት።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በወጪ ዕቃዎች ላይ ወይም ከእቃዎቹ አወጣጥ ጋር በተገናኘ ቀረጥ ወይም ግብር የሚጥል የስምምነቱ አባል ሀገር ይኸው እርምጃ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በዘጠና ቀናት ውስጥ ለጽህፈት ቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

አንቀጽ 11
ስምምነት የተደረገበትን የቀረጥ ሠንጠረዥ ስለማሻሻል

1. ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የስምምነቱ አባል ሀገር የቀረጥ ስምምነት ሠንጠረዡን ለማሻሻል ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።

2. እነዚሁ ልዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የስምምነቱ አባል ሀገር **/ ከዚህ በኋላ ማሻሻያውን ያቀረበው የስምምነቱ አባል ሀገር ተብሎ የሚጠራ/** ልዩ ሁኔታዎች መኖራቸውን ከሚያሳዩ ማስረጃዎች ጋር ጥያቄውን ለጽ/ቤቱ በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. ጽህፈት ቤቱ ጥያቄው እንደደረሰው ወዲያውኑ ለስምምነቱ አባል ሀገራት ማሰራጨት አለበት፡፡

4. አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ማሻሻያ በቀረበበት የቀረጥ ስምምነት ሠንጠረዥ ላይ ከፍ ያለ ጥቅም አለኝ ብሎ ካሰበ /ከዚህ በኋላ ከፍ ያለ ጥቅም ያለው የስምምነቱ አባል ሀገር ተብሎ የሚጠራ/ በ30 ቀናት ውስጥ ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር በጽህፈት ቤቱ በኩል ማሻሻያውን ላቀረበው የስምምነቱ አባል ሀገር በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ጽህፈት ቤቱ እንዲህ አይነት ጥያቄዎችን እንደተቀበለ ወዲያውኑ ለሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት ማሰራጨት አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ማሻሻያውን ያቀረበው የስምምነቱ አባል ሀገር እና ከፍ ያለ ጥቅም ያለው የስምምነቱ አባል ሀገር በጽህፈት ቤቱ አስተባባሪነት በቀረበው የማሻሻያ ጥያቄና አስፈላጊ በሆኑ የማካካሻ ማስተካከያ ላይ ስምምነት ላይ ለመድረስ ወደ ድርድር መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ ድርድር እና ስምምነት አባል ሀገራት የሚገቡት ጠቅላላ ግዴታ በመነሻው ስምምነት ከተገባው ግዴታ ያነሰ ሊሆን አይችልም።

6. ከድርድሩ የሚገኘው ውጤት እና በቀጣይነት የሚከናወነው የቀረጥ ስምምነት ሠንጠረዥ ማስተካከያ እና የተያያዙ የማካካሻ ስምምነቶች በስራ ላይ የሚውሉት ከፍ ያለ ጥቅም ባለው የስምምነቱ አባል ሀገራት ሲፀድቅ እና ጽህፈት ቤቱ እንዲያውቀው ተደርጎ ለሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት እንዲደርስ ሲደረግ ነው፡፡ ማካካሻው በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 4 መሠረት ይከናወናል፡፡

7. The modifying State Party shall not modify its commitment until it has made compensatory adjustments as provided for in paragraph 6 and endorsed by the Council of Ministers. The outcome of the compensatory adjustment shall be notified to State Parties.

Article 12
Elimination of Non-Tariff Barriers

Except as may be provided for in this Protocol, the identification, categorisation, monitoring and elimination of Non-Tariff Barriers by State Parties shall be in accordance with the provisions of Annex 5 on Non-Tariff Barriers.

Article 13
Rules of Origin

Goods shall be eligible for preferential treatment under this Protocol, if they are originating in any of the State Parties in accordance with the criteria and conditions set out in Annex 2 on Rules of Origin, and in accordance with the Appendix to be developed on General and Product Specific Rules.

PART IV
CUSTOMS COOPERATION, TRADE FACILITATION AND TRANSIT

Article 14
Customs Cooperation and Mutual Administrative Assistance

State Parties shall take appropriate measures including arrangements regarding customs cooperation and mutual administrative assistance in accordance with the provisions of Annex 3 on Customs Cooperation and Mutual Administrative Assistance.

Article 15
Trade Facilitation

State Parties shall take appropriate measures including arrangements regarding trade facilitation in accordance with the provisions of Annex 4 on Trade Facilitation.

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት አስፈላጊው ማካካሻ እስከሚደረግ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት እስከሚፀድቅ ድረስ ማሻሻያውን ያቀረበው የስምምነቱ አባል የቀረጥ ስምምነት ሠንጠረዡ ላይ ማንኛውንም ማስተካከያ መተግበር አይችልም፡፡ የማካካሻ ማስተካከያው ድርድር ውጤት ሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት እንዲያውቁት መደረግ አለበት፡፡

አንቀጽ 12
ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎችን ስለማስወገድ

በዚህ ፕሮቶኮል በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በስምምነቱ አባል ሀገራት ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎችን የመለየት፣ የመመደብ ፣ የመከታተል እና የማስወገድ እንቅስቃሴ የሚከናወንበት ሁኔታ በአባሪ 5 ቀረጥ ያልሆኑ መሰናክሎች ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

አንቀጽ 13
የስሪት ሀገር ምንጭ ደንብ

ከስምምነቱ አባል ሀገራት የሚመነጩ ዕቃዎች በዚህ ፕሮቶኮል መሠረት ልዩ ጥቅም ለማግኘት፣ በአባሪ 2 የስሪት ሀገር ምንጭ ደንብ መሰረት ከስምምነቱ አባል ሀገራት የመነጩና፣ አጠቃላይ እና ዝርዝር ዕቃዎች ልዩ ደንቦችን በሚለዩ በሚዘጋጁ ተቀጽላዎች የሚካተቱ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡

ክፍል IV
የጉምሩክ ትብብር፣የንግድ ማሳለጥ እና ማስተላለፍ

አንቀጽ 14
የጉምሩክ ትብብር እና የጋራ አስተዳደራዊ መደጋገፍ

የስምምነቱ አባል ሀገራት የጉምሩክ ትብብር እና የጋራ አስተዳደራዊ መደጋገፍን ጨምሮ በአባሪ 3 የጉምሩክ ትብብርና የጋራ አስተዳደራዊ ድጋፍ ድንጋጌዎች መሰረት ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

አንቀጽ 15
ንግድን ማሳለጥ

የስምምነቱ አባል ሀገራት ንግድን ለማሳለጥ የሚያገለግሉና ሌሎች እርምጃዎችን በአባሪ 4 ንግድ ማሳለጥን አስመልከቶ በተቀመጡ ድንጋጌዎች መሰረት መተግበር አለባቸው።

Article 16
Transit

State Parties shall take appropriate measures including arrangements regarding transit in accordance with the provisions of Annex 8 on Transit.

PART V
TRADE REMEDIES

Article 17
Anti-dumping and Countervailing Measures

1. Subject to the provisions of this Protocol, nothing in this Protocol shall prevent State Parties from applying anti-dumping and countervailing measures.
2. In applying this Article, State Parties shall be guided by the provisions of Annex 9 on Trade Remedies and the AfCFTA Guidelines on Implementation of Trade Remedies in accordance with relevant WTO Agreements.

Article 18
Global Safeguard Measures

The implementation of this Article shall be in accordance with Annex 9 on Trade Remedies and Guidelines on Implementation of Trade Remedies, Article XIX of GATT 1994 and the WTO Agreement on Safeguards.

Article 19
Preferential Safeguards

1. State Parties may apply safeguard measures to situations where there is a sudden surge of a product imported into a State Party, under conditions which cause or threaten to cause serious injury to domestic producers of like or directly competing products within the territory.

አንቀጽ 16
ዕቃዎችን ስለማስተላለፍ

የስምምነቱ አባል ሀገራት ዕቃዎች የሚተላለፉበት አኳኋን ጨምሮ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን በአባሪ 8 ድንጋጌዎች መሠረት መተግበር አለባቸው፡፡

ክፍል V
የንግድ መፍትሄዎች

አንቀጽ 17
እቃዎች በርካሽ ሲራገፉና ከድጎማ የሚመነጩ ጉዳቶችን ለመከላከል ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

1. የዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በዚህ ፕሮቶኮል ውስጥ የስምምነቱ አባል ሀገራት እቃዎች በርካሽ እንዳይራገፉ እና ከድጎማ የመነጩ ጉዳቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን ከመውሰድ አይከለክልም ::

2. ይህን አንቀጽ በስራ ላይ በሚያውሉበት ጊዜ የስምምነቱ አባል ሀገራት ስለንግድ መፍትሄዎች በአባሪ 9 በተደነገገው እና የንግድ መፍትሄ አግባብነት ካላቸው የዓለም ንግድ ድርጅት ስምምነቶች ጋር ተጣጥመው እንዲፈጸሙ ለማስቻል የአፍሪካ የነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት በሚያወጣው የንግድ መፍትሄዎች መሰረት ይሆናል፡

አንቀጽ 18
ሁሉን አቀፍ የንግድ መከላከያ እርምጃዎች

የዚህ አንቀጽ ትግበራ በአባሪ 9 የተካተተው በንግድ መፍትሄዎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ የንግድ መፍትሄዎች እና መመሪያዎች እንዲሁም በ1994ቱ የቀረጥና ንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ XIX እና የዓለም የንግድ ድርጅት የንግድ መከላከያ እርምጃዎች ስምምነት መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡

አንቀጽ 19
በልዩ ጥቅም ስለሚስተናገዱ የንግድ መከላከያ እርምጃዎች

1. አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ከሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት የሚገባ እቃ ባልታሰበ ሁኔታ ጨምሮ ተመሳሳይ ወይም በቀጥታ ተወዳዳሪ የሆኑ የሀገሪቱ አምራቾች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ሲያደርስ ወይም የጉዳት አደጋ ሊያደርስ የሚቻልበት ሁኔታ ሲፈጥር የመከላከያ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፡፡

2. The implementation of this Article shall be in accordance with the provisions of Annex 9 on Trade Remedies and AfCFTA Guidelines on Implementation of Trade Remedies.

Article 20
Cooperation relating to Anti-dumping, Countervailing and Safeguards Investigations

State Parties shall cooperate in the area of trade remedies in accordance with the provisions of Annex 9 on Trade Remedies and AfCFTA Guidelines on Implementation of Trade Remedies.

PART VI
PRODUCT STANDARDS AND REGULATIONS

Article 21
Technical Barriers to Trade

The implementation of this Article shall be in accordance with the provisions of Annex 6 on Technical Barriers to Trade.

Article 22
Sanitary and Phytosanitary Measures

The implementation of this Article shall be in accordance with the provisions of Annex 7 on Sanitary and Phytosanitary Measures.

PART VII
COMPLEMENTARY POLICIES

Article 23
Special Economic Arrangements/Zones

1. State Parties may support the establishment and operation of special economic arrangements or zones for the purpose of accelerating development.

2. ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው በአባሪ 9 የንግድ መፍትሄዎች ድንጋጌዎች እና የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት የንግድ መፍትሄዎች የአተገባበር መመሪያ መሠረት ነው፡፡

አንቀጽ 20
እቃዎች በርካሽ ሲራገፉ፣ ከድጎማ የሚመነጩ ጉዳቶችን ለመከላከል እና የንግድ መከላከያ እርምጃዎች ምርመራ ላይ ስለመተባበር

የስምምነቱ አባል ሀገራት በአባሪ 9 የንግድ መፍትሄዎች ድንጋጌዎች እና የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት የንግድ መፍትሄዎችን በተግባር ላይ ስለማዋል በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት በንግድ መፍትሄዎች ላይ መተባበር አለባቸው፡፡

ክፍል VI
ስለምርቶች ደረጃዎችና ቴክኒካዊ ደንቦች

አንቀጽ 21
የንግድ ቴክኒካዊ እንቅፋቶች

የዚህ አንቀጽ ትግበራ ስለ ንግድ ቴክኒካዊ እንቅፋቶች በሚደነግገው አባሪ 6 መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 22
ስለሰው፣ እንሰሳትና፣ እጽዋት ጤና አጠባበቅ እርምጃዎች

የዚህ አንቀጽ ትግበራ የእንሰሳት፣ የእጽዋትና የሰው ጤና የመጠበቅ እርምጃዎች አባሪ 7 በሚደነግገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል VII
ስለደጋፊ ፖሊሲዎች

አንቀጽ 23
ስለ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች/አወቃቀሮች

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማፋጠን የሚያግዙ ልዩ የኢኮኖሚ አወቃቀሮችን ወይም ዞኖችን መቋቋምና ስራ ላይ መዋልን ሊደግፉ ይችላሉ፡፡

2. Products benefiting from special economic arrangements or zones shall be subject to any regulations that shall be developed by the Council of Ministers. Regulations under this paragraph shall be in support of the continental industrialisation programmes.
3. The trade of products manufactured in special economic arrangements or zones within the AfCFTA shall be subject to the provisions of Annex 2 on Rules of Origin.

Article 24
Infant Industries

1. For the purposes of protecting an infant industry having strategic importance at the national level, a State Party may, provided that it has taken reasonable steps to overcome the difficulties related to such infant industry, impose measures for protecting such an industry. Such measures shall be applied on a non-discriminatory basis and for a specified period of time.
2. Council of Ministers shall adopt guidelines for implementation of this Article as an integral part of this Protocol.

Article 25
Transparency and Notification requirements for State Trading Enterprises

1. In order to ensure the transparency of the activities of State Trading Enterprises (STE), State Parties shall notify such enterprises to the Secretariat for transmission to other State Parties.
2. For the purpose of this Article, STE refers to governmental, non- governmental enterprises, including Marketing boards, which have been granted exclusive or special rights or privileges, including statutory or constitutional powers, in the exercise of which they influence through their purchases or sales the level or direction of imports or exports with reference to provisions of Article XVII of GATT 1994.

2. በልዩ የኢኮኖሚ አወቃቀሮች ወይም ዞኖች ተጠቃሚ የሚሆኑ ምርቶች የሚኒስትሮቹ ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት የሚገዙ ይሆናል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወጣ ደንብ አህጉራዊ የኢንዱስትሪ ልማት ፕሮግራሞችን የሚደግፍ መሆን ይኖርበታል፡፡

3. በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ውስጥ በሚገኙ በልዩ ኢኮኖሚ አወቃቀሮች ወይም ዞኖች የሚመረቱ ምርቶች ንግድ በአባሪ 2 የስሪት ሀገር ምንጭ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

አንቀጽ 24
ስለጨቅላ ኢንዱስትሪዎች

1. በሀገር ደረጃ ስትራቴጅያዊ ጠቀሜታ ያለውን ጨቅላ ኢንዱስትሪ ለመጠበቅ ሲባል የስምምነቱ አባል ሀገር የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው ጨቅላ ኢንዱስትሪው ያጋጠመውን ችግሮች ለመቅረፍ አግባብ ያላቸው እርምጃዎችን ከተወሰዱ በኋላ ነው፡፡ የሚወሰዱት እርምጃዎችም ያለ አድሎ እና በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ብቻ የሚተገበሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አንቀጽ ለማስፈፀም የሚያስችል እና የዚህ ፕሮቶኮል ክፍል የሚሆን ደንብ ያወጣል፡፡

አንቀጽ 25
የመንግስት የንግድ ድርጅቶችን በተመለከተ የግልፅነት እና የማሳወቅ ግዴታዎች

1. የመንግስት የንግድ ድርጅቶች ተግባራትን ግልፅነት ለማረጋገጥ እንዲቻል የስምምነቱ አባል ሀገራት ስለድርጅቶቻቸው ለጽህፈት ቤቱ ያሳውቃሉ፣ ጽህፈት ቤቱም ወደ ሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት መረጃውን ያስተላልፋል።

2. ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ሲባል፣የመንግስት የንግድ ድርጅቶች ማለት በ1994 ዓ.ም.ቱ የቀረጥና እና ንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ XVII መሠረት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በዕቃ ግዥ ወይም ሽያጭ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ወይም ለውጭ ገበያ በሚላኩ ዕቃዎች መጠንና አቅጣጫ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የሚያስችል ከህግ ወይም ከህገ መንግስት የመነጨ ስልጣን፣ ብቸኛ ወይም ልዩ መብቶችና ጥቅሞች ያላቸው የገበያ ቦርዶችን ጨምሮ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ኢንተርፕራይዞች ናቸው።

PART VIII
EXCEPTIONS

Article 26
General Exceptions

Subject to the requirement that such measures are not applied in a manner which would constitute a means of arbitrary or unjustifiable discrimination between State Parties where the same conditions prevail, or a disguised restriction on international trade, nothing in this Protocol shall be construed as preventing the adoption or enforcement of measures by any State Party that are:

(a) necessary to protect public morals or to maintain public order;

(b) necessary to protect human, animal or plant life or health;

(c) relating to the importations and exportations of gold or silver;

(d) relating to the products of prison labour;

(e) necessary to secure compliance with laws or regulations which are not inconsistent with the provisions of this Protocol, including those relating to customs enforcement, the protection of patents, trademarks and copyrights, and the prevention of deceptive practices;

(f) imposed for the protection of national treasures of artistic, historic or archaeological value;

(g) relating to the conservation of exhaustible natural resources if such measures are made effective in conjunction with restrictions on domestic production or consumption;

(h) undertaken in pursuance of obligations under any intergovernmental commodity agreement approved by the State Parties;

(i) involving restrictions on exports of domestic materials necessary to ensure essential quantities of such materials to a domestic processing industry during periods when the domestic price of such materials is held below the world price as part of a governmental stabilisation plan, provided that such restrictions shall not operate to increase the exports of or the protection afforded to such domestic industry, and shall not depart from the provisions of this Protocol relating to non-discrimination; and

ክፍል VIII
ልዩ ሁኔታዎች

አንቀጽ 26
ጠቅላላ ልዩ ሁኔታዎች

በስምምነቱ አባል ሀገራት መካከል ተመሳሳይ ሁኔታዎች እያሉ በዘፈቀደ ወይም ተገቢነት በሌለው አድልዎ ወይም በአለም አቀፍ ንግድ ላይ ድብቅ ክልከላ በሚፈጥር መንገድ እስካልተተገበሩ ድረስ ፣የትኛውም የዚህ ፕሮቶኮል ክፍል ማንኛውንም የስምምነቱ አባል ሀገር የሚከተሉትን እርምጃዎች ከመወሰድ ወይም ከማስፈጸም የሚከለክለው ተደርጎ መተርጎም የለበትም፤

(ሀ) የሕዝብ ሞራል ለመጠበቅ ወይም የህዝብን ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

(ለ) የሰዎችን የእንስሳትና የእጽዋትን ህይወትና ጤና ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

(ሐ) ወርቅ ወይም ብርን ከሀገር ውስጥ ከማስገባት ወይም ከማስወጣት ጋር የተገናኘ ሲሆን፤

(መ) ከእስረኞች ጉልበት የተመረቱ ምርቶች ጋር የተገናኙ ሲሆን፣

(ሠ) ከዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎች ጋር የማይጣረሱ ሕግና ደንቦች መከበራቸውን ለማረጋገጥ፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ማስከበርን ጨምሮ ፣የፊጠራ ስራ ባለቤትነትን ፣ የንግድ ምልክት እና የቅጅ ሙብትን ለመጠበቅ እና የማታለል ተግባሮችን ለመከላከል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

(ረ) ስነ ጥበባዊ፣ ታሪካዊ ወይም አርኪዎሎጂዊ እሴት ያላቸውን ብሔራዊ ቅርሶችን ለመጠበቅ ሲባል፣

(ሰ) ታዳሽ ያልሆነ የተፈጥሮ ሀብትን ከመጠበቅ ጋር የተገናኙ እርምጃዎች ሆነው በሀገር ውስጥ የማምረትና እና ፍጆታዎች ላይ ከሚጣል ገደብ ጋር በጥምረት ተፈፃሚ ሲደረጉ፣

(ሸ) በአባል ሀገሮች የፀደቀ ማንኛውም በበይነ መንግስታት መካከል የተደረገ የሽቀጦች ስምምነት ግዴታዎችን ለመወጣት፣

(ቀ) በመንግስት ገበያ ማረጋጊያ መርሀ ግብር አማካኝነት የሀገር ውስጥ ግብዓት ዋጋ ከአለም ዋጋ በተነፃፃሪነት በወረደበት ሁኔታ ብቻ የሚተገበሩና ለሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪ በቂ የግብዓት መጠን እንዲያገኝ የሚያስችሉ የወጪ ንግድ ክልከላዎች ፡፡ ይሁንና እነዚህ ክልከላዎች የሀገር ውስጥ አምራቾችን ከውድድር ለመጠበቅ ወይንም የወጪ ንግድን ለማሳደግ የማይውሉ እና በተጨማሪም በዚህ ፕሮቶኮል አድሎአዊ አሰራሮችን ስለመከልከል በተቀመጡት አንቀፆች መሰረት የሚተገበሩ ሲሆን፣

(j) essential to the acquisition or distribution of foodstuffs or any other products in general or local short supply, provided that any such measures shall be consistent with the principle that all State Parties are entitled to an equitable share of the international supply of such products, and that any such measures, which are inconsistent with the other provisions of the Protocol shall be discontinued as soon as the conditions giving rise to them have ceased to exist.

Article 27
Security Exceptions

Nothing in this Protocol shall be construed to:

(a) require any State Party to furnish any information the disclosure of which it considers contrary to its essential security interests; or

(b) prevent any State Party from taking any action which it considers necessary for the protection of its essential security interests:

i. relating to fissionable materials or the materials from which they are derived;

ii. relating to the traffic in arms, ammunition and implements of war and to such traffic in other goods and materials taking place either directly or indirectly for the purpose of supplying a military establishment; and

iii. taken in time of war or other emergency in international relations; or

(c) prevent any State Party from taking any action in pursuance of its obligations under the United Nations Charter for the maintenance of international peace and security.

Article 28
Balance of Payments

1. Where a State Party is in critical balance of payments difficulties, or under imminent threat thereof, or has the need to safeguard its external financial position difficulties and that has taken all reasonable steps to overcome the difficulties, may adopt appropriate restrictive measures in accordance with international rights and obligations of the State Party concerned, including those under the WTO Agreement, the Articles of Agreement of the International Monetary Fund and the African Development Bank respectively. Such measures shall be equitable, non-discriminatory, in good faith, of limited duration and may not go beyond what is necessary to remedy the balance of payments situation.

(በ) የምግብ ወይም የሌሎች ምርቶችን መያዝና ማከፋፈል ወይም የሃገር ውስጥ እጥረትን ለመፍታት ሲባል የሚወሰዱ እርምጃዎች። ይሁንና እነዚህ እርምጃዎች በሁሉም አባል ሀገራት መካከል የፍትሃዊ ተጠቃሚነትና፣ የወቅታዊ ችግሮቹን መቅለል ተከትሎ ከዚህ ፕሮቶኮል ጋር ያልተጣጣሙ እርምጃዎች መነሳት ይኖርባቸዋል።

አንቀጽ 27
የደህንነት የተለዩ ሁኔታዎች

በዚህ ፕሮቶኮል የተደነገገው ቢኖርም፤

(ሀ) ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ይፋ መደረጋቸው ሀገራዊ ደህንነቱን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ መረጃዎችን እንዲያቀርብ አይገደድም ፣ወይም

(ለ) ማንኛውም አባል ሀገር የደህንነት ፍላጎቱን ለማስጠበቅ አስፈላጊ የሆነና በሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን ለመከላከል፤

፩. ከኑክሊየር ሀይል የሚያመነጩ ኢቃዎች ወይም ከእነዚህ ከመነጩ ኢቃዎች የተገናኘ፣

፪. ከጦር መሳሪያ ዝውውር ጋር የተያያዘ፣ ጥይት እና ለጦርነት የሚውሉ እና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለወታደራዊ ተቋም የሚውሉ ሌሎች ዕቃዎችና ቁሶች ፣ እና

፫. በጦርነት ጊዜ ወይም ሌሎች ከዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ጋር በተገናኘ የሚወሰዱ አስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች

መወሰድ አይከለከልም፤ ወይም

(ሐ) ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር በተባበሩት መንግስታት ቻርተር መሠረት ዓለምአቀፍ ሠላምና ደህንነትን ለማስጠበቅ ያለበትን ግዴታ ለመወጣት የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ አይከለከልም።

አንቀጽ 28
የክፍያ ሚዛን

1. አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር አሳሳቢ የክፍያ ሚዛን ጉድለት ችግር በገጠመው ጊዜ ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ ይከሰታል ተብሎ ሲታሰብ ወይም አለም አቀፍ የፋይናንስ ቁመናው ጋር በተገናኘ የገጠመውን ችግር አስቀድሞ መከላከል ሲያስፈልገው እና ችግሩን ለመቅረፍ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች የወሰደ ከሆነ፣ የዓለም ንግድ ድርጅት ስምምነት ድንጋጌዎችን ጨምሮ ከሚመለከተው አለም አቀፍ መብትና ግዴታዎች፣ የዓለም የገንዘብ ተቋም ስምምነት አንቀጾችን እና እንደአግባብነቱ በአፍሪካ የልማት ባንክ ጋር በተጣጣመ መልኩ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል። አነዚህ እርምጃዎችም ፍትሀዊ የሆነ፣ ከአድሎ የነፃ፣ በቅን ልቦና የተመሰረተ፣ በጊዜ የተገደበና የክፍያ ሚዛን ጉድለቱን ለማስተካከል ከሚያስፈልገው በላይ የማይቀጥል መሆን ይኖርበታል።

2. The State Party concerned, having adopted or maintained such measures shall inform the other State Parties forthwith and submit, as soon as possible, a time schedule for their removal.

PART IX
TECHNICAL ASSISTANCE, CAPACITY BUILDING AND COOPERATION

Article 29
Technical Assistance, Capacity Building and Cooperation

1. The Secretariat, working with State Parties, RECs and partners, shall coordinate and provide technical assistance and capacity building in trade and trade related issues for the implementation of this Protocol.
2. State Parties agree to enhance cooperation for the implementation of this Protocol.
3. The Secretariat shall explore avenues to secure resources required for these programmes.

PART X
INSTITUTIONAL PROVISIONS

Article 30
Consultation and Dispute Settlement

Except as otherwise provided in this Protocol, the relevant provisions of the Protocol on Rules and Procedures on the Settlement of Disputes shall apply to consultations and the settlement of disputes under this Protocol.

Article 31
Implementation, Monitoring and Evaluation

1. The Council of Ministers in accordance with Article 11 of the Agreement shall establish the Committee on Trade in Goods, which shall carry out such functions as may be assigned to it by the Council of Ministers to facilitate the operation of this Protocol and further its objectives. The Committee may establish such subsidiary bodies as it considers appropriate for the effective discharge of its functions.

2. የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር እርምጃውን ከወሰደ ወይም ከተገበረ በኋላ ወዲያውኑ ሰለተወሰደው እርምጃና ስለሚያበቃበት የጊዜ ሰሌዳ ለሌሎች አባል ሀገራት በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅ አለበት፡፡

ክፍል IX
የቴክኒክ ድጋፍ ፣ አቅም ግንባታ እና ትብብር

አንቀጽ 29
የቴክኒክ ድጋፍ፣ አቅም ግንባታ እና ትብብር

1. ጽህፈት ቤቱ ከስምምነቱ አባል ሀገራት፣ ከአካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰቦች እና ኢጋሮች ጋር አብሮ በመስራት ይህንን ፕሮቶኮል ለመተግበር የሚያግዙና ከንግድ እና ከንግድ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የቴክኒክ ድጋፍና እና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል፡፡
2. የስምምነቱ አባል ሀገራት ይህን ፕሮቶኮል ለማስፈፀም በትብብር ለመስራት ተስማምተዋል፡፡
3. ጽህፈት ቤቱ ለነዚህ ፕሮግራሞች አስፈላጊ የሆነውን አቅም ለማሟላት የተለያዩ መንገዶችን ያፈላልጋል፡፡

ክፍል X
ተቋማዊ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 30
ምክክር እና አለመግባባቶች ስለመፍታት

በዚህ ፕሮቶኮል በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር አግባብነት ያላቸው የምክክር እና የአለመግባባቶች መፍቻ ደንቦችና ሥነ ሥርዓቶች ፕሮቶኮል በዚህ ፕሮቶኮል ላይ በተደነገጉ ጉዳዮች በሚደረጉ የምክክርና አለመግባባቶች የመፍታት ሂደቶች ላይ ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

አንቀጽ 31
ትግበራ፣ ክትትልና እና ምዘና

1. በዚህ ስምምነት አንቀጽ ፲፩ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የእቃዎች ንግድን በተመለከተ የዕቃዎች ንግድ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡ ኮሚቴውም ይህንን ፕሮቶኮል ለማስፈፀም እና ሌሎች ዓላማዎችን ለማሳካት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰጠውን ተግባራት ያከናውናል፡፡ ኮሚቴው ለስራው ውጤታማነት ተገቢ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ተጨማሪ የበታች አካላትን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2. This Committee and its subsidiary bodies, shall be open to participation by representatives of all State Parties unless otherwise decided.
3. The Chairperson of the Committee shall be elected by the State Parties.
4. In accordance with Article 13(5) of the Agreement, the Secretariat shall, in consultation with State Parties, prepare annual factual reports to facilitate the process of implementation, monitoring and evaluation of this Protocol.
5. These reports should be considered and adopted by the Council of Ministers.

Article 32
Amendment

Amendment to this Protocol shall be in accordance with Article 29 of the Agreement.

2. በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ኮሚቴው እና በስሩ የሚቋቋሙ አካላት ለሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት ተሳትፎ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡
3. የኮሚቴው ሰብሳቢ በስምምነቱ አባል ሀገራት ይመረጣል ፡፡
4. ጽህፈት ቤቱ በዚህ ስምምነት አንቀጽ 13(5) መሠረት ከስምምነቱ አባል ሀገራት ጋር በመማካከር የዚህን ፕሮቶኮል ትግበራ፣ቁጥጥር እና ምዘና ሂደትን የሚያመቻቹ አመታዊ የፍሬ ነገር ሪፖርቶችን ያዘጋጃል፡፡
5. አነዚህ ሪፖርቶችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በመገምገም ያፀድቃል።

አንቀጽ 32
ማሻሻያ

የዚህ ፕሮቶኮል ማሻሻያ በዚህ ስምምነት አንቀጽ 29 መሠረት መሆን ይኖርበታል፡፡

PROTOCOL ON TRADE IN SERVICES

የአገልግሎት ንግድ ፕሮቶኮል

PROTOCOL ON TRADE IN SERVICES

PREAMBLE

WE, Member States of the African Union,

DETERMINED to establish a continental framework of principles and rules for trade in services with a view to boosting intra-African trade in line with the objectives of the African Continental Free Trade Area (AfCFTA) and promoting economic growth and development within the continent;

DESIROUS to create, on the basis of progressive liberalisation of trade in services, an open, rules based, transparent, inclusive and integrated single services market which provides economic, social and welfare-enhancing opportunities across all sectors for the African people;

MINDFUL of the urgent need to consolidate and build on achievements in services liberalisation and regulatory harmonisation at the Regional Economic Community (REC) and continental levels;

DESIRING to harness the potential and capacities of African services suppliers, in particular at the micro, small and medium levels, to engage in regional and global value chains;

RECOGNISING the right of State Parties to regulate in pursuit of national policy objectives, and to introduce new regulations, on the supply of services, within their territories, in order to meet legitimate national policy objectives, including competitiveness, consumer protection and overall sustainable development with respect to the degree of the development of services regulations in different countries, the particular need for State Parties to exercise this right, without compromising consumer protection, environmental protection and overall sustainable development;

COGNISANT of the serious difficulty of the least developed, land locked, island states and vulnerable economies in view of their special economic situation and their development, trade and financial needs;

ACKNOWLEDGING the African Union Assembly Decision Assembly/AU/666 (XXX) adopted at the 30th Ordinary Session of the Assembly of Heads of State and Government of the AU, in Addis Ababa, Ethiopia on 28 January 2018 on the Establishment of a Single African Air Transport Market through the Implementation of the Yamoussoukro Decision;

FURTHER RECOGNISING the potentially significant contribution of air transport services and, in particular, the Single African Air Transport Market to boost intra-African trade and fast track the African Continental Free Trade Area (AfCFTA),

HAVE AGREED AS FOLLOWS:

የአገልግሎት ንግድ ፕሮቶኮል

መግቢያ

እኛ የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት፣

በአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ዓላማ መሰረት አህጉራዊ ንግድን ለማሳደግ እና አህጉራዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ለማምጣት ያለመ የአገልግሎት ንግድ አህጉራዊ መርሆዎችና ህጎች ማዕቀፍ ለማቋቋም **በመወሰን፣**

በሂደት እያደገ የሚሄድ የአገልግሎት ነጻ ንግድ፣ ክፍት፣በህግ ላይ የተመሰረተ፣ ግልጽ፣ አካታችና የተሳሰረ አንድ የአገልግሎት ገበያ መፍጠር ላይ በመንተራስ ለሁሉም የአፍሪካ ህዝቦች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ደህነትን የሚያሰፉ ዕድሎች ማምጣት **በማስፈለጉ፣**

በአካባቢያዊ የንግድ ማህበረሰብ እና በአህጉር ደረጃ አገልግሎቶችን ነጻ በማድረግና ህጎችን በማጣጣም በተገኙ ውጤቶች ላይ ተመርኩዞ እነዚህኑ ማጠናከር ጊዜ የማይሰጥ ፍላጎት መሆኑን **ከግምት ውስጥ በማስገባት፣**

የአፍሪካን በተለይም ጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ አገልግሎት ሰጪዎችን ያላቸውንና እምቅ አቅማቸውን በመጠቀም በአካባቢያዊና በአለምአቀፍ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ **በመሻት፣**

አባል ሀገራት በግዛታቸው ውስጥ የብሄራዊ ፖሊሲ ዓላማዎችን ለማሳካት የሚያስችሉ የአገልግሎት አቅርቦትን የመቆጣጠርና አዳዲስ ህጎችን የማውጣት መብት እንዳላቸው፣ ህጋዊ የብሄራዊ ፖሊሲ አላማዎችን ጨምሮ የውድድር፣ የሸማቾች ጥበቃና ሁሉን አቀፍ ቀጣይነት ያለው ዕድገት በተገናኘ በተለያዩ ሀገሮች ያለው የአገልግሎት ህጎች ደረጃ፣ የሸማቾች ጥበቃን ፣ የአካባቢያዊ ጥበቃና አጠቃላይ ቀጣይነት ያለው ዕድገት ሳይጻረር ይህንን መብት ለመተግበር የስምምነቱ አባል ሀገርን የተለየ ፍላጎትን **እውቅና በመስጠት፣**

በልዩ የኢኮኖሚ ሁኔታቸውና በልማት ደረጃቸው፣ የንግድና የፋይናንስ ፍላጎት የተነሳ በልማት ወደኋላ የቀሩ ሀገራት፣ ወደብ አልባ፣ ደሴት ሀገሮች እና ለጉዳት ተጋላጭ ኢኮኖሚዎች ያለባቸውን አንገብጋቢ ችግር **በመገንዘብ፣**

በጃንዋሪ 28 ቀን 2018 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ በተካሄደው 30ኛው መደበኛ የመንግስታትና የሀገራት መሪዎች ጉባኤ በጸደቀው የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ውሳኔ AU/666 (XXX) የያማሶኩሩ ውሳኔን በመተግበር አንድ የአፍሪካ የአየር ትራንስፖርት ገበያ ማቋቋምን **እውቅና በመስጠት፣**

የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት እና በተለይም አንድ የአፍሪካ የአየር ትራንስፖርት ገበያ አህጉራዊ ንግድ ለማሳደግ እና የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣናን ለማፋጠን ያለውን እምቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦን **በተጨማሪ እውቅና በመስጠት፣**

እንደሚከተለዉ ተስማምተናል፤

PART I
DEFINITIONS

Article 1
Definitions

For the purposes of this Protocol:

(a) **"Commercial presence"** means any type of business or professional establishment, including through:

i. the constitution, acquisition or maintenance of a juridical person, or

ii. the creation or maintenance of a branch or a representative office, within the territory of a State Party for the purpose of supplying a service;

(b) **"Direct taxes"** comprise all taxes on total income, on total capital or on elements of income or of capital, including taxes on gains from the alienation of property, taxes on estates, inheritances and gifts, and taxes on the total amounts of wages or salaries paid by enterprises, as well as taxes on capital appreciation;

(c) **"Juridical person"** means any legal entity duly constituted or otherwise organised under applicable law of State Parties, whether for profit or otherwise, and whether privately-owned or governmentally-owned, including any corporation, trust, partnership, joint venture, sole proprietorship or association;

(d) **A juridical person is:**

i. "Affiliated" with another person when it controls, or is controlled by, that other person; or when it and the other person are both controlled by the same person;

ii. "Controlled" by persons of a State Party if such persons have the power to name a majority of its directors or otherwise to legally direct its actions; and

iii. "Owned" by persons of a State Party if more than 50 per cent of the equity interest in it is beneficially owned by persons of that State Party;

ክፍል I
ትርጉም

አንቀጽ 1
ትርጉም

ለዚህ ፕሮቶኮል ሲባል፣

(ሀ) **"ለንግድ ስራ በአካል መገኘት"** ማለት የሚከተሉትን ጨምሮ ማንኛውም ዓይነት የንግድ ስራ ወይም ሙያዊ ተቋም ነው፣

ⴰ. ህጋዊ ሰውነትን በመመስረት፣ በማግኘት ወይም የነበረውን ማስቀጠል፣ ወይም

ⴱ. በስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት አገልግሎትን ለማቅረብ የቅርንጫፍ ወይም ወኪል ቢሮ መክፈት ወይም የነበረውን ማስቀጠል፣

(ለ) **"ቀጥተኛ ታክስ"** ሁሉንም የጠቅላላ ገቢ ፣ የጠቅላላ ካፒታል ወይም የገቢ ወይም ካፒታል የተወሰነ ክፍል ታክስ፤ ከንብረት ባለቤትነት መብት ማስተላለፍ የሚገኝ ፣ የሀብትና ንብረት፣ የውርስና ስጦታ እና ድርጅቶች ከሚከፍሉት ጠቅላላ ደመወዝ ወይም ክፍያ ታክሶችን ጨምሮ እንዲሁም የካፒታል ማሳደግ ታክሶችን ያካትታል፣

(ሐ) **"በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው"** ማለት በስምምነቱ አባል ሀገሩ አግባብ ባለው ህግ የተቋቋመ ወይም የተደራጀ ኮርፖሬሽን፣ ትረስት፣የጋራ፣ ሽርክና ፣የግል ንግድን ወይም ማህበርን ጨምሮ ለትርፍም ሆነ ሌላ ዓላማ የተቋቋመ እና የመንግስትም ሆነ የግል፣ ማንኛውም የህግ አካል ማለት ነው።።

(መ) **አንድ በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው፣ -**

ⴰ. ሌላ ሰውን ለመቆጣጠር ወይም በሌላ ሰው ቁጥጥር ሲደረግበት ወይም ሁለቱም ሰዎች በተመሳሳይ ሰው ቁጥጥር የመደረግ **"ግንኙነት ያለው"** ፣

ⴱ. በስምምነቱ አባል ሀገር ሰው **"ቁጥጥር"** ሲደረግና ይህ ሰው አብላጫውን ዳይሬክተሮች ለመሰየም ወይም በህግ ስራውን ለመምራት ሥልጣን ያለው ሲሆን፣ እና

ⴲ. በስምምነቱ አባል ሀገር ሰው ከ 50 ፐርሰንት ድርሻ በላይ **"ባለቤትነት"** ከኖረውና በዚያ የስምምነቱ አባል ሀገር ሰው የሚተዳደር ነው።።

(e) **"Juridical person of another State Party"** means a juridical person which is either:

i. constituted or otherwise organised under the law of that other State Party, and is engaged in substantive business operations in the territory of that State Party or any other State Party; or

ii. in the case of the supply of a service through commercial presence, owned or controlled by:

1. natural persons of that State Party; or
2. juridical persons of that other State Party identified under subparagraph (i);

(f) **"Measure"** means any measure by a State Party, whether in the form of a law, regulation, rule, procedure, decision, administrative action, or any other form;

(g) **"Measures by State Parties affecting trade in services"** include measures in respect of:

i. the purchase, payment or use of a service;

ii. the access to and use of, in connection with the supply of a service, services which are required by those State Parties to be offered to the public generally;

iii. the presence, including commercial presence, of persons of a State Party for the supply of a service in the territory of another State Party;

(h) **"Monopoly supplier of a service"** means any person, public or private, which in the relevant market of the territory of a State Party operates as or is authorised or established formally or in effect by that State Party as the sole supplier of that service;

(i) **"Natural person of another State Party"** means a natural person who resides in the territory of that other State Party or any other State Party and who under the law of that other State Party:

i. is a national; or

ii. has the right of permanent residence;

(j) **"Person"** means either a natural person or a juridical person;

(ሥ) **"በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው"** ማለት በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ፡

ፅ. በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ህግ መሰረት የተቋቋመ ወይም በተለየ መንገድ የተደራጀ እና በዚያው የስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት ውስጥ ወይም በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር በተጨባጭ የቢዝነስ እንቅስቃሴ የተሰማራ ፣ ወይም

ፆ. በንግድ ስራ በአካል በመገኘት አገልግሎት ማቅረብን በሚመለከት በስምምነቱ አባል ሀገር ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ስር ያለ፡-

1. የዚያ የስምምነት አባል ሀገር የተፈጥሮ ሰው፣ ወይም

2. በንዑስ አንቀጽ (ቀ) በተመለከተው መሰረት በዚያ የስምምነት አባል ሀገር በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው፣

(ረ) **"እርምጃ"** ማለት በስምምነቱ አባል ሀገር በህግ፣ በደንብ፣በአሰራር፣ በውሳኔ፣ አስተዳደራዊ ድርጊት ወይም በማንኛውም ሌላ አይነት መንገድ የሚወሰድ ማንኛውም እርምጃ ማለት ነው፣

(ሰ) **"በስምምነቱ አባል ሀገራት የአገልግሎት ንግድ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እርምጃዎች"** የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ፅ. የአገልግሎት ግዢ፣ ክፍያና አጠቃቀም፣

ፄ. ከአገልግሎት አቅርቦት ጋር በተገናኘ ለስምምነቱ አባል ሀገራት የሚያስፈልጉና ለአጠቃላይ ህዝብ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ተደራሽነትና አጠቃቀም ፣

ፏ. የአንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ሰዎች በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት አገልግሎት ለማቅረብ በንግድ ስራ በአካል መገኘትን ጨምሮ መገኘት፣

(ሸ) **"ብቸኛ አገልግሎት አቅራቢ"** ማለት በስምምነቱ አባል ሀገር ገበያ እንቅስቃሴ ለማድረግ ወይም በይፋ ወይም በተግባር በስምምነቱ አባል ሀገር ብቸኛ የአገልግሎት አቅራቢነት ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም የግልም ሆነ የመንግስት ሰው ማለት ነው፤

(ቀ) **"የሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር የተፈጥሮ ሰው"** ማለት በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት ወይም በማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር የሚኖር የተፈጥሮ ሰው ሆኖ በዚያ የስምምነቱ አባል ሀገር ህግ መሰረት፡-

ፅ. ዜጋ የሆነ፣ ወይም

ፄ. ቋሚ የመኖሪያ መብት ያለው፣

(በ) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ማለት ነው፣

(k) **"Sector"** of a service means:

i. with reference to a specific commitment, one or more, or all, subsectors of that service, as specified in a State Party's schedule of specific commitments;

ii. otherwise, the whole of that service sector, including all of its subsectors;

(l) **"Service of another State Party"** means a service which is supplied:

i. from or in the territory of that other State Party, or in the case of maritime transport, by a vessel registered under the laws of that other State Party, or by a person of that other State Party which supplies the service through the operation of a vessel and/or its use in whole or in part; or

ii. in the case of the supply of a service through commercial presence or through the presence of natural persons, by a service supplier of that other State Party;

(m) **"Service consumer"** means any person that receives or uses a service;

(n) **"Service supplier"** means any person that supplies a service[4];

(o) **"Supply of a Service"** includes the production, distribution, marketing, sale and delivery of a service;

(p) **"Trade in services"** means the supply of service:

i. from the territory of one State Party into the territory of any other State Party;

ii. in the territory of one State Party to the service consumer of any other State Party;

iii. by a service supplier of one State Party, through commercial presence in the territory of any other State Party;

iv. by a service supplier of one State Party, through presence of natural persons of a State Party in the territory of any other State Party.

[4]*Where the service is not supplied directly by a juridical person but through other forms of commercial presence such as a branch or representative office, the service supplier (i.e. the juridical person) shall, nonetheless, through such presence be accorded the treatment provided for service suppliers under the agreement. Such treatment shall be extended to the presence through which the service is supplied and need not be extended to any other parts of the supplier located outside of the territory where the service is supplied.*

(ተ) የአገልግሎት **"ዘርፍ"** ማለት፡-

ፅ. ዝርዝር ግዴታዎች ጋር በተገናኘ በስምምነቱ አባል ሀገር የግዴታዎች ሰንጠረዥ ላይ የተመለከቱ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ወይም ሁሉም የአገልግሎት ንዑስ ዘርፎች፣

ፆ. ወይም ሁሉንም ንዑስ ዘርፎች ጨምሮ ሁሉም የአገልግሎት ዘርፎች፣

(ቸ) **"የሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር አገልግሎት"** ማለት፣

ፅ. ከራሱ ወይም በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት ውስጥ ወይም የባህር ትራንስፖርትን በሚመለከት በዚያ ሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ህግ የተመዘገበ መርከብ, ወይም በሙሉ ወይም በከፊል የመርከቡ እንቅስቃሴ እና/ወይም አጠቃቀም በሚመለከት በስምምነቱ አባል ሀገር ሰው የተመዘገበ፣ወይም

ፆ. በንግድ ስራ በአካል በመገኘት ወይም በተፈጥሮ ሰው አማካኝነት በመገኘት አገልግሎት ማቅረብን በሚመለከት በዚያ የሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር አገልግሎት ማቅረብ፣

ማለት ነው፣

(ኀ) **"የአገልግሎት ተጠቃሚ"** ማለት ማንኛውም አገልግሎት ተገልጋይ ወይም የሚጠቀም ሰው ማለት ነው፣

(ነ) **"የአገልግሎት አቅራቢ"** ማለት ማንኛውም አገልግሎት የሚያቀርብ ሰው ማለት ነው[4]፣

(ኘ) **"አገልግሎት አቅርቦት"** አገልግሎት ማምረት፣ ማከፋፈል፣ ግብይት፣ ሽያጭ እና ማሰራጨትን ይጨምራል፣

(አ) **"የአገልግሎት ንግድ"** ማለት :-

ፅ. ከአንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት ወደሌላ ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት ፣

ፆ. አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር በራሱ ግዛት ውስጥ ሆኖ ለሌላ ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር የአገልግሎት ተጠቃሚ፣

ጵ. የአንድ የስምምነቱ አባል ሀገር አገልግሎት አቅራቢ በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ውስጥ ለንግድ ስራ በአካል በመገኘት የሚያቀርበው ፣

ፀ. የአንድ የስምምነቱ አባል ሀገር አገልግሎት አቅራቢ በሌላ ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር በተፈጥሮ ሰው አማካኝነት በመገኘት የሚያደርገው፣

የአገልግሎት አቅርቦት ማለት ነው፤

[4] አገልግሎቱ በቀጥታ የህግ ሰውነት ባለው የማይቀርብ ሲሆንና በሌላ ዓይነት የንግድ ስራ በአካል መገኘት ለምሳሌ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ቢሮ፣ አገልግሎት አቅራቢው (በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው) የሚቀርብ ሲሆን ይህ በአካል መገኘት አገልግሎት አቅራቢዎች አያያዝ በስምምነቱ መሰረት መስተናገድ አለበት፡፡ ይህ አያያዝ ወደሌላው አገልግሎት አቅርቦት የሚሰፋ ሲሆን በሌላ ግዛት ወደሚሰጥ አገልግሎት ግን አይሸጋገርም፡፡

PART II
SCOPE OF APPLICATION

Article 2
Scope of Application

1. This Protocol applies to measures by State Parties affecting trade in services.
2. For the purposes of this Protocol, trade in services is based on the four modes of supply of a service as defined in Article 1(p) of this Protocol.
3. For the purposes of this Protocol:
   (a) **"Measures by State Parties"** means measures taken by:
      i. State Parties' central, regional or local governments and authorities; and
      ii. Non-governmental bodies in the exercise of powers delegated by State Parties' central, regional or local governments or authorities.

      In fulfilling its obligations and commitments under the Protocol, each State Party shall take such reasonable measures as may be available to it to ensure their observance by regional and local governments and authorities and non-governmental bodies within its territory;
   (b) **"Services"** includes any service in any sector except services supplied in the exercise of governmental authority; and
   (c) **"A service supplied in the exercise of governmental authority"** means any service which is supplied neither on a commercial basis, nor in competition with one or more service suppliers.
4. Procurement by governmental agencies purchased for governmental purposes and not with a view to commercial re-sale are excluded from the scope of this Protocol.
5. This Protocol shall not apply to measures affecting:
   (a) air traffic rights, however granted; and

ክፍል II
የተፈጻሚነት ወሰን

አንቀጽ 2
የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ ፕሮቶኮል የስምምነቱ አባል ሀገራት በሚወስዷቸው የአገልግሎት ዘርፎች ላይ ተጽእኖ በሚያሳርፉ እርምጃዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፣

2. ለዚህ ፕሮቶኮል ሲባል የአገልግሎት ንግድ በአንቀጽ ነ(በ) መሰረት በአራት አገልግሎት መስጫ ዘዴዎች የተመለከተው ነው፣

3. ለዚህ ፕሮቶኮል ሲባል፣

   (ሀ) **"በስምምነቱ በአባል ሀገራት የሚወሰዱ እርምጃዎች"** ማለት፡-

      ፩. በስምምነቱ አባል ሀገራት ማዕከላዊ፣ክልላዊ እና አካባቢያዊ አስተዳደሮችና ባለስልጣናት እና

      ፪. በማዕከላዊ፣ክልላዊ እንዲሁም አካባቢያዊ ባለስልጣናት መንግስታዊ ላልሆኑ አካላት በውክልና በተሰጠ ስልጣን መሰረት ፣

      የሚወሰዱ እርምጃዎች ናቸው::

በፕሮቶኮሉ አማካኝነት የተወሰዱ ግዴታዎችና እና የተገቡ ቃል ኪዳኖችን ለመወጣት ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ያለውን ህግ በመንተራስ በግዛቱ ውስጥ የሚገኙ የክልላዊ መንግስታት ባለስልጣናት እና አካባቢያዊ አስተዳደሮች እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ህጉን እንዲያከብሩ ለማረጋገጥ የሚያስችል ተገቢ እርምጃዎችን መዉሰድ አለበት።

   (ለ) "አገልግሎቶች" መንግስታዊ ሃላፊነትን ለመወጣት ከሚሰጡ አገልግሎቶች ዉጪ ያሉትን ማንኛዉንም የአገልግሎት ዘርፍ ያጠቃልላል፤ እና

   (ሐ) "መንግስታዊ ሀላፊነትን ለመወጣት የሚሰጥ አገልግሎት" ማለት ማንኛውም በንግድ መልክ ወይም ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር በመወዳደር የማይሰጥ አገልግሎት ማለት ነው::

4. ለመንግሰት ስራ ጥቅም የሚውሉና ለንግድ እንደገና መሸጥን አላማ ያላደረጉ በመንግሰት ኤጀንሲዎች የሚደረጉ ግዢዎች ከዚህ ፕሮቶኮል ወሰን ውጪ ናቸው፤.

5. ይህ ፕሮቶኮል፣

   (ሀ) በማናቸውም መልኩ የተሰጡ የአየር የትራፊክ መብቶች፣ እና

(b) services directly related to the exercise of air traffic rights;

6. This Protocol shall apply to measures affecting:
   (a) aircraft repair and maintenance services;
   (b) the selling and marketing of air transport services; and
   (c) computer reservation system (CRS) services.

PART III
OBJECTIVES

Article 3
Objectives

1. The principal objective of this Protocol is to support the objectives of the AfCFTA, as set out in Article 3 of the Agreement particularly to create a single liberalised market for trade in services.
2. The specific objectives of this Protocol are to:
   (a) enhance competitiveness of services through: economies of scale, reduced business costs, enhanced continental market access, and an improved allocation of resources including the development of trade-related infrastructure;
   (b) promote sustainable development in accordance with the Sustainable Development Goals (SDGs);
   (c) foster domestic and foreign investment;
   (d) accelerate efforts on industrial development to promote the development of regional value chains;
   (e) progressively liberalise trade in services across the African continent on the basis of equity, balance and mutual benefit, by eliminating barriers to trade in services;
   (f) ensure consistency and complementarity between liberalisation of trade in services and the various Annexes in specific services sectors;

(ለ) የአየር ትራፊክ መብትን ከመጠቀም ጋር በቀጥታ የተገናኙ አገልግሎቶች፣

ተጽእኖ በሚያሳድሩ እርምጃዎች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

6. ይህ ፕሮቶኮል፣

(ሀ) የአውሮፕላን እድሳትና ጥገና፣

(ለ) የአየር ትራንስፖርት አገልግሎቶች ሽያጭና ግብይት እና

(ሐ) በኮምፒዩተር የትኬት ምዝገባ ስርዓት አገልግሎት፣

ተጽእኖ በሚያሳድሩ እርምጃዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

ክፍል III
ዓላማዎች

አንቀጽ 3
ዓላማዎች

1. የዚህ ፕሮቶኮል ዋነኛ ዓላማ በስምምነቱ አንቀጽ 3 በተቀመጠው መሰረት የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣናን በተለይም አንድ ነጻ አገልግሎት ገበያ የመፍጠር ዓላማን መደገፍ ነው፡፡

2. የፕሮቶኮሉ ዝርዝር ዓላማዎች፡-

(ሀ) በጥቅመ ግዝፈት ፣ ወጪን በመቆጠብ፣በተስፋፋ አህጉራዊ የገበያ እድል እና ንግድ ነክ የመሰረተ ልማት ግንባታ ማስፋፋትን ጨምሮ በተሻለ የሀብት አመዳደብ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል የአገልግሎት ዘርፍን ተወዳዳሪነት ማሳደግ፣

(ለ) ቀጣይነት ያለው ልማትን ቀጣይነት ያለው የልማት ግቦች መሰረት ማስፋፋት፣

(ሐ) የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ፣

(መ) የአካባቢያዊ የእሴት ሰንሰለት በማሳደግ የኢንዱስትሪ ልማት ጥረትን ማፋጠን ፣

(ሠ) በአገልግሎት ዘርፍ ያሉ የንግድ መሰናክሎችን በማስወገድ የአገልግሎት ንግድን በሚዛናዊነት፣በተመጣጠነና በእኩል ተጠቃሚነት ደረጃ በሂደት በአህጉሩ ነጻ ማድረግ፣

(ረ) የአገልግሎት ንግድን ነጻ በማድረግና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች አባሪዎች መካከል መጣጣምና መደጋገፍ መኖሩን ማረጋገጥ፣

(g) pursue services trade liberalisation in line with Article V of the GATS by expanding the depth and scope of liberalisation and increasing, improving and developing the export of services, while fully preserving the right to regulate and to introduce new regulations;

(h) promote and enhance common understanding and cooperation in trade in services amongst State Parties in order to improve the capacity, efficiency and competitiveness of their services markets; and

(i) promote research and technological advancement in the field of services to accelerate economic and social development.

PART IV
GENERAL OBLIGATIONS AND DISCIPLINES

Article 4
Most-Favoured-Nation Treatment

1. With respect to any measure covered by this Protocol, each State Party shall, upon entry into force, accord immediately and unconditionally to services and service suppliers of any other State Party treatment no less favourable than that it accords to like services and service suppliers of any Third Party.
2. Nothing in this Protocol shall prevent a State Party from entering into a new preferential agreement with a Third Party, in accordance with Article V of the GATS provided such agreements do not impede or frustrate the objectives of this Protocol. Such preferential treatment shall be extended to all State Parties on a reciprocal and non- discriminatory basis.
3. Notwithstanding paragraph 1, two (2) or more State Parties may conduct negotiations and agree to liberalise trade in services for specific sectors or sub-sectors in accordance with the objectives in this Protocol. Other State Parties shall be afforded opportunity to negotiate the preferences granted therein on a reciprocal basis.

(ሰ) የአገልግሎት ዘርፍን መቆጣጠርና አዳዲስ ህጎችን የማውጣት መብት ሙሉ ለሙሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ V መሰረት የነጻ ንግድ ጥልቀቱንና ወሰኑን በማስፋትና የአገልግሎት ዘርፍ ወጪ ንግድን በመጨመር፣ በማሳደግ እና በማስፋት የአገልግሎት ዘርፍን ነጻ የማድረግ አቅጣጫ መከተል፣

(ሸ) የአገልግሎት ገበያቸውን አቅም ፣ ብቃትና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በስምምነቱ አባል ሀገራት መካከል የአገልግሎት ንግድን በተመለከተ የጋራ መግባባትና ትብብር ማስፋፋትና ማሳደግ፣ እና

(ቀ) የኢኮኖሚ እድገትና የማህበራዊ ልማት ለማምጣት የሚያስችል የአገልግሎት ዘርፍ ምርምርና የቴክኖሎጂ ዕድገትን ማበረታታት፤

ክፍል IV
አጠቃላይ ግዴታዎች እና ሥርዓቶች

አንቀጽ 4
ሁሉንም ሀገራት ያለልዩነት ማስተናገድ

1. በዚህ ስምምነት የሚካተቱትን ማንኛውንም አይነት እርምጃዎች በተመለከተ፣ እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ለማንኛውም ሌላ ሶሥተኛ ወገን አገልግሎቶች እና አገልግሎት አቅራቢዎች የሰጠዉን ልዩ የንግድ ጥቅም ወዲያዉኑ እና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለስምምነቱ አባል ሀገራት ተመሳሳይ አገልግሎቶች እና አገልግሎት አቅራቢዎች ከሰጠው ጥቅም ባላነሰ ደረጃ በሚያስገኝ መልኩ መስጠት አለበት።

2. ይህ ፕሮቶኮል አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር የዚህን ፕሮቶኮል ዓላማዎች የሚያግድ ወይም የሚያጨናግፍ እስካልሆነ ድረስ ከሌላ ሶስተኛ ወገን ጋር ልዩ ጥቅም የሚሰጥ አዲስ ስምምነት በአገልግሎት ንግድ አጠቃላይ ስምምነት አንቀጽ V በሚጣጣም መልኩ ስምምነት ከማድረግ አይከለከለውም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ልዩ ጥቅም የሚሰጥ ስምምነት ለሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት በሰጥቶ መቀበል መሰረት ለማግኘት የመደራደር ዕድል መሰጠት ይኖርበታል፡፡

3. በንዑስ አንቀጽ ፣ የተጠቀሰው ቢኖርም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የስምምነቱ አባል ሀገራት ከዚህ ፕሮቶኮል አላማ ጋር በሚጣጣም መልኩ በተወሰኑ ዘርፎችና ንዑስ ዘርፎች የአገልግሎት ንግድ ድርድር በማካሄድ የአገልግሎት ንግድን ነጻ ለማድረግ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡ ሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት የተሰጠውን ልዩ ጥቅም በሰጥቶ መቀበል መርህ ለማግኘት እንዲችሉ የመደራደር ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

4. Notwithstanding the provisions of paragraph 2, a State Party shall not be obliged to extend preferences agreed with any Third Party prior to the entry into force of this Protocol, of which that State Party was a member or a beneficiary. A State Party may afford opportunity to the other State Parties to negotiate the preferences granted therein on a reciprocal basis.
5. The provisions of this Protocol shall not be so construed as to prevent any State Party from conferring or according advantages to adjacent countries in order to facilitate exchanges limited to contiguous frontier zones of services that are both locally produced and consumed.
6. A State Party may maintain a measure which is inconsistent with paragraph 1, provided it is listed in the Most Favoured Nation (MFN) exemption list. The agreed list of MFN exemptions shall be annexed to this Protocol. States Parties shall regularly review MFN exemptions, with a view to determining which MFN exemptions can be eliminated.

Article 5
Transparency

1. Each State Party shall, in a medium[5] that is accessible, publish promptly and, except in emergency situations, at the latest by the time of their entry into force, all relevant measures of general application which pertain to or affect the operation of this Protocol. International and regional agreements pertaining to or affecting trade in services to which a State Party is a signatory shall also be published.
2. Each State Party shall notify the Secretariat of any international and regional agreements pertaining to or affecting trade in services with Third Parties to which they are signatory prior to or after entry into force of this Protocol.
3. Each State Party shall promptly and at least annually notify the Secretariat of the introduction of any new, or any changes to, existing laws, regulations or administrative guidelines which significantly affect trade in services under this Protocol.
4. Where a State Party submits a notification to the Secretariat, the latter shall promptly circulate the said notification to all State Parties.

[5] *For example through Gazette, newsletter, Hansard, or websites in one of the African Union languages.*

4. በንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ይህ ፕሮቶኮል ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከሶስተኛ ወገኖች ጋር አባል ወይም ተጠቃሚ የሆነበትን ልዩ ጥቅም የሚያስገኝ ስምምነት ለስምምነቱ አባል ሀገራት ለመስጠት አይገደድም፡፡ አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ለሶስተኛ ወገን የሰጠውን ልዩ ጥቅም ሌሎች አባል ሀገራት በሰጥቶ መቀበል መርህ ለማግኘት እንዲደራደሩ እድል ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. የዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎች ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር በአዋሳኝ ሀገሮች ድንበር አካባቢዎች የተወሰኑ፣ በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ጥቅም ላይ ለሚውሉ አገልግሎቶች የተለዩ ጥቅሞችን መስጠት የሚከለክል ተደርጎ መተርጎም የለበትም፡፡

6. ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ከአንቀጽ ነ ጋር የማይጣጣሙ እርምጃዎችን ሁሉንም ሀገራት ያለልዩነት ማስተናገድ ግዴታ የማይመለከታቸው ዝርዝር ውስጥ በማካተት ሊያስጠብቅ ይችላል፡ : ስምምነት የተደረሰባቸው ሁሉንም ሀገራት ያለልዩነት ማስተናገድ ግዴታ የማይመለከታቸው ዝርዝር የፕሮቶኮሉ አባሪ ተደርጎ መያያዝ አለበት፡፡ የስምምነቱ አባል ሀገራት ሀገራትን ያለልዩነት የማስተናገድ ግዴታ የማይመለከታቸው ዝርዝር ሁኔታ፣ የትኞቹ ከዝርዝሩ መውጣት እንዳለባቸው ለመወሰን በመደበኛነት መገምገም አለባቸው፡፡

አንቀጽ 5
ስለ ግልጽነት

ነ. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር ህዝብ ሊያገኛቸው በሚችሉ ማሰራጫ መንገዶች[5] አጠቃላይ አተገባበርን የሚመለከቱ ከፕሮቶኮሉ ጋር የሚዛመዱ ወይም ተጽእኖ የሚያሳርፉ ሁሉንም አግባብ የሆኑ እርምጃዎች በአስቸኳይ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ወዲያውኑ፣ ቢዘገይ ወደስራ በሚገቡበት ጊዜ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡ ከአገልግሎት ንግድ የሚገናኙ ወይም ተጽእኖ የሚያሳርፉ የስምምነቱ አባል ሀገራት የፈረሟቸው አለም አቀፍና አካባቢያዊ ስምምነቶችም ይፋ መደረግ አለባቸው፡፡

2. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር ይህ ፕሮቶኮል ወደ ስራ ከመግባቱም አስቀድሞም ሆነ በኋላ የፈረመውን ከአገልግሎት ንግድ ጋር የሚገናኙ ወይም ተጽእኖ የሚያሳርፉ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የገባውን አለም አቀፍና አካባቢያዊ ስምምነቶች ለጽህፈት ቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

3. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር ወዲያውኑ እና ቢያንስ በየአመቱ በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት የአገልግሎት ንግድ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ አዳዲስ ህጎችን ወይም በነባር ህጎች፣ ደንቦች ወይም አስተዳደራዊ መመሪያዎች ላይ የተደረጉ ማንኛውንም ለውጦች ለጽህፈት ቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. ጽህፈት ቤቱ በስምምነቱ አባል ሀገራት የተላኩትን ማሳወቂያዎች ለሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት ወዲያውኑ ማሰራጨት አለበት፡፡

[5] ለምሳሌ በአንዱ የአፍሪካ ህብረት ቋንቋ በጋዜጣ፣ የውይይቶች ኦፊሴላዊ መዝገብ በድህረ ገጽ ወ.ዘ.ተ.

5. Each State Party shall respond promptly to all requests by any other State Party for specific information on any of its measures of general application or international and/or regional agreements within the meaning of paragraph 1. State Parties shall also reply to any question from any other State Party relating to an actual or proposed measure that might substantially affect the operation of this Protocol.
6. Each State Party shall designate the relevant enquiry points to provide State Parties with specific information, upon request, on all such matters related to trade in services as well as those subject to the notification requirement above.

Article 6
Disclosure of Confidential Information

Nothing in this Protocol shall require any State Party to disclose confidential information and data, the disclosure of which would impede law enforcement, or otherwise be contrary to the public interest, or which would prejudice legitimate commercial interests of particular enterprises, public or private.

Article 7
Special and Differential Treatment

In order to ensure increased and beneficial participation in trade in services by all parties, State Parties shall:

(a) provide special consideration to the progressive liberalisation of service sectors commitments and modes of supply which will promote critical sectors of growth, social and sustainable economic development;

(b) take into account the challenges that may be encountered by State Parties and may grant flexibilities such as transitional periods, within the framework of action plans, on a case by case basis, to accommodate special economic situations and development, trade and financial needs in implementing this Protocol for the establishment of an integrated and liberalised single market for trade in services; and

(c) accord special consideration to the provision of technical assistance and capacity-building through continental support programmes.

5. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር በአንቀጽ 1 ትርጉም መሰረት በሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት የሚነሱ አጠቃላይ አተገባበር ያላቸው እርምጃዎች ወይም አለም አቀፍ እና/ ወይም የአካባቢያዊ ስምምነቶችን የሚመለከት የተለየ መረጃ ከማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ለሚቀርብለት ለሁሉም ጥያቄዎች ወዲያውኑ መልስ መስጠት አለበት፡፡ የስምምነቱ አባል ሀገራት በዚህ ፕሮቶኮል አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ የሚያሳድሩ በተግባር ላይ ካሉ ወይም ከታቀዱ እርምጃዎች ጋር በተገናኘ ለሚቀርቡ ማንኛውም ጥያቄዎች መልስ መስጠት አለባቸው፡፡

6. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር ሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት በአገልግሎት ዘርፍና ከፍ ብለው በተጠቀሱ የማሳወቅ ግዴታዎች ላይ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ አስፈላጊውን የመረጃ መስጫ ማዕከል መሰየም አለባቸው፡፡

አንቀጽ 6
ሚስጥራዊ መረጃን ይፋ ስለማድረግ

ይህ ፕሮቶኮል ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ሕግን ማስከበር የሚያሰናክል ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር ተጻራሪ ከሆነ ወይም የመንግስትም ሆነ የግል ኢንተርፕራይዞችን ህጋዊ የንግድ ጥቅም ላይ ያልተገባ አሉታዊ አመለካከት የሚፈጥር ሆኖ ሲያገኘው ሚስጥራዊ መረጃዎችን ይፋ እንዲያደርግ አይጠይቅም፡፡

አንቀጽ 7
ልዩ መስተንግዶ

የሁሉም አገራት የአገልግሎት ንግድ ዘርፍ እየጨመረ የሚሄድና ጠቀሜታ ያለው ተሳትፎ ለማረጋገጥ የስምምነቱ አባል ሀገራት የሚከተሉትን ያከናውናሉ፣

(ሀ) የአገልግሎት ዘርፎችን ግዴታን እና የአቅርቦት ዘዴዎችን በሂደት ነጻ ማድረግን ልዩ ትኩረት በመስጠት የወሳኝ ዘርፎችን ዕድገት፣ የማህበራዊና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ልማትን ከፍ ማድረግ፣

(ለ) የስምምነቱ አባል ሀገራት የሚያጋጥማቸውን ፈተናዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ፕሮቶኮሉን ለመተግበር የተዋሀደና አንድ የአገልግሎት ንግድ ገበያ ለመመስረት እያንዳንዱን እንደየሁኔታው በድርጊት መርሀ ግብር የታቀፈ የሽግግር ጊዜ፣ ልዩ የኢኮኖሚ ሁኔታን ፣ ልማት፣ ንግድና የፋይናንስ ፍላጎት በማስተናገድ ተለማጭ አማራጭ መስጠት መቻል፣ እና

(ሐ) በአህጉራዊ ድጋፍ ፕሮግራም አማካይነት ለቴክኒክ እገዛና ለአቅም ግንባታ ልዩ ትኩረት መስጠት፣

Article 8
Right to Regulate

Each State Party may regulate and introduce new regulations on services and services suppliers within its territory in order to meet national policy objectives, in so far as such regulations do not impair any rights and obligations arising under this Protocol.

Article 9
Domestic Regulation

1. In sectors where specific commitments are undertaken, each State Party shall ensure that all measures of general application affecting trade in services are administered in a reasonable, objective, transparent and impartial manner.
2. Each State Party shall maintain or institute, as soon as practicable, judicial, arbitral or administrative tribunals or procedures which provide, at the request of an affected service supplier, for the prompt review of, and where justified, appropriate remedies for, administrative decisions affecting trade in services. Where such procedures are not independent of the agency entrusted with the administrative decision concerned, the State Party shall ensure that the procedures in fact provide for an objective and impartial review.
3. Where authorisation is required for the supply of a service liberalised under this Protocol, the competent authorities of a State Party shall, within a reasonable period of time after the submission of an application considered complete under domestic laws and regulations, inform the applicant of the decision concerning the application. At the request of the applicant, the competent authorities of the State Party shall provide, without undue delay, information concerning the status of the application.

Article 10
Mutual Recognition

1. For the purposes of the fulfilment, in whole or in part, of its standards or criteria for the authorisation, licensing or certification of services suppliers, and subject to the requirements of paragraph 3 of this Article, a State Party may recognise the education or experience obtained, requirements met, or licenses or certifications granted in another State Party. Such recognition, which may be achieved through harmonisation or otherwise, may be based upon an agreement or arrangement with the State Party concerned or may be accorded autonomously.

አንቀጽ 8
የመቆጣጠር መብት

እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር ከፕሮቶኮሉ የሚመነጩ መብትና ግዴታዎችን እስካልተጻረረ ድረስ በግዛቱ ውስጥ የብሄራዊ ፖሊሲውን ዓላማ ለማሳካት የአገልግሎትና አገልግሎት አቅራቢዎችን መቆጣጠርና አዳዲስ የህግ ቁጥጥር ስርአቶችን ማውጣት ይችላል፡፡

አንቀጽ 9
የሀገር ውስጥ ህግ ቁጥጥር

1. ዝርዝር ግዴታ በተገባባቸው የአገልግሎት ዘርፎች እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር የአገልግሎት ዘርፍ ላይ ተጽእኖ የሚያሳርፉና በአጠቃላይ ተግባራዊ የሚደረጉ እርምጃዎችን ምክንያታዊ በሆነ ፣ እውነታ ላይ በተመሰረተ፣ ግልጽና ከአድሎ በጸዳ መንገድ ስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ አለበት፡ :

2. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር ጉዳት በደረሰበት አገልግሎት አቅራቢ ጠያቂነት የአገልግሎት ንግድን የሚመለከቱ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፍጥነት የሚታዩበት ወይም አስፈላጊነቱ ሲታመንበት አግባብነት ያላቸው መፍትሄዎች የሚሰጡበት የዳኝነት፣የግልግል ወይም አስተዳደራዊ ችሎቶችና ስነስርአቶችን በተቻለ ፍጥነት ማቋቋም አለበት፡፡ የተዘረጋው ሥርአት አስተዳደራዊ ውሳኔ ከሚሰጠው ተቋም ነጻ ሆኖ ያልተቋቋመ ከሆነ የስምምነቱ አባል ሀገር ሂደቱ ከአድሎ የነጻና ትክክለኛ ምርመራ መካሄዱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት ክፍት ለተደረጉ የአገልግሎት ዘርፎች አገልግሎት ለማቅረብ ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በስምምነቱ አባል ሀገር ስልጣን የተሰጠው አካል በሀገር ውስጥ ህግና ደንብ መሰረት ማመልከቻው ተጠናቆ በቀረበ ምክኒያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፡፡ አመልካቹ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ በስምምነቱ አባል ሀገር ስልጣን የተሰጠው አካል ያለምንም ተገቢ ያልሆነ መዘግየት ማመልከቻው የሚገኝበትን ሁኔታ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

አንቀጽ 10
የእርስ በርስ እውቅና

1. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ እንድ የስምምነቱ አባል ሀገር የአገልግሎትና የአገልግሎት አቅራቢዎች ፈቃድ ወይም እውቅና ለመስጠት የሚያስፈልጉ ደረጃዎች ወይም መስፈርቶች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል መሟላታቸውን ለማረጋገጥ፣ በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር የተሰጠን የትምህርት ወይም ልምድ፣ የተሟሉ መመዘኛዎችን ወይም በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር የተሰጡ ፈቃድና ማረጋገጫዎችን እንደራሱ አድርጎ እውቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ እውቅና መስፈርቶችን በማጣጣም ወይም ከሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ጋር በሚደረግ ስምምነት ወይም የተለየ ሁኔታ በማዘጋጀት ወይም በስምምነቱ አባል ሀገር በራስ ተነሳሽነት የሚሰጥ ሊሆን ይችላል፡፡

2. A State Party that is a party to an agreement or arrangement of the type referred to in paragraph 1 of this Article, whether existing or future, shall afford adequate opportunity for other interested State Parties to negotiate their accession to such an agreement or arrangement or to negotiate comparable ones with it. Where a State Party accords recognition autonomously, it shall afford adequate opportunity for any other State Party to demonstrate that education, experience, licenses, or certifications obtained or requirements met in that other State Party's territory should be recognised.
3. A State Party shall not accord recognition in a manner which would constitute a means of discrimination between State Parties in the application of its standards or criteria for the authorisation, licensing or certification of service suppliers, or a disguised restriction on trade in services.
4. Each State Party shall:
   (a) within twelve (12) months from the date on which the Agreement enters into force for it, inform the Secretariat of its existing recognition measures and state whether such measures are based on agreements or arrangements of the type referred to in paragraph 1 of this Article;
   (b) promptly inform the State Parties through the Secretariat as far in advance as possible of the opening of negotiations on an agreement or arrangement of the type referred to in paragraph 1 of this Article in order to provide adequate opportunity to any other State Party to indicate their interest in participating in the negotiations before they enter a substantive phase; and
   (c) promptly inform the States Parties through the Secretariat when it adopts new recognition measures or significantly modifies existing ones and state whether the measures are based on an agreement or arrangement of the type referred to in paragraph 1 of this Article.
5. Wherever appropriate, recognition should be based on AfCFTA agreed criteria by State Parties. In appropriate cases, State Parties shall work in cooperation with relevant intergovernmental and non-governmental organisations towards the establishment and adoption of common continental standards and criteria for recognition and common continental standards for the practice of relevant services trades and professions.

2. የስምምነቱ አባል ሀገር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ነ የተገለጸው ዓይነት ቀደም ሲል የነበረም ሆነ ወደፊት የሚቋቋም ስምምነት ወይም ሥርዓት አካል ከሆነ ለሌሎች ፍላጎት ላላቸው የስምምነቱ አባል ሀገራት ስምምነቱን ወይም ሥርዓቱን ተደራድረው መቀላቀል እንዲችሉ ወይም ከስምምነቱ አባል ሀገር ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ስምምነት ወይም ሥርዓት ለማበጀት እንዲደራደሩ በቂ እድል መሰጠት አለበት፡፡ አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ለሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር እውቅናውን የሰጠው በራሱ ተነሳሽነት እንደሆነ ሌሎች ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገራት በግዛታቸው ውስጥ የተገኙ የትምህርት፣ ልምድ ፈቃድ እውቅና በተመሳሳይ እውቅና እንዲያገኙ ለማሳመን በቂ ዕድል መሰጠት አለበት፡፡

3. የስምምነቱ አባል ሀገር በደረጃዎች ፣በመመዘኛ፣ በፈቃድ አሰጣጥ ትግበራ ወቅት በአባል ሀገራት አገልግሎት አቅራቢዎች መካከል አድሎ በሚፈጥር ወይም ድብቅ በሆነ መልኩ የአገልግሎት ንግድ የሚገድብ እውቅና መስጠት የለበትም፡፡

4. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር፤

   (ሀ) ስምምነቱ ለእርሱ ወደ ትግበራ በገባበት በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ በስራ ላይ ያሉ የእውቅና እርምጃዎችን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ነ በተገለጸው መሰረት በስምምነት ወይም ስርዓት ተበጅቶለት እንደሆነ በመጥቀስ ለጽህፈት ቤቱ ማሳወቅ አለበት፣

   (ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ነ የተገለጸው ዓይነት ስምምነት ወይም በሌላ ስርዓት ድርድር መጀመርን ሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት ወደ ዋና ጉዳዮች ከመገባቱ አስቀድሞ በድርድሩ ፍላጎታቸውን ለማመላከት በቂ ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ በጽህፈት ቤቱ በኩል ለስምምነቱ አባል ሀገራት ወዲያወኑ ቢቻል አስቀድሞ ማሳወቅ፣ እና

   (ሐ) አዲስ የእውቅና እርምጃዎች ስራ ላይ በሚወሉበት ወይም በስራ ላይ ያለውን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሻሽል ሲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ነ መሰረት በስምምነት ወይም በሌላ ስርአት መሆኑን በመጥቀስ በጽህፈት ቤቱ በኩል ለስምምነቱ አባል ሀገራት በፍጥነት ማሳወቅ አለበት፡፡

5. ተገቢ ሆኖ ሲገኝ እውቅናው በአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት መሰረት የስምምነቱ አባል ሀገራት በሚስማሙበት መመዘኛ መሆን አለበት፡፡ ተገቢ በሆኑ ጉዳዮች የስምምነቱ አባል ሀገራት አግባብነት ካላቸው የበይነ መንግስታት እና መንግሰታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር አስፈላጊ ለሆኑ አገልግሎቶችና ሙያዎች ተግባራዊ የሚደረግ አህጉራዊ የጋራ ደረጃዎች እና መመዘኛዎች እና የጋራ አህጉራዊ ደረጃዎች እውቅና ለመመስረትና ለማጽደቅ የሚያስችል ስራ ያከናውናሉ፡፡

Article 11
Monopolies and Exclusive Service Suppliers

1. Each State Party shall ensure that any monopoly supplier of a service in its territory does not, in the supply of the monopoly service in the relevant market, act in a manner inconsistent with that State Party's obligations and specific commitments under this Protocol.
2. Where a State Party's monopoly supplier competes, either directly or through an affiliated company, in the supply of a service outside the scope of its monopoly rights and which is subject to that State Party's specific commitments, the State Party shall ensure that such a supplier does not abuse its monopoly position to act in its territory in a manner inconsistent with such commitments.
3. A State Party which has a reason to believe that a monopoly supplier of a service of any other State Party is acting in a manner inconsistent with paragraphs 1 and 2 of this Article, may request the State Party establishing, maintaining or authorising such supplier to provide specific information concerning the relevant operations.
4. If, after the date of entry into force of this Protocol, a State Party grants monopoly rights regarding the supply of a service covered by its specific commitments, that State Party shall notify the Secretariat no later than three (3) months before the intended implementation of the grant of monopoly rights and the provisions concerning modification of specific commitments will apply.
5. The provisions of this Article shall also apply to cases of exclusive service suppliers where a State Party, formally or in effect:
    (a) authorises or establishes a small number of service suppliers; and
    (b) substantially prevents competition among those suppliers in its territory.

Article 12
Anti-competitive Business Practices

1. State Parties recognise that certain business practices of service suppliers, other than those concerning monopolies and exclusive service suppliers, may restrain competition and thereby restrict trade in services.

አንቀጽ 11
ብቸኛ እና በሞኖፖል አገልግሎት አቅራቢዎች

1. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር በግዛቱ ውስጥ ያለ ማንኛውም በሞኖፖል የአገልግሎት አቅራቢ አገልግሎቱን በአንድ የገበያው ክልል ውስጥ በሚያቀርብበት ወቅት የስምምነቱ አባል ሀገር በፕሮቶኮሉ ከገባቸው ግዴታዎችና ዝርዝር ቃል ኪዳኖች ጋር የማይጣጣም ድርጊት ያለመፈጸሙን ማረጋገጥ አለበት ::

2. የስምምነቱ አባል ሀገር የሞኖፖል አገልግሎት አቅራቢ በቀጥታ ወይም ግንኙነት ባለው ኩባንያ በኩል በብቸኝነት ከያዘው አገልግሎት ወሰን ውጪ የሚወዳደር ከሆነና ዝርዝር ቃልኪዳን ግዴታ የገባበት ከሆነ የስምምነቱ አባል ሀገር የሞኖፖል አቅራቢነቱን አቋም ባልተገባ ሁኔታ በመጠቀም በግዛቱ ውስጥ ከዝርዝር ቃል ኪዳኑ ጋር የማይጣጣም ድርጊት ያለመፈጸሙን ማረጋገጥ አለበት ::

3. አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ሌላ ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር የሞኖፖል አገልግሎት አቅራቢ ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ነ እና 2 ጋር የማይጣጣም ድርጊት መፈጸሙን ለማመን ምክንያት ካለው የሞኖፖል አቅራቢውን ያቋቋመውን ወይም ፈቃድ የሰጠውን የስምምነቱ አባል ሀገር ስለተካሄደው ግንኙነት ያለው እንቅስቃሴ ማንኛውንም የተለየ መረጃ እንዲሰጥ ሊጠይቅ ይችላል::

4. ይህ ፕሮቶኮል ወደስራ ከገባ በኋላ አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር በገባው ዝርዝር ቃል ኪዳን ውስጥ በተካተተ አገልግሎት ላይ የሞኖፖል አገልግሎት አቅራቢነት መብት የሰጠ እንደሆነ ይኸው የስምምነቱ አባል ሀገር የሰጠው የሞኖፖል አቅራቢነት መብት ወደተግባር ለማስገባት ከታቀደበት ከሶስት ወራት በፊት ባለ ጊዜ ውስጥ ለጽህፈት ቤቱ ማሳወቅ አለበት:: ይህ በሆነ ጊዜ የዝርዝር ግዴታ ቃል ኪዳንን ስለማሻሻል የሚደነግጉት አንቀጾች ተፈጻሚ ይሆናሉ::

5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የስምምነቱ አንድ አባል ሀገር በይፋ ወይም በተግባር ለውስን አገልግሎት አቅራቢዎች የተሰጡ፣

   (ሀ) በቁጥር አነስተኛ የሆኑ አገልግሎት አቅራቢዎችን ሲያቋቁም ወይም ሲፈቅድ፣እና

   (ለ) በግዛቱ ውስጥ በአቅራቢዎቹ መካከል ውድድር እንዳይኖር በእብዛኛው በሚገድብ፣ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

አንቀጽ 12
ጸረ ውድድር የቢዝነስ አሰራሮች

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት ከሞኖፖልና ብቸኛ አገልግሎት አቅራቢዎች ውጭ ያሉ የተወሰኑ የቢዝነስ አሰራሮች ውድድርን በማቀብ የአገልግሎት ንግድ ሊገድቡ እንደሚችሉ እውቅና ሰጥተዋል::

2. Each State Party shall, at the request of any other State Party, enter into consultations with a view to eliminating practices referred to in paragraph 1 of this Article. The State Party addressed shall respond to such a request and shall cooperate through the supply of publicly available non-confidential information of relevance to the matter in question. The State Party addressed shall also provide other information available to the requesting State Party, subject to its domestic law and to the conclusion of a satisfactory agreement concerning the safeguarding of its confidentiality by the requesting State Party.

Article 13
Payments and Transfers

1. Except under the circumstances envisaged in Article 14 of this Protocol, a State Party shall not apply restrictions on international transfers and payments for current transactions relating to its specific commitments.
2. Nothing in this Protocol shall affect the rights and obligations of the members of the International Monetary Fund under the Articles of Agreement of the Fund, including the use of exchange actions which are in conformity with the Articles of Agreement, provided that a State Party shall not impose restrictions on any capital transactions inconsistently with its specific commitments regarding such transactions, except as provided under Article 14 of this Protocol, or at the request of the Fund.

Article 14
Restrictions to Safeguard the Balance of Payments

1. In the event of serious balance of payments and external financial difficulties or threat thereof, a State Party may adopt or maintain restrictions on trade in services on which it has undertaken specific commitments, including on payments or transfers for transactions related to such commitments. It is recognised that particular pressures on the balance of payments of a State Party in the process of economic development or economic transition may necessitate the use of restrictions to ensure, inter alia, the maintenance of a level of financial reserves adequate for the implementation of its programme of economic development or economic transition.
2. The restrictions referred to in paragraph 1 of this Article shall:
   (a) not discriminate among State Parties;
   (b) be consistent with the Articles of Agreement of the International Monetary Fund;

2. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር በሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ጥያቄ መሰረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተገለጹትን አሰራሮች ለማስወገድ ያለሙ ምክክሮች ላይ የመግባት ግዴታ አለበት፡፡ ጥያቄው የቀረበለት የስምምነቱ አባል ሀገር ምላሹን መስጠትና ከጥያቄው ጋር አግባብነት ያላቸው ለህዝብ ይፋ የተደረጉ ሚስጥራዊ ያልሆኑ መረጃዎችን በማቅረብ መተባበር አለበት፡፡ በተጨማሪም ጥያቄው የቀረበለት የስምምነቱ አባል ሀገር የሀገር ውስጥ ህግን በመንተራስና ከጠያቂው ሀገር ጋር ሚስጥራዊነታቸው እንደሚጠበቅ በሚደረስ አጥጋቢ ስምምነት ሌሎች መረጃዎች መስጠት አለበት፡፡

አንቀጽ 13
ስለ ክፍያዎች እና ዝውውሮች

1. በዚህ ፕሮቶኮል በአንቀጽ 14 ከተገለጸው ሁኔታ በስተቀር የስምምነቱ አባል ሀገር ከገባው ዝርዝር ቃል ኪዳን ጋር በተገናኘ በአለም አቀፍ ዝውውሮች እና በተንቀሳቃሽ የገንዘብ ክፍያዎች ላይ ከልከላ ማድረግ አይችልም፡፡

2. ይህ ፕሮቶኮል የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባላት ከስምምነቱ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ የገንዘብ ምንዛሬ እርምጃዎች መውሰድን ጨምሮ በድርጅቱ የስምምነት አንቀፆች መሰረት ባላቸው መብቶችና እና ግዴታዎች ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ አይኖርም። ይሁንና አንድ የስምምነቱ አባል በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 14 በተጠቀሰው መሰረት ወይም በድርጅቱ ጥያቄ ካልሆነ በስተቀር ከገባው የተናጠል ግዴታ ጋር የማይጣጣም ማንኛውንም የካፒታል እንቅስቃሴዎች ላይ ገደብ መጣል አይችልም።

አንቀጽ 14
የክፍያ ሚዛንን ለመጠበቅ የሚደረጉ ክልከላዎች

1. አሳሳቢ የክፍያ ሚዛን እና የውጭ ፋይናንስ ችግሮች ወይም ስጋት በሚኖርበት ወቅት የስምምነቱ አባል ሀገራት የተናጠል ቃል ኪዳን በገቡባቸው የአገልግሎት ንግድ ዘርፎች ክፍያዎችንና የገንዘብ ዝውውሮችን ጨምሮ ክልከላዎችን ስራ ላይ ማዋል ወይም የነበረውን ማስቀጠል ይችላሉ፡፡ በኢኮኖሚ ልማት ሂደት ወይም በሽግግር ኢኮኖሚ ውስጥ ያለ የስምምነቱ አባል ሀገር የክፍያ ሚዛን የተለየ ጫና የተነሳ ለኢኮኖሚ ልማት ወይም የኢኮኖሚ ሽግግር ፕሮግራሙን ለማስፈጸም ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ በቂ የሆነ የፋይናንስ ክምችት እንዲይዝ የሚያስችል ክልከላዎችን መጠቀም ሊያስፈልገው እንደሚችል እውቅና ተሰጥቷል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሱት ክልከላዎች፣

   (ሀ) በስምምነቱ አባል ሀገራት መካከል አድሎ ማድረግ የለባቸውም፣

   (ለ) ከአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የስምምነት አንቀጾች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፣

(c) avoid unnecessary damage to the commercial, economic and financial interests of any other State Party;

(d) not exceed those necessary to deal with the circumstances described in paragraph 1 of this Article; and

(e) be temporary and be phased out progressively as the situation specified in paragraph 1 of this Article improves.

3. In determining the incidence of such restrictions, State Parties may give priority to the supply of services which are more essential to their economic or development programmes. However, such restrictions shall not be adopted or maintained for the purpose of protecting a particular service sector.

4. Any restrictions adopted or maintained under paragraph 1 of this Article, or any changes therein, shall be promptly notified to the Secretariat.

5. State Parties applying the provisions of this Article shall consult promptly within the Committee on Trade in Services on restrictions adopted under this Article.

6. The Committee on Trade in Services shall establish procedures for periodic consultations with the objective of enabling such recommendations to be made to the State Party concerned as it may deem appropriate.

7. Such consultations shall assess the balance-of-payment situation of the State Party concerned and the restrictions adopted or maintained under this Article, taking into account, inter alia, such factors as:

(a) the nature and extent of the balance-of-payments and the external financial difficulties;

(b) the external economic and trading environment of the consulting State Party; and

(c) alternative corrective measures which may be available.

8. The consultations shall address the compliance of any restrictions with paragraph 2 of this Article, in particular the progressive phase-out of restrictions in accordance with paragraph 2(e) of this Article.

9. In such consultations, all findings of statistical and other facts presented by the International Monetary Fund relating to foreign exchange, monetary reserves and balance of payments, shall be accepted and conclusions shall be based on the assessment by the Fund of the balance-of-payments and the external financial situation of the consulting State Party.

(ሐ) በሌላ ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር የንግድ፣ የኢኮኖሚና የፋይናንስ ፍላጎት ላይ ተገቢ ያልሆነ ጉዳት የሚያስወግዱ መሆን አለባቸው፣

(መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፣ የተገለጹትን ሁኔቶች ለማረቅ አስፈላጊ ከሆኑት በላይ መሆን አይገባቸውም፣ እና

(ሠ) ጊዚያዊና በንኡስ አንቀጽ ፣ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሻሻሉ በሂደት እየቀረ የሚሄድ መሆን አለበት፡፡

3. የክልከላዎችን ተከሳችነት ለመወሰን የስምምነቱ አባል ሀገራት ለኢኮኖሚያቸው ወይም ለልማት ፕሮግራማቸው ይበልጥ ጠቃሚ ለሆኑ የአገልግሎት አቅርቦቶች ቅድሚያ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ክልከላዎቹ የተለየ የአገልግሎት ዘርፍን ጥበቃ ለማድረግ አላማ ስራ ላይ መዋል ወይም መቀጠል የለባቸውም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፣ ማንኛውም ስራ ላይ የዋሉ የቀጠሉ ክልከላዎች ወይም ማናቸውም በዚህ ረገድ የሚደረጉ ለውጦች ለጽህፈት ቤቱ ወዲያውኑ እንዲታወቁ መደረግ አለባቸው፡፡

5. የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ የስምምነቱ አባል ሀገራት በዚህ አንቀጽ ስራ ላይ ያዋሉትን ክልከላዎች በአገልግሎት ንግድ ኮሚቴ ውስጥ ወዲያውኑ ምክክር ማድረግ አለባቸው፡፡

6. የአገልግሎት ንግድ ኮሚቴ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር ምክረ ሀሳብ ማቅረብን ዓላማ ያደረገ በየጊዜው ምክክር ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት መመስረት አለበት፡፡

7. ይህ ምክክር የሚመለከተውን የስምምነቱ አባል አገር የክፍያ ሚዛን ሁኔታንና በዚህ አንቀጽ ስራ ላይ የዋሉ ወይም የቀጠሉ ክልከላዎችን ይገመግማል፡፡ ግምገማው ከሌሎች በተጨማሪ፣

(ሀ) የክፍያ ሚዛንና የውጭ የፋይናንስ ተግዳሮቶች ባህርይና ደረጃን፣

(ለ) ምክክር የሚያደርገው የስምምነቱ አባል ሀገር የውጭ ኢኮኖሚና የንግድ ከባቢ ሁኔታን፣ እና

(ሐ) ሊኖሩ የሚችሉ አማራጭ የእርምት እርምጃዎችን

ያካትታል፡፡

8. ምክክሮቹ ማንኛውም ክልከላዎች ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ጋር የተጣጣመ መሆኑን በተለይም ክልከላዎቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) መሰረት በሂደት እየቀሩ መሄዳቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

9. በምክክሮቹ የውጭ ምንዛሪ፣ የገንዘብ ክምችት እና የክፍያ ሚዛንን አስመልክቶ በአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሚቀርቡ ሁሉም አሀዛዊ እና ሌሎች ግኝቶች ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ መደምደሚያዎችም በምክክር አድራጊው የስምምነቱ አባል ሀገር ላይ በድርጅቱ የተከናወነ የክፍያ ሚዛን እና የውጭ የፋይናንስ ሁኔታ ግምገማን መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

10. If a State Party which is not a member of the International Monetary Fund wishes to apply the provisions of this Article, the Council of Ministers shall establish a review procedure and any other procedures necessary.

Article 15
General Exceptions

Subject to the requirement that such measures are not applied in a manner which would constitute a means of arbitrary or unjustifiable discrimination between State Parties where like conditions prevail, or a disguised restriction on trade in services, nothing in this Protocol shall be construed to prevent the adoption or enforcement by any State Party of measures:

(a) necessary to protect public morals or to maintain public order[6];

(b) necessary to protect human, animal or plant life or health;

(c) necessary to secure compliance with laws or regulations which are not inconsistent with the provisions of this Protocol including those relating to:

  i. the prevention of deceptive and fraudulent practices or to deal with the effects of a default on services contracts;

  ii. the protection of the privacy of individuals in relation to the processing and dissemination of personal data and the protection of confidentiality of individual records and accounts;

  iii. safety;

(d) inconsistent with National Treatment, provided that the difference in treatment is aimed at ensuring the equitable or effective imposition or collection of direct taxes in respect of services or service suppliers of other States Parties; and[7]

---

[6] *The public order exception may be invoked only where a genuine and sufficiently serious threat is posed to one of the fundamental interests of society.*

[7] *Measures that are aimed at ensuring the equitable or effective imposition or collection of direct taxes include measures taken by a State Party under its taxation system which:*

a. Apply to non-resident service suppliers in recognition of the fact that the tax obligation of non-residents is determined with respect to taxable items sourced or located in the State Party's territory; or

b. Apply to non-residents in order to ensure the imposition or collection of taxes in the State Party's territory; or

c. Apply to non-residents or residents in order to prevent the avoidance or evasion of taxes, including compliance measures; or

d. Apply to consumers of services supplied in or from the territory of another State Party in order to ensure the imposition or collection of taxes on such consumers derived from sources in the State Party's territory; or

e. Distinguish service suppliers subject to tax on worldwide taxable items from other service suppliers, in recognition of the difference in the nature of the tax base between them; or

f. Determine, allocate or apportion income, profit, gain, loss, deduction or credit of resident persons or branches, or between related persons or branches of the same person, in order to safeguard the State Party's tax base.

Tax terms or concepts in paragraph (d) of Article 15 and in this footnote are determined according to tax definitions and concepts, or equivalent or similar definitions and concepts, under the domestic law of the State Party taking the measure.

10. አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አባል ካልሆነና የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎችን መተግበር ከፈለገ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የግምገማ ስርአት ወይም ሌላ ማንኛውንም አስፈላጊ ስርአት ይመሰርታል፡፡

አንቀጽ 15
ጠቅላላ ልዩ ሁኔታዎች

በስምምነቱ አባል ሀገራት መካከል ተመሳሳይ ሁኔታዎች እያሉ በዘፈቀደ ወይም ተገቢነት በሌለው አድልዎ ወይም በአገልግሎት ንግድ ላይ ድብቅ ክልከላ በሚፈጥር መንገድ እስካልተገበሩ ድረስ ፣ የትኛውም የዚህ ፕሮቶኮል ክፍል ማንኛውንም የስምምነቱ አባል ሀገር የሚከተሉትን እርምጃዎች ከመወሰድ ወይም ከማስፈጸም የሚከለክለው ተደርጎ መተርጎም የለበትም፤

(ሀ) የሕዝብ ሞራል ለመጠበቅ ወይም የህዝብን ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣[6]

(ለ) የሰዎችን የእንስሳትና የእጽዋትን ህይወትና ጤና ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆነ ሲገኝ፣

(ሐ) ከዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎች ጋር የማይጣረሱ ህጎች ወይም ደንቦችን ማክበር አስፈላጊ ሲሆንና ሌሎች መሰል ሁኔታዎችን ጨምሮ፤

i. አሳሳች እና የማጭበርበር ተግባራት ለመከላከል ወይም የአገልግሎት ውል ያለመፈጸም ተጽእኖን ለመቆጣጠር፣

ii. የግለሰቦችን የግል መረጃን ከማደራጀትና ከማሰራጨት ጋር በተገናኘ ግላዊነትን ለመጠበቅ እና የግል ፋይል እና መግለጫ ሚስጢራዊነትን ለመጠበቅ፣ እና

iii. ደህንነትን ለማረጋገጥ፤

(መ) የሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር አገልግሎት ወይም አገልግሎት አቅራቢዎች ላይ ቀጥተኛ ታክሶችን ፍትሃዊ ወይም ውጤታማ በሆነ መልኩ መጣል ወይም መሰብሰብን ለማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ የሀገር ውስጥና የውጭ አገልግሎትና አገልግሎት አቅራቢዎችን ያለ ልዩነት ከማስተናገድ ጋር የማይጣጣም ፣ እና[7]

---

[6] የህዝብ ሰላምና መረጋጋት ያለማካተትን መጠቀም የሚቻለው እውነተኛ እና በቂ የሆነ አሳሳቢ ስጋት በህዝብ መሰረታዊ ፍላጎት ላይ ሲጋረጥ ነው፡፡

[7] ቀጥተኛ ታክሶችን ፍትሀዊ ወይም ውጤታማ በሆነ መንገድ መጣል ወይም ማሰባሰብ ያለሙ እርምጃዎች በአባል ሀገሩ የታክስ ስርዓት መሰረት የሚወሰዱትን እርምጃዎች ጨምሮ የሚከተሉትን ያካትታል፣

(ሀ) ታክስ የሚጣልባቸው ጉዳዮች የሚወሰኑት ምንጫቸው ወይም የሚገኙበት ቦታ በስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት ውስጥ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነዋሪ ባልሆኑ የአገልግሎት አቅራቢዎች ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ የታክስ ግዴታዎች፣

(ለ) በስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት ውስጥ በስምምነቱ አባል ሀገር ነዋሪ ባልሆኑ ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ ታክሶች መጣላቸውን ወይም መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ፣ ወይም

(ሐ) በስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት ውስጥ ነዋሪ በሆኑ ወይም ባልሆኑ ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ የማስፈጸሚያ እርምጃዎችን ጨምሮ ታክስ ያለመክፈልን ወይም ታክስ ስወራን ለመግታት፣

(መ) በሌላ ወይም ከሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት የሚቀርቡ አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ ከስምምነቱ አባል ሀገር ግዛት የሚመነጩ ታክሶች መጣላቸውን ወይም መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ፣ወይም

(ሠ) በአለም አቀፍ ደረጃ ታክስ የሚጣልባቸው አገልግሎት አቅራቢዎችን ከሌሎች አገልግሎት አቅራቢዎች በመለየት በመካከላቸው ያለውን የታክስ መሰረትና ባህርይ ልዩነት አውቅና ለመስጠት፣ ወይም

(ረ) የስምምነቱ አባል ሀገርን የታክስ መሰረት ለመጠበቅ በነዋሪ ግለሰቦች ወይም ቅርንጫፎች ወይም ግንኙነት ባላቸው ግለሰቦች ወይም የተመሳሳይ ሰዎች ቅርንጫፎችን የገቢ ድርሻ ፣ ትርፍ፣ ኪሳራ፣ ቅናሽ ወይም እዳ ለመወሰን፣ ለመመደብ ወይም ለማከፋፈል፡፡

በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (መ) እና በዚህ የግርጌ ማስታወሻ የተጠቀሱት የታክስ ቃላት ወይም ጽንሰ ሀሳቦች እርምጃውን በሚወስደው የስምምነቱ አባል ሀገር የሀገር ውስጥ ህግ በታክስ ትርጉምና ጽንሰ ሀሳብ ወይም አቻ ወይም ተመሳሳይ ትርጉም እና ጽንሰ ሀሳቦች መሰረት ይወሰናል፡፡

(e) inconsistent with the Most Favoured Nation obligation provided that the difference in treatment is the result of an agreement on avoidance of double taxation or provisions on the avoidance of double taxation in any other international agreement or arrangement by which the State Party is bound.

Article 16
Security Exceptions

1. Nothing in this Protocol shall be construed:
   (a) to require any State Party to furnish any information, the disclosure of which it considers contrary to its essential security interests; or
   (b) to prevent any State Party from taking any action which it considers necessary for the protection of its essential security interests:
      i. relating to the supply of services as carried out directly or indirectly for the purpose of provisioning a military establishment;
      ii. relating to fissionable and fusionable materials or the materials from which they are derived; and
      iii. taken in time of war or other emergency in international relations; or
   (c) to prevent any State Party from taking any action in pursuance of its obligations under the United Nations Charter for the maintenance of international peace and security.
2. The Secretariat shall be informed, to the fullest extent possible, of measures taken under paragraphs 1(b) and 1(c) of this Article, and of their termination.

(ሠ) ተደጋጋሚ ታክሶችን ለማስወገድ በተደረሰ ስምምነት ወይም ተደጋጋሚ ታክሶችን ለማስወገድ በማንኛውም አለም አቀፍ ስምምነት ወይም አሰራር የስምምነቱ አባል ሀገር ተገዢ እስከሆነ ድረስ የውጭ አገልግሎትና አገልግሎት አቅራቢዎችን ያለ ልዩነት ማስተናገድ ጋር የማይጣጣም ፣

አንቀጽ 16
የደህንነት ልዩ ሁኔታዎች

1. በዚህ ፕሮቶኮል የተደነገገው ቢኖርም፤

   (ሀ) ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ይፋ መደረጋቸው ሀገራዊ ደህንነቱን አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ ብሎ የሚያምነባቸውን መረጃዎችን እንዲያቀርብ አይገደድም፣

   (ለ) ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር የደህንነት ፍላጎቱን ለማስጠበቅ አስፈላጊ የሆነና በሌሎች የስምምነቱ አባል ሀገራት ሊወሰዱ የሚችሉ ዕርምጃዎችን ለመከላከል፤

      ፩. በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከወታደራዊ ማቋቋም መሰናዶ ጋር የተገናኘ የአገልግሎት አቅርቦት፣

      ፪. ከኑክሊየር ሀይል የሚያመነጩ እቃዎች ወይም ከእነዚህ ከመነጩ እቃዎች የተገናኘ፣ እና

      ፫. በጦርነት ጊዜ ወይም ሌሎች ከዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ጋር በተገናኘ የሚወሰዱ አስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች፣

   መውሰድ አይከለክልም::

   (ሐ) ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር በተባበሩት መንግስታት ቻርተር በገባው ግዴታ መሰረት የአለም አቀፍ ሰላምና ደህንነትና ለማስጠበቅ ማንኛውንም ድርጊት መፈጸምን አይከለክልም::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) እና (ሐ) በሚመለከት የተወሰዱ እርምጃዎችንና የሚያበቁበትን ጊዜ ጽህፈት ቤቱ በተቻለ መጠን ሙሉ በሙሉ እንዲያውቀው መደረግ አለበት::

Article 17
Subsidies

1. Nothing in this Protocol shall be construed to prevent State Parties from using subsidies in relation to their development programmes.
2. State Parties shall decide on mechanisms for information exchange and review of all subsidies related to trade in services that State Parties provide to their domestic service suppliers.
3. Any State Party which considers that it is adversely affected by a subsidy of another State Party may request consultations with that State Party on such matters. Such requests shall be accorded sympathetic consideration.

PART V
PROGRESSIVE LIBERALISATION

Article 18
Progressive Liberalisation

1. State Parties shall undertake successive rounds of negotiations based on the principle of progressive liberalisation accompanied by the development of regulatory cooperation, and sectoral disciplines, taking into account the objectives of the 1991 Abuja Treaty that aim to strengthen integration at the regional and continental levels in all fields of trade, and in line with the general principle of progressivity towards achievement of the ultimate goal of the African Economic Community.
2. State Parties shall negotiate sector specific obligations through the development of regulatory frameworks for each of the sectors, as necessary, taking account of the best practices and acquis from the RECs, as well as the negotiated agreement on sectors for regulatory cooperation. State Parties agree that negotiations for continuing the process shall commence following the establishment of the AfCFTA, based on the work programme to be agreed by the Committee on Trade in Services.
3. The liberalisation process shall focus on the progressive elimination of the adverse effects of measures on trade in services as a means of providing effective market access with a view to boosting intra-African trade in services.

አንቀጽ 17
ድጎማዎች

1. ይህ ፕሮቶኮል የስምምነቱ አባል ሀገራት ለልማት ፕሮግራማቸው ድጎማን መጠቀም የሚከለክል ሆኖ መተርጎም የለበትም፡፡

2. የስምምነቱ አባል ሀገራት ከአገልግሎት ንግድ ጋር የተገናኙ ለሀገር ውስጥ አገልግሎት አቅራቢዎች የሚሰጧቸው ሁሉንም ድጎማዎች የመረጃ መለዋወጫ እና ግምገማ ዘዴዎችን ይወስናሉ፡፡

3. ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር በሌላ ሀገር ድጎማ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ካመነ ከጉዳት አድራሹ የስምምነቱ አባል ሀገር ጋር ምክክር ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ጥያቄው በበጎ ጎኑ ታይቶ ተገቢ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል፡፡

ክፍል V
ደረጃ በደረጃ ነጻ ማድረግ

አንቀጽ 18
ደረጃ በደረጃ ነጻ ማድረግ

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት የአገልግሎት ዘርፍን ደረጃ በደረጃ ነጻ ማድረግ መርህ መሰረት የቁጥጥር ትብብር በማዘጋጀትና እና የዘርፍ ስነ ስርአት ጋር በማቀናጀት በሁሉም የንግድ ዘርፎች በአካባቢያዊና በአህጉር ውህደትን ለማጠናከር ያለመውን የ1991ዓ.ምቱን የአቡጃ ስምምነት አላማዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት እና በሂደት የአፍሪካን የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመጨረሻ ግብ የማሳካት አጠቃላይ መርህን በመንተራስ ተከታታይ ዙር ድርድሮችን ያካሂዳሉ፡፡

2. የስምምነቱ አባል ሀገራት በእያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ የህግ ማዕቀፍን በማዘጋጀት፣ እንደአስፈላጊነቱ ምርጥ ተሞክሮዎችን እና የአካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ ትብብሮች የደረሱበትን መነሻ ማድረግ እና በተጨማሪም በዘርፎች ድርድር የተደረገባቸውን የቁጥጥር ትብብሮች ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ከግምት ውስጥ በማስገባት በእያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ የተናጠል ግዴታዎችን መደራደር አለባቸው፡፡ የስምምነቱ አባል ሀገራት የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና ከተቋቋመ በኋላ በአገልግሎት ንግድ ኮሚቴ ስምምነት በተደረሰበት የሥራ ፕሮግራም መሰረት የድርድሮቹን ሂደት ለማስቀጠል ተስማምተዋል፡፡

3. የአገልግሎት ንግድን ነጻ የማድረግ ስርአት በአገልግሎት ንግድ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥሩ እርምጃዎች ደረጃ በደረጃ ማስወገድን የገበያ ዕድል መፍጠሪያ መንገድ አድርጎ በመጠቀም በአፍሪካ ሀገራት መካከል ውጤታማ የሆነ የአገልግሎት ንግድን ማሳደግ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

4. The list of Priority Sectors and the Modalities on Trade in Services shall be annexed to this Protocol and shall form an integral part hereof.
5. The Transitional Implementation Work Programme developed by Member States shall guide the finalisation of outstanding Phase I negotiations on this Protocol, before the entry into force of the Agreement.

Article 19
Market Access

1. With respect to market access through the modes of supply identified in Article 1(p) of this Protocol, each State Party shall accord services and service suppliers of any other State Party treatment no less favourable than that provided for under the terms, limitations and conditions agreed and specified in its Schedule.[8]
2. In sectors where market-access commitments are undertaken, the measures which a State Party shall not maintain or adopt either on the basis of a regional subdivision or on the basis of its entire territory, unless otherwise specified in its Schedule, are defined as:
    (a) limitations on the number of service suppliers whether in the form of numerical quotas, monopolies, exclusive service suppliers or the requirements of an economic needs test;
    (b) limitations on the total value of service transactions or assets in the form of numerical quotas or the requirement of an economic needs test;
    (c) limitations on the total number of service operations or on the total quantity of service output expressed in terms of designated numerical units in the form of quotas or the requirement of an economic needs test;[9]
    (d) limitations on the total number of natural persons that may be employed in a particular service sector or that a service supplier may employ and who are necessary for, and directly related to, the supply of a specific service in the form of numerical quotas or the requirement of an economic needs test;

[8] *If a State Party undertakes a market-access commitment in relation to the supply of a service through the mode of supply defined in Article 1(p) and if the cross-border movement of capital is an essential part of the service itself, that State Party is thereby committed to allow such movement of capital. If a State Party undertakes a market-access commitment in relation to the supply of a service through the mode of supply referred to in Article 1(p) (iii), it is thereby committed to allow related transfers of capital into its territory.*

[9] *Article 1(g) (iii) does not cover measures of a State Party which limit inputs for the supply of services.*

4. ቅድሚያ የተሰጣቸው የአገልግሎት ዘርፎችና የድርድር አካሄድ የዚህ ፕሮቶኮል አባሪ እና የፕሮቶኮሉ አካል መደረግ ይኖርበታል፡፡

5. በአባል ሀገራት የተዘጋጀው የመሸጋገሪያ ትግበራ የስራ ፕሮግራም በዚህ ፕሮቶኮል ያልተጠናቀቁ የምዕራፍ ፣ ድርድሮችን ስምምነቱ ወደሥራ ከመግባቱ አስቀድሞ ለማጠናቀቅ እንደ መመሪያ ያገለግላል፡፡

አንቀጽ 19
የገበያ ዕድል

1. በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ ፣(አ) በተለዩት የአገልግሎት አቅርቦት መሰረት የሚሰጡ የገበያ እድልን በተመለከተ ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር በገባው ግዴታ በተቀመጠው የቃል ኪዳን ሰንጠረዥ ገደቦች እና ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት የሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር አገልግሎትና አገልግሎት አቅራቢዎችን ከራሱ ባላነሰ ሁኔታ ማስተናገድ አለበት፡፡[8]

2. የገበያ እድል ግዴታዎች በተገባባቸው የአገልግሎት ዘርፎች የስምምነቱ አባል ሀገር በግዛቱም ሆነ በውስጡ በሚገኙ ከልሎች በቃል ኪዳን ሰንጠረዡ በግልጽ እስካላሰፈረ ድረስ ለማስቀጠል ወይም ስራ ላይ ለማዋል መውሰድ የማይችላቸው እርምጃዎች፤

    (ሀ) በኮታ፣ በሞኖፖል አቅራቢነት፣ በብቸኛ አገልግሎት አቅራቢዎች ወይም የኢኮኖሚ ፍላጎት መመዘኛ መልኩ የአገልግሎት አቅራቢዎችን ቁጥር መወሰን፣

    (ለ) በኮታ ወይም የኢኮኖሚ ፍላጎት መመዘኛ መልኩ የአገልግሎቱን እንቅስቃሴ አጠቃላይ መጠን ወይም ሀብት መወሰን፣

    (ሐ) በአጠቃላይ የአገልግሎት እንቅስቃሴ ወይም ውጤት በአህዝ ሆኖ በኮታ የተገለጸ ወይም የኢኮኖሚ ፍላጎት መመዘኛ መሰረት መወሰን፤[9]

    (መ) በተለየ የአገልግሎት ዘርፍ የሚቀጠሩ ሰዎችን ጠቅላላ ቁጥር ወይም አገልግሎት አቅራቢው አገልግሎቱን ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑና በቀጥታ የተገናኙ በመሆናቸው የሚቀጥራቸውን ሰዎች ቁጥር በኮታ ወይም የኢኮኖሚ ፍላጎት መመዘኛ መሰረት መወሰን፣

[8] አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር በስምምነቱ አንቀጽ ፣(አ) የአቅርቦት ዘዴ ትርጉም መሰረት የገበያ ዕድል ለመስጠት ግዴታ ከገባ እና የካፒታል እንቅስቃሴ ለአገልግሎቱ ፍጹም አስፈላጊ ክፍል ከሆነ የስምምነቱ አባል ሀገር የካፒታል ዝውውሩን ለመፍቀድ ግዴታ ገብቷል፡፡ አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር በአንቀጽ ፣(አ) ፫ በተገለጸው መሰረት የገበያ እድል ለመስጠት ግዴታ ውስጥ ከገባ ተዛማጅ ካፒታል ወደግዛቱ እንዲዘዋወር ለመፍቀድ ግዴታ ገብቷል፡፡

[9] አንቀጽ ፣(ሰ)(iii) በአባል ሀገራት የሚወሰዱ የአገልግሎት አቅርቦት ግብአት ውሱንነት እርምጃዎችን አያካትትም፡፡

(e) measures which restrict or require specific types of legal entity or joint venture through which a service supplier may supply a service; and

(f) limitations on the participation of foreign capital in terms of maximum percentage limit on foreign shareholding or the total value of individual or aggregate foreign investment.

Article 20
National Treatment

1. In all sectors inscribed in the schedule, and subject to any conditions and qualifications set out therein, each State Party shall accord to services and service suppliers of any other State Party treatment no less favourable than that it accords to its own like services and service suppliers, subject to the conditions and qualifications agreed and specified in its Schedule of Specific Commitments.
2. A State Party may meet the requirement of paragraph 1 of this Article, by according to services and service suppliers of any other State Party either formally identical treatment or formally different treatment to that it accords to its own like services and service suppliers.
3. Formally identical or formally different treatment shall be considered to be less favourable if it modifies the conditions of competition in favour of services or service suppliers of the State Party compared to like services or service suppliers of any other State Party.

Article 21
Additional Commitments

The State Parties may negotiate commitments with respect to measures affecting trade in services not subject to scheduling under Articles 19 or 20 of this Protocol, including but not limited to those regarding qualification, standards or licensing matters. Such commitments shall be inscribed in a State Party's Schedule of Specific Commitments.

Article 22
Schedules of Specific Commitments

1. Each State Party shall set out in a schedule, the specific commitments that it undertakes under Articles 19, 20 and 21 of this Protocol.
2. With respect to sectors where such commitments are undertaken, each Schedule of Specific Commitments shall specify:

(ሠ) አገልግሎቱን የተወሰነ ህጋዊ ሰውነት ባላቸው ተቋማት ወይም አገልግሎት አቅራቢው ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ጋር በሽርክና ብቻ እንዲሰጥ የሚገድቡ እርምጃዎች፣እና

(ረ) የውጭ ካፒታል ተሳትፎን በከፍተኛ የአክሲዮን ድርሻ መወሰን ወይም የግለሰብ ወይም አጠቃላይ የውጭ ኢንቨስትመንት መጠንን መወሰን፡፡

አንቀጽ 20
የሀገር ውስጥና የውጭ አገልግሎትና አገልግሎት አቅራቢዎችን ያለ ልዩነት ማስተናገድ

1. ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ለሌላ አባል ሀገር አገልግሎት አቅራቢዎች ተመሳሳይ ለሆኑ አገልግሎቶችና አገልግሎት ሰጪዎች ቃል ኪዳን በተገባባቸው በሁሉም የአገልግሎት ዘርፎች በቃል ኪዳን ሰንጠረዡ ውስጥ በሰፈሩት ሁኔታዎችና መመዘኛዎች ስምምነት መሰረት ከራሱ አገልግሎትና አገልግሎት ሰጪዎች ባላነሰ ደረጃ ማስተናገድ አለበት፡፡

2. አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ለሌላ ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ለራሱ አገልግሎቶች ወይም አገልግሎት አቅራቢዎች ከሚሰጠው አንድ አይነት ወይም የተለየ መስተንግዶ በመስጠት የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ነን ሊያሟላ ይችላል፡፡

3. አንድ አይነት ወይም የተለየ መስተንግዶ ከሀገር ውስጥ አገልግሎትና አገልግሎት አቅራቢ ያነሰ መስተንግዶ ነው ተብሎ የሚወሰደው የውድድር ስርአቱን ከሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ጋር ሲነጻጸር ለሀገር ውስጥ አገልግሎቶችና አገልግሎት አቅራቢዎች በአድሎአዊነት ሲያሻሽል ነው፡፡

አንቀጽ 21
ተጨማሪ ግዴታዎች

የስምምነቱ አባል ሀገራት የአገልግሎት ንግድ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ እርምጃዎችን በተመለከተ የዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 20 ወይም 21 ግዴታዎች ሰንጠረዥ አካል ያልሆኑ ሌሎችን ጨምሮና በእነዚህ ብቻ ላይ ሳይወሰን በሙያ ብቃት፣በደረጃ ወይም ፈቃድ ጉዳዮች ሊደራደሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ግዴታዎች በስምምነቱ አባል ሀገር የቃል ኪዳን ሰንጠረዥ ውስጥ መስፈር አለባቸው፡፡

አንቀጽ 22
የዝርዝር ግዴታዎች ቃልኪዳን ሰንጠረዥ

1. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 19፣ 20 እና 21 መሰረት የገባውን ዝርዝር ግዴታ ቃልኪዳን በሰንጠረዥ ማስፈር አለበት፣

2. ግዴታ የተገባባቸውን የአገልግሎት ዘርፎችን በተመለከተ ዝርዝር ግዴታዎቹ የሚከተሉትን ማመላከት አለበት፣



(a) terms, limitations and conditions on market access;

(b) conditions and qualifications on national treatment;

(c) undertakings relating to additional commitments; and

(d) where appropriate the time-frame for implementation of such commitments, including their date of entry into force.

3. Measures inconsistent with both Articles 19 and 20 of this Protocol shall be inscribed in the column relating to Article 19 of this Protocol. In this case the inscription will be considered to provide a condition or qualification to Article 20 of this Protocol as well.
4. The Schedules of Specific Commitments, the Modalities for Trade in Services and the list of Priority Sectors shall, upon adoption, form an integral part of this Protocol.
5. The Transitional Implementation Work Programme developed by Member States shall guide the finalisation of outstanding Phase I negotiations on this Protocol, before the entry into force of the Agreement.

Article 23
Modification of Schedules of Specific Commitments

1. A State Party (referred to in this Article as the "modifying State Party") may modify or withdraw any commitment in its schedule, at any time after three years have elapsed from the date on which that commitment entered into force, in accordance with the provisions of this Article.
2. A modifying State Party shall notify its intent to modify or withdraw a commitment pursuant to this Article to the Secretariat no later than three (3) months before the intended date of implementation of the modification or withdrawal. The Secretariat shall promptly circulate this information to State Parties.
3. At the request of any State Party the benefits of which under this Protocol may be affected (referred to in this Article as an "affected State Party"), by a proposed modification or withdrawal notified under paragraph 2 of this Article, the modifying State Party shall enter into negotiations with a view to reaching agreement on any necessary compensatory adjustment. In such negotiations and agreement, the State Parties concerned shall endeavour to maintain a general level of mutually advantageous commitments not less favourable to trade than that provided for in commitments prior to such negotiations.

(ሀ) የገበያ ዕድል ለመስጠት ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች፣ሁኔታዎችና ገደቦች፣

(ለ) ከሀገር ውስጥ አገልግሎት አቅራቢዎችን ያለ ልዩነት ለመስተናገድ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችና መመዘኛዎች፣

(ሐ) በተጨማሪ ግዴታነት በተገናኘ የተገቡ ግዴታዎች ፣ እና

(መ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተገባው ግዴታ ወደስራ የሚገባበትን የጊዜ ማእቀፍ ጨምሮ ግዴታው የሚተገበርበት ቀን፣

3. በዚህ ፕሮቶኮል ከአንቀጽ 19 እና 20 ጋር የማይጣጣሙ እርምጃዎች በአንቀጽ 19 በተገናኘው ረድፍ ላይ ይሰፍራሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ በአንቀጽ 19 ረድፍ ላይ የሰፈሩት ሁኔታዎችና መመዘኛዎች ለአንቀጽ 20ም ያገለግላል፡፡

4. የዝርዝር ግዴታዎች ቃልኪዳን ሰንጠረዥ፣ የአገልግሎት ንግድ አሰራር እና ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው አገልግሎት ዘርፎች ዝርዝር ተቀባይነት ባገኘ ጊዜ የዚህ ፕሮቶኮል አካል መደረግ አለበት፡፡

5. የአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ወደተግባር ከመግባቱ አስቀድሞ የዚህ ፕሮቶኮል የምዕራፍ ነ ድርድሮችን ለማጠናቀቅ የሚረዳ የመሸጋገሪያ ጊዜ ድርጊት የሥራ ፕሮግራም በአባል ሀገራት ይቀረጻል፡፡

አንቀጽ 23
የዝርዝር ግዴታዎችን ቃል ኪዳን ስለማሻሻል

1. ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር (በዚህ አንቀጽ “የሚያሻሽለው የስምምነቱ አባል ሀገር”) በቃል ኪዳኑ የሰፈረውን ማንኛውንም ግዴታ፣ ግዴታው ወደተግባር ከገባ ከሶስት ዓመታት በኋላ በማንኛውም ጊዜ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መሰረት ግዴታውን ሊያሻሽል ወይም ከግዴታው ሊወጣ ይችላል፡፡

2. ግዴታውን የሚያሻሽለው የስምምነቱ አባል ሀገር ግዴታውን የማሻሻል ወይም ከግዴታው የመውጣት ውጥኑን በዚህ አንቀጽ መሰረት ለጽህፈት ቤቱ ግዴታውን ማሻሻሉን ወይም ከግዴታው መውጣቱን ለመተግበር ከታሰበበት ቀን ሶስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡ ጽህፈት ቤቱ መረጃውን ለስምምነቱ አባል ሀገራት ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

3. በማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ጥያቄ መሰረት በዚህ ፕሮቶኮል ጥቅሙ ሊነካ የሚችል (በዚህ አንቀጽ “ጥቅሙ የተነካ የስምምነቱ አባል ሀገር” ተብሎ የሚገለጽ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የማሻሻል ወይም የመውጣት ዕቅዱን ባሳወቀው መሰረት ያሻሽለው አባል ሀገር ጥቅሙ ከተነካ የስምምነቱ አባል ሀገር ጋር ማንኛውንም አስፈላጊ የማካካሻ ስምምነት ላይ ለመድረስ ድርድር ማድረግ አለበት፡፡ በዚህ ድርድርና ስምምነት የሚመለከታቸው የስምምነቱ አባል ሀገራት ከድርድሩ በፊት ከነበረው ግዴታ የማይተናነስና የጋራ ተጠቃሚነት ሊያመጣ የሚችል ግዴታዎችን ለመጠበቅ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

4. Compensatory adjustments shall be made on a most-favoured-nation basis.
5. If agreement is not reached between the modifying State Party and any affected State Party before the end of the period provided for negotiations, such affected State Party may refer the matter to dispute settlement. Any affected State Party that wishes to enforce a right that it may have to compensation must participate in the dispute process.
6. If no affected State Party has requested dispute settlement, the modifying State Party shall be free to implement the proposed modification or withdrawal, within a reasonable period of time.
7. The modifying State Party may not modify or withdraw its commitment until it has made compensatory adjustments in conformity with the findings of the dispute settlement.
8. If the modifying State Party implements its proposed modification or withdrawal and does not comply with the findings of the arbitration, any affected State Party that participated in the dispute settlement may modify or withdraw substantially equivalent benefits in conformity with those findings. Notwithstanding the obligations under Article 4 of this Protocol, such a modification or withdrawal may be implemented solely with respect to the modifying State Party.
9. The Committee on Trade in Services shall facilitate such negotiations and establish related appropriate procedures.

Article 24
Denial of Benefits

Subject to prior notification and consultation, a State Party may deny the benefits of this Protocol to service suppliers of another State Party where the service is being supplied by a juridical person of a non-State Party, without real and continuous link with the economy of the State Party or with negligible or no business operations in the territory of the other State Party or any other State Party.

4. ማካካሻው ለሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት አገልግሎትና አገልግሎት ሰጪዎችን ያለ ልዩነት ማስተናገድ መሰረት መሆን አለበት፡፡

5. ግዴታውን ያሻሻለው የስምምነቱ አባል ሀገርና በማንኛውም ጥቅሙ በተነካ የስምምነቱ አባል ሀገር መካከል የድርድሩ ማጠናቀቂያ ከማለቁ አስቀድሞ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ጥቅሙ የተነካው የስምምነቱ አባል ሀገር ጉዳዩን ወደ አለመግባባቶች መፍቻ ሊወስደው ይችላል፡፡ ማንኛውም ጥቅሙ የተነካና በማካካሻ መብቱን ለማስከበር የሚፈልግ የስምምነቱ አባል ሀገር አለመግባባት አፈታት ሂደት መሳተፍ አለበት፡፡

6. ጥቅሙ የተነካ የስምምነቱ አባል ሀገር አለመግባባት እንዲፈታለት ካልጠየቀ ግዴታውን ያሻሻለው የስምምነቱ አባል ሀገር በምክኒያታዊ ጊዜ ውስጥ ግዴታውን የማሻሻል ወይም ከግዴታው የመውጣት እቅዱን ለመተግበር ነጻ ነው፡፡

7. ከአለመግባባት አፈታቱ ግኝት ጋር በተስማማ መልኩ ማካካሻ እስኪያመቻች ድረስ ግዴታውን ያሻሻለው የስምምነቱ አባል ሀገር ግዴታውን ላያሻሽል ወይም ከግዴታው ያለመውጣት ይችላል፡፡

8. ግዴታውን ያሻሻለው የስምምነቱ አባል ሀገር ግዴታውን የማሻሻል ወይም ከግዴታው የመውጣት እቅዱን ከተገበረና ለግልግል ዳኝነት ግኝት ተገዢ ካልሆነ ማንኛውም አለመግባባት አፈታቱ ላይ ተሳታፊ የነበረ ጥቅሙ የተነካ የስምምነቱ አባል ሀገር ከግኝቱ ጋር አቻ የሆነ ጥቅም የሚያሳጣ ግዴታ ማሻሻል ወይም መሻር ይችላል፡፡ በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 4 የተጠቀሰው ቢኖርም ግዴታ ማሻሻሉ ወይም ከግዴታ መወጣቱ ተግባራዊ የሚደረገው ግዴታውን ባሻሸለው የስምምነቱ አባል ሀገር ላይ ብቻ ሊሆን ይችላል፡፡

9. የአገልግሎት ንግድ ኮሚቴ ድርድሮቹ እንዲቀላጠፉ ያደርጋል፡፡ አስፈላጊውን ተዛማጅ የአሰራር ስርዓት ያቋቁማል፡፡

አንቀጽ 24
ጥቅሞችን ስለመከልከል

አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር አገልግሎቱ ህጋዊ ሰውነት ባለው የስምምነቱ አባል አገር ባልሆነ ከቀረበ፣ ከስምምነቱ አባል ሀገር ኢኮኖሚ ጋር እውነተኛና ቀጣይ ትስስር የሌለው ወይም አነስተኛ ወይም ምንም አይነት የቢዝነስ እንቅስቃሴ በስምምነቱ አባል ሀገር ወይም በማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር የማያደርግ ከሆነ ቅድሚያ በማሳወቅና በመመካከር ላይ ተሞርኩዞ የዚህን ፕሮቶኮል ጥቅም ለሌላ የስምምነቱ አባል ሀገር ሊከለክል ይችላል፣

PART VI
INSTITUTIONAL PROVISIONS

Article 25
Consultation and Dispute Settlement

The provisions of the Protocol on the Rules and Procedures on the Settlement of Disputes shall apply to consultations and the settlement of disputes under this Protocol.

Article 26
Implementation, Monitoring and Evaluation

1. The Council of Ministers in accordance with Article 11 of the Agreement shall establish the Committee on Trade in Services, which shall carry out such functions as may be assigned to it by the Council of Ministers to facilitate the operation of this Protocol and further its objectives. The Committee may establish such subsidiary bodies as it considers appropriate for the effective discharge of its functions.
2. The Chairman of the Committee shall be elected by the State Parties.
3. The Committee shall prepare annual reports for State Parties to facilitate the process of implementation, monitoring and evaluation of this Protocol.

Article 27
Technical Assistance, Capacity Building and Cooperation

1. State Parties recognise the importance of technical assistance, capacity building and cooperation in order to complement the liberalisation of services, to support State Parties' efforts to strengthen their capacity in the supply of services and to facilitate implementation and attainment of the objectives of this Protocol.
2. State Parties agree, where possible, to mobilise resources, in collaboration with development partners, and implement measures, in support of the domestic efforts of State Parties, with a view to, inter alia:
    (a) building capacity and training for trade in services;

ክፍል VI
ተቋማዊ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 25
ምክክርና አለመግባባትን ስለመፍታት

የዚህ ፕሮቶኮል አለመግባባት አፈታት ድንጋጌ ደንብና አሰራሮች ለምክክር እና አለመግባባትን ለመፍታት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 26
ስለትግበራ፣ቁጥጥርና ምዘና

1. የአፍሪካ የሚኒሰትሮች ምክር ቤት በአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ ንግድ ቀጣና አንቀጽ ፲፩ መሰረት በምክር ቤቱ የሚሰጠውን ስራ ለማከናወን፣ የፕሮቶኮሉን እንቅስቃሴ ለማቀላጠፍና ዓላማውን ለማስፋፋት የአገልግሎት ንግድ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ኮሚቴው ስራውን በብቃት ለመወጣት እንደአስፈላጊነቱ ኣጋዥ አካለትን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2. የኮሚቴው ሊቀመንበር በስምምነቱ አባል ሀገራት ይመረጣል፡፡

3. ኮሚቴው የትግበራ ሂደትን፣ቁጥጥርና ምዘናን ለማቀላጠፍ ለስምምነቱ አባል ሀገራት ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

አንቀጽ 27
የቴክኒክ እገዛ፣ አቅም ግንባታ እና ትብብር

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት የቴክኒክ እገዛን አቅም ግንባታ እና ትብብር የአገልግሎት ንግድ ነጻ ማድረግን ለማሟለት፣የስምምነቱ አባል ሀገራትን የአገልግሎት አቅርቦት አቅም ጥረት ለማጎልበት እና የፕሮቶኮሉን ትግበራ ለማቀላጠፍና አላማውን ለማሳካት ጠቃሚነት እውቅና ይሰጣሉ፡፡

2. የስምምነቱ አባል ሀገራት በተቻለ መጠን ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር ሀብትን ለማሰባሰብ፣እና እርምጃዎችን ለመተግበር የስምምነቱ አባል ሀገራትን የሀገር ውስጥ ጥረትን ለመደገፍ ከሌሎች በተጨማሪ የሚከተሉትን ያከናውናሉ፤

    (ሀ) የአገልግሎት ንግድ አቅም ግንባታና ስልጠና፣

(b) improving the ability of service suppliers to gather information on and to meet regulations and standards at international, continental, regional and national levels;

(c) supporting the collection and management of statistical data on trade in services;

(d) improving the export capacity of both formal and informal service suppliers, with particular attention to micro, small and medium size; women and youth service suppliers;

(e) supporting the negotiation of mutual recognition agreements;

(f) facilitating interaction and dialogue between service suppliers of State Parties with a view to promotion of information sharing with respect to market access opportunities, peer learning and the sharing of best practices;

(g) addressing quality and standards needs in those sectors where State Parties have undertaken commitments under this Protocol with a view to supporting the development and adoption of standards; and

(h) developing and implementing regulatory regimes for specific services sectors at continental, regional and national levels, in particular in those sectors in which State Parties have undertaken specific commitments.

3. The Secretariat, working with State Parties, RECs and partners, shall coordinate the provision of technical assistance.

Article 28
Annexes to this Protocol

1. Member States may develop annexes for the implementation of this Protocol relating, inter alia, to:

   (a) Schedules of Specific Commitments;

   (b) MFN Exemption(s);

   (c) Air Transport Services;

   (d) List of Priority Sectors; and

   (e) A framework document on Regulatory Cooperation.

2. Upon adoption by the Assembly, such annexes shall form an integral part of this Protocol.

(ለ) ህጎችና እና ደረጃዎችን በአለም አቀፍ፣ በአህጉራዊ፣ በአካባቢያዊና በብሄራዊ ደረጃ ለማሟላት የአገልግሎት አቅራቢዎችን መረጃ የማሰብሰብ አቅምን ማሻሻል፣

(ሐ) የአገልግሎት ንግድ መረጃዎችን አሰባስበና አስተዳደርን መደገፍ፣

(መ) የመደበኛና መደበኛ ያልሆኑ አገልግሎት አቅራቢዎች በተለይም ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ደረጃ፣ ለሴቶችና ወጣቶች አገልግሎት አቅራቢዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት የወጪ ንግድ አቅማቸውን ማሳደግ፣

(ሠ) የእርስ በርስ እውቅና ስምምነት ድርድርን መደገፍ፣

(ረ) በገበያ ዕድል፣ እርስ በርስ ለመማርና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ የመረጃ ልውውጥ ላይ ያነጣጠረ በአገልግሎት አቅራቢዎችና በመንግስት አካላት መካከል ተግባቦትና ውይይት ማመቻቸት፣

(ሰ) በዚህ ፕሮቶኮል የስምምነቱ አባል ሀገራት ግዴታ በወሰዱባቸው የአገልግሎት ዘርፎች የጥራትና ደረጃን ፍላጎት መረዳት ደረጃዎችን ለማውጣትና ለመደገፍ ባለመ ስራ ላይ ማዋል፣

(ረ) ለተለዩ የአገልግሎት ዘርፎች በአህጉራዊ፣ በአካባቢያዊ እና በብሄራዊ ደረጃ በተለይም አባል ሀገራት ዝርዝር ግዴታ በገቡባቸው ዘርፎች ህጋዊ ሥርዓቶችን መፍጠርና እና መተግበር፣

3. ጽህፈት ቤቱ ከስምምነቱ አባል ሀገራት፣ ከአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰቦች እና አጋሮች ጋር በመሆን የቴክኒክ እገዛ መስጠትን ማስተባበር አለበት::

አንቀጽ 28
የፕሮቶኮሉ አባሪዎች

1. አባል ሀገራት ፕሮቶኮሉን ለመተግበር የሚያስችሉ ከሚከተሉት አባሪዎች ጋር የተገናኙትን ጨምሮ ሊያዘጋጁ ይችላሉ ፤

(ሀ) የዝርዝር ግዴታዎች ቃል ኪዳን፣

(ለ) በአባል ሀገራት መካከል ያለ ልዩነት ማስተናገድ ውጭ የሆኑ፣

(ሐ) የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፣

(መ) ቅድሚያ የተሰጣቸው የአገልግሎት ዘርፎች ዝርዝር፣ እና

(ሠ) የቁጥጥር ትብብር ማዕቀፍ ሰነድ፣

2. አባሪዎቹ በመሪዎች ከጸደቁ በኋላ የፕሮቶኮሉ አካል ይሆናሉ::

3. State Parties may develop additional annexes for the implementation of this Protocol for adoption by the Assembly. Upon adoption by the Assembly, such annexes shall form an integral part of this Protocol.

Article 29
Amendment

This Protocol shall be amended in accordance with the provisions of Article 29 of the Agreement.

3. የስምምነቱ አባል ሀገራት ፕሮቶኮሉን ለመተግበር የሚያስችሉ ተጨማሪ አባሪዎችን በማዘጋጀት በመሪዎች እንዲጸድቁ ለማድረግ ይችላሉ፡፡ አባሪዎቹ በመሪዎች ከጸደቁ በኋላ የፕሮቶኮሉ አካል ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 29
ማሻሻያ

ይህ ፕሮቶኮል በአፍሪካ የነጻ ንግድ ቀጣና አንቀጽ 29 ስምምነት መሰረት ይሻሻላል፡፡

PROTOCOL ON RULES AND PROCEDURES ON THE SETTLEMENT OF DISPUTES

የአለመግባባቶች መፍቻ ህጎችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮል

PROTOCOL ON RULES AND PROCEDURES ON THE SETTLEMENT OF DISPUTES

WE Member States of the African Union,
HAVE AGREED AS FOLLOWS:

Article 1
Definitions

(a) **"AB"** means the Appellate Body established under Article 20 of this Protocol;

(b) **"Complaining Party"** means a State Party that has initiated a dispute settlement procedure under the Agreement;

(c) **"Consensus"** means if no State Party present at the meeting of the DSB when a decision is taken, formally objects to the decision;

(d) **"Days"** means working days save for cases involving perishable goods where Days shall mean calendar days;

(e) **"Dispute"** means a disagreement between State Parties regarding the interpretation and/or application of the Agreement in relation to their rights and obligations;

(f) **"DSB"** means the Dispute Settlement Body established under Article 5 of this Protocol;

(g) **"Panel"** means a Dispute Settlement Panel established under Article 9 of this Protocol;

(h) **"Party to a dispute or proceedings"** means a State Party to a dispute or proceedings;

(i) **"State Party concerned"** is a State Party to which rulings and recommendations of the DSB are directed; and

(j) **"Third Party"** means a State Party with a substantial interest in a dispute.

Article 2
Objective

This Protocol provides for the administration of the Dispute Settlement Mechanism established in accordance with Article 20 of the Agreement and aims at ensuring that the dispute settlement process is transparent, accountable, fair, predictable and consistent with the provisions of the Agreement.

የአለመግባባቶች መፍቻ ሀጎችና ስነስርአቶች ፕሮቶኮል

እኛ የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት፣

እንደሚከተለው ተስማምተናል፡ -

አንቀፅ 1
ትርጓሜ

(ሀ) **"ይግባኝ ሰሚ አካል"** ማለት በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 20 መሰረት የተቋቋመ የይግባኝ ሰሚ አካል ነው፤

(ለ) **"ቅሬታ አቅራቢ ወገን ማለት"** በዚህ ስምምነት መሰረት የአለመግባባት መፍቻ ስነስርአት የጀመረ የዚህ ስምምነት አባል ሀገር ነው፤

(ሐ) **"ስምምነት"** ማለት የአለመግባባት መፍቻ አካል ዉሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ተገኝቶ ዉሳኔውን በይፋ የሚቃወም የስምምነቱ አባል ሀገር የሌለ ሲሆን ነው፤

(መ) **"ቀናት"** ማለት የስራ ቅናት ማለት ሲሆን ለሚበላሹ እቃዎች ሲሆን የካላንደር ቀናት ማለት ነው፤

(ሠ) **"አለመግባባት"** ማለት በዚህ ስምምነት አባል ሀገራት መካከል ሙብቶቻቸዉንና ግዴታዎቻቸውን በተመለከተ በዚህ ስምምነት አተረጓጎም ወይም አተገባበር ላይ የሚነሳ አለመግባባት ነው፤

(ረ) **"የአለመግባባት መፍቻ አካል"** ማለት በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 5 መሰረት የተቋቋመ የአለመግባባት መፍቻ አካል ነው፤

(ሰ) **"ፓነል"** ማለት በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 9 መሰረት የተቋቋመ የአለመግባባት መፍቻ ፓነል ነው።

(ቀ) **"የአለመግባባብት ወይም የክርክር ተሳታፊ ወገን"** ማለት በአለመግባባት ወይም በክርክር ላይ የሚሳተፍ የዚህ ስምምነት አባል ሀገር ነው፤

(ተ) **"የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር"** ማለት የአለመግባባት መፍቻ አካል ዉሳኔ ወይም የዉሳኔ ሀሳብ የሰጠበት የዚህ ስምምነት አባል ሀገር ነው፤ እና

(ቸ) **"ሶስተኛ ወገን"** ማለት በአለመግባባቱ ላይ ከፍተኛ ጥቅም ያለው የዚህ ስምምነት አባል ሀገር ነው።

አንቀፅ 2
ዓላማ

ይህ ፕሮቶኮል በዚህ ስምምነት አንቀጽ 20 መሰረት ለተቋቋመው የአለመግባባት መፍቻ መንገድ አስተዳደርን የሚያቋቋም ሲሆን አላማውም የአለመግባባት መፍቻ መንገዱ ግልፅ፤ተጠያቂ፤ፍትሀዊ፤ተገማች እና ከዚህ ስምምነት ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

Article 3
Scope of Application

1. This Protocol shall apply to disputes arising between State Parties concerning their rights and obligations under the provisions of the Agreement.
2. This Protocol shall apply subject to such special and additional rules and procedures on dispute settlement contained in the Agreement. To the extent that there is a difference between the rules and procedures of this Protocol and the special or additional rules and procedures in the Agreement, the special or additional rules and procedures shall prevail.
3. For the purposes of this Article, a dispute settlement proceeding shall be considered to have been initiated in accordance with this Protocol when the Complaining Party requests consultations pursuant to Article 7 of this Protocol.
4. A State Party which has invoked the rules and procedures of this Protocol with regards to a specific matter, shall not invoke another forum for dispute settlement on the same matter.

Article 4
General Provisions

1. The dispute settlement mechanism of the AfCFTA is a central element in providing security and predictability to the regional trading system. The dispute settlement mechanism shall preserve the rights and obligations of State Parties under the Agreement and clarify the existing provisions of the Agreement in accordance with customary rules of interpretation of public international law.
2. Recommendations or rulings made by the DSB shall be aimed at achieving a satisfactory settlement of a dispute in accordance with rights and obligations under the Agreement.
3. Mutually agreed solutions to matters formally raised in accordance with the consultation and dispute settlement provisions of this Protocol shall be notified to the DSB, where any State Party may raise any point relating thereto.
4. All resolutions to matters formally raised in accordance with the consultations and dispute settlement provisions of this Protocol, including arbitration awards, shall be consistent with the Agreement.

አንቀፅ 3
የአፈፃፀም ወሰን

1. ይህ ፕሮቶኮል የዚህ ስምምነት አባል ሀገራት ከዚህ ስምምነት ከሚመነጩ ሙበቶቻቸውና ግዴታዎቻቸው ጋር በሚነሱ አለመግባባቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

2. ይህ ፕሮቶኮል ተፈፃሚ የሚሆነው በዚህ ስምምነት የተካተቱት ልዩና ተጨማሪ የአለመግባባቶች መፍቻ ድንጋጌዎችና ስነስርአቶች እንደተጠበቁ ሆነው ነው። በዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎችና ስነስርአቶች እና በዚህ ስምምነት የተካተቱት ልዩና ተጨማሪ የአለመግባባቶች መፍቻ ድንጋጌዎችና ስነስርአቶች መካከል ልዩነት ሲኖር ልዩና ተጨማሪ የአለመግባባቶች መፍቻ ድንጋጌዎችና ስነስርአቶች የበላይነት ይኖራቸዋል።

3. ለዚህ አንቀፅ ተፈፃሚነት በዚህ ስምምነት መሰረት አንድ አለመግባባት ተጀመረ የሚባለው ቅሬታ አቅራቢው ወገን በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 7 መሰረት ምክክር ሲጠይቅ ነው።

4. §በዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎችና ስነስርአቶች ለአንድ የተለየ ጉዳይ የጀመረ የዚህ ስምምነት አባል ሀገር በተመሳሳይ ጉዳይ ሌላ የአለመግባባቶች መፍቻ መንገድ መጀመር የለበትም።

አንቀፅ 4
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና የአለመግባባቶች መፍቻ መንገድ ለአካባቢያዊ የንግድ ስርአት ዋስትናና ተገማችነት መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የአለመግባባቶች መፍቻ መንገድ የስምምነቱ አባል ሀገራት በስምምነቱ ያላቸውን መብቶችና ግዴታዎች መጠበቅ እና የዚህን ስምምነት ድንጋጌዎች በመንግስታዊ አለም አቀፍ ህግ ልማዳዊ የትርጓሜ ደንቦች መሰረት ግልፅ ያደርጋል።

2. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የሚሰጣቸው የዉሳኔ ሀሳብና ዉሳኔዎች ግብ በዚህ ስምምነት መብቶችና ግዴታዎች መሰረት አለመግባባቱ ተቀባይነት ባለው መንገድ እንዲፈታ ማድረግ መሆን አለበት።

3. በዚህ ፕሮቶኮል የምክክርና የአለመግባባቶች መፍቻ ድንግጌዎች መሰረት በቀረበ ጉዳይ በጋራ የሚደረስባቸው መፍትሄዎች ለአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ እንዲታወቁ መደረግ ያለበት ሲሆን፤ማንኛዉም የስምምነቱ አባል ሀገር ማንኛውንም ጉዳይ ሊያነሳ ይችላል።

4. በዚህ ፕሮቶኮል የምክክርና የአለመግባባቶች መፍቻ ድንጋጌዎች መሰረት በቀረበ ጉዳይ ላይ የግልግል ዳኝነት ዉሳኔን ጨምሮ የሚሰጥ ማንኛዉም ዉሳኔ ከዚህ ስምምነት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

5. Requests for conciliation, good offices, mediation and the use of dispute settlement procedures should not be intended or considered as contentious acts. If a dispute arises, State Parties will engage in these procedures in good faith in an effort to resolve the dispute. Further, complaints and counter-complaints in regard to separate matters should not be linked.
6. In their findings and recommendations, the Panel and AB shall not add to or diminish the rights and obligations of State Parties pursuant to the Agreement.

Article 5
Dispute Settlement Body

1. The Dispute Settlement Body is hereby established in accordance with Article 20 of the Agreement to administer the provisions of this Protocol except as otherwise provided for in the Agreement.
2. The DSB shall be composed of representatives of the State Parties.
3. The DSB shall have the authority to:
   (a) establish Dispute Settlement Panels and an Appellate Body;
   (b) adopt Panel and Appellate Body reports;
   (c) maintain surveillance of implementation of rulings and recommendations of the Panels and Appellate Body; and
   (d) authorise the suspension of concessions and other obligations under the Agreement.
4. The DSB shall have its own Chairperson and shall establish such rules of procedure as it deems necessary for the fulfilment of its responsibilities. The DSB Chairperson shall be elected by the State Parties.
5. The DSB shall meet as often as necessary to discharge its functions as provided for in this Protocol.
6. Where the rules and procedures of this Protocol provide for the DSB to take a decision, it shall do so by consensus.
7. The DSB shall inform the Secretariat of any dispute related to the provisions of the Agreement.

5. የማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና ጥያቄ ወይም የአለመግባባቶችን መፍቻ ስነስርአቶችን መጠቀም አጨቃጫቂ ጉዳይ ያሉ መሆኑን አያመለክትም። አለመግባባት በሚኖርበት ጊዜ የስምምነቱ አባል ሀገራት አለመግባባቱን በቅን ልቦና ለማስወገድ በማሰብ ወደእነዚህ ስነስርአቶች ይገባሉ። ተመሳሳይ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ እቤቱታዎች እና የአቤቱታ አቤቱታዎች መያያዝ አይኖርባቸዉም።

6. ፓነሉና ይግባኝ ሰሚ አካሉ ግኝቶችና የዉሳኔ ሀሳቦች የስምምነቱ አባል ሀገራት በዚህ ስምምነት ያላቸውን መብቶችና ግዴታዎችን የሚጨምር ወይም የሚቀንስ መሆን የለበትም።

አንቀፅ 5
የአለመግባባቶች መፍቻ አካል

1. የአለመግባባቶች መፍቻ አካል በዚህ ስምምነት አንቀፅ 20 መሰረት በዚህ ስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ይህንን ስምምነት እንዲያስፈፅም ተቋቁሟል።

2. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የስምምነቱ አባል ሀገራት ተወካዮችን ያካተተ መሆን አለበት።

3. የአለመግባባቶች መፍቻ አካል የሚከተሉት ስልጣኖች ይኖሩታል፤

   (ሀ) የአለመግባባት መፍቻ ፓነልና ይግባኝ ሰሚ አካል ማቋቋም፤

   (ለ) የፓነልና ይግባኝ ሰሚ አካሉን ሪፖርቶች ማፅደቅ፤

   (ሐ) የፓነሎችና ይግባኝ ሰሚ አካሉ ዉሳኔዎችና የዉሳኔ ሀሳቦች ስለመፈፀማቸው ክትትል ያደርጋል፤ እና

   (መ) በዚህ ስምምነት መሰረት የተሰጡ ጥቅሞችና ሌሎች ግዴታዎች እንዲታገዱ ያዛል፤

4. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የራሱ ስብሳቢ ይኖረዋል፤ሀላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ነው ብሎ ያሰበውን የአሰራር ስነስርአት ማዘጋጀት አለበት። የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ስብሳቢ በስምምነቱ አባል ሀገራት ይመረጣል።

5. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ በዚህ ፕሮቶኮል የተሰጡትን ተግባራት ለማከናወን እንደአስፈላጊነቱ መሰብሰብ አለበት።

6. የዚህ ፕሮቶኮል ድንጋጌዎችና ስነስርአቶች የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ዉሳኔ እንዲሰጥ በሚፈቅድበት ጊዜ ዉሳኔዉን በስምምነት መስጠት አለበት።

7. የአለመግባባቶች መፍቻ አካል ከዚህ ስምምነት ጋር በተገናኘ የሚቀርቡ አለመግባባቶችን ለጽህፈት ቤቱ ማስታወቅ አለበት።

Article 6
Procedures under the Dispute Settlement Mechanism

1. Where a dispute arises between or among the State Parties, in the first instance, recourse shall be had to consultations, with a view to finding an amicable resolution to the dispute.
2. Where an amicable resolution is not achieved, any party to the dispute shall, after notifying the other parties to the dispute, refer the matter to the DSB, through the Chairperson and request for the establishment of a Dispute Settlement Panel, (hereinafter referred to as the "Panel") for purposes of settling the dispute.
3. The DSB shall adopt Rules of Procedure for the selection of the Panel, including the issues of conduct, to ensure impartiality.
4. The Panel shall set in motion the process of a formal resolution of the dispute as provided for in this Protocol and the parties to the dispute shall, in good faith, observe in a timely manner, any directions, rulings and stipulations that may be given to them by the Panel in relation to procedural matters and shall make their submissions, arguments and rebuttals in a format prescribed by the Panel.
5. The DSB shall make its determination of the matter and its decision shall be final and binding on the parties to a dispute.
6. Where the parties to a dispute consider it expedient to have recourse to arbitration as the first dispute settlement avenue, the parties to a dispute may proceed with arbitration as provided for in Article 27 of this Protocol.

Article 7
Consultations

1. State Parties with a view to encouraging amicable resolution of disputes, affirm their resolve to strengthen and improve the effectiveness of consultation procedures employed by State Parties.
2. Each State Party undertakes to accord consideration to, and afford adequate opportunity for consultations regarding any representation made by another State Party concerning measures affecting the operation of the Agreement.
3. Requests for consultations shall be notified to the DSB through the Secretariat in writing, giving the reasons for the request, including identification of the issues and an indication of the legal basis for the complaint.

አንቀፅ 6
የአለመግባባት ስምምነት ስርአት አካሄድ

1. በአባል ሀገራት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር የሚያስማማ መፍትሄ ለማስገኘት መጀመሪያ ወደ ምክክር መግባት አለባቸው።

2. የሚያስማማ መፍትሄ ማግኘት ካልተገኘ ማንኛውም የሙግቱ ተሳታፊ ወገን ሌላኛዎቹን የሙግቱ ተሳታፊ ወገኖች ካሳወቀ በኋላ አለመግባባቱን በሰብሳቢው በኩል ለአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ማስተላለፍና አለመግባባቱ እንዲፈታለት የአለመግባባት መፍቻ ፓነል (ከዚህ በኋላ ፓነል እየተባለ የሚጠራ) እንዲቋቋም መጠየቅ ይችላል።

3. የአለመግባባቶች መፍቻ አካል ከአድሎ የፀዳ እንዲሆን ለማስቻል የፀባይ/ባህሪን ጨምሮ ለፓነል የአመራረጥ ደንቦችን ማዉጣት አለበት።

4. ፓነሉ አለመግባባቱን ለመፍታት በዚህ ፕሮቶኮል የተቀመጠውን አለመግባባት መፍቻ ስርአት መጀመር ያለበት ሲሆን አለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖችም ስነስርአቶችን በተመለከት ፓነሉ የሚሰጣቸውን አቅጣጫ፤ውሳኔና ትዕዛዝ በቅን ልቦና በጊዜ መፈፀም ይኖርባቸዋል።

5. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ በጉዳይ ላይ ዉሳኔ መስጠት ሲሆን ዉሳኔውም በአለመግባባት ተሳታፊ ወገኖች ላይ የመጨረሻና ገዥ ይሆናል።

6. የአለመግባባት ተሳታፊ ወገኖች የሽምግልና ዳኝነትን እንደፈጣን የመጀመሪያ የአለመግባባት መፍቻ መንገድ ሲወስዱት በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 27 መሰረት ወደሽምግልና ዳኝነት ሊሄዱ ይችላሉ።

አንቀፅ 7
ስለምክክር

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት አለመግባባቶቻቸውን በስምምነት መፍታትን ለማበረታታት በማሰብ የምክክር ስርአቱን ዉጤታማነት ለማጠናከርና ለማሳደግ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያረጋግጣሉ።

2. ማንኛውም አባል ሀገር ሌላ አባል ሀገር በወሰደው በዚህ ስምምነት አፈፃፀም ላይ ተፅእኖ ያላቸውን እርምጃዎች በተመለከተ ለሚያቀርበው የምክክር ጥያቄ ተገቢውን ግምትና እድል መስጠት ይኖርበታል።

3. የምክክር ጥያቄ በጽህፈት ቤቱ በኩል ለአለመግባባት መፍቻ አካል መቅረብና ጉዳዮችን መለየት ጨምሮ ጥያቄው የቀረበበትን ምክንያት እና የአቤቱታውን የህግ መሰረትን ማሳየት አለበት።

4. Where a request for consultations is made pursuant to this Protocol, the State Party to which the request is made shall, unless otherwise mutually agreed, reply to the request within ten (10) days after the date of its receipt and shall enter into consultations in good faith within a period not exceeding thirty (30) days after the date of receipt of the request, with a view to reaching a mutually satisfactory solution.
5. Where a State Party to which the request is made does not respond within ten (10) days after the date of receipt of the request, or does not enter into consultations within a period of thirty (30) days, or a period otherwise mutually agreed, after the date of receipt of the request, the State Party that requested for the consultations may refer the matter to the DSB requesting for the establishment of a Panel.
6. In the course of consultations and before resorting to further action under this Protocol, State Parties shall attempt to obtain satisfactory settlement of the dispute.
7. Consultations shall be:
    (a) confidential; and
    (b) without prejudice to the rights of any State Party in any further proceedings.
8. Where State Parties to a dispute fail to settle a dispute through consultations within sixty (60) days after the date of receipt of the request for consultations, the complaining party may refer the matter to the DSB, for establishment of a Panel. Consultations may be held in the territory of the party complained against unless the Parties agree otherwise. Unless State Parties to a dispute agree to continue or suspend consultations, consultations shall be deemed concluded within the sixty (60) days.
9. In cases of urgency, including cases of perishable goods:
    (a) the State Party shall within ten (10) days after the date of receipt of the request enter into consultations;
    (b) where the parties fail to settle the dispute through consultations within twenty (20) days after the date of receipt of the request, the complaining party may refer the matter to the DSB for establishment of a Panel;

4. በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት የምክክር ጥያቄ ሲቀርብ ጥያቄው የቀረበለት የስምምነቱ አባል ሀገር የተለይ የጋራ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ጥያቄውን በተቀበለ በአስር(10) ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠትና ጥያቄውን በተቀበለ ከሰላሳ (30) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ በቅን ልቦና ወደ ምክክር መግባት አለበት።

5. ጥያቄ የቀረበለት የስምምነቱ አባል ሀገር ጥያቄውን በተቀበለ በአስር (10) ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ወይም ጥያቄውን በተቀበለ ከሰላሳ (30) ቀናት ባልበለጠ ወይም በሌላ በጋራ ስምምነት የተደረገበት ጊዜ ውስጥ ወደ ምክክር ካልገባ ጥያቄውን ያቀረበው የስምምነቱ አባል ሀገር ፓነል እንዲቋቋምለት በመጠየቅ ጉዳዩን ወደ አለመግባባት መፍቻ አካል ሊያስተላልፈው ይችላል።

6. በምክክሩ ጊዜ እና በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት ሌላ ተጨማሪ እርምጃ ከመውሰድ በፊት የስምምነቱ አባል ሀገራት ለአለመግባባቱ ተቀባይነት ያለው መፍትሄ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

7. ምክክሮች፤

   (ሀ) ሚስጥራዊ መሆን፤ እና

   (ለ) የስምምነቱ አባል ሀገራት በሌላ ተጨማሪ ስነስርአቶች ያላቸውን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።

8 በአለመግባባቱ የሚሳተፉ የስምምነቱ አባል ሀገራት ጥያቄውን በተቀበሉ በስድሳ (60) ቀናት ውስጥ አለመግባባቶቻቸውን መፍታት ካልቻሉ አቤቱታ አቅራቢው ወገን ፓነል እንዲቋቋምለት ጉዳዩን ወደ አለመግባባቶች መፍቻ አካል ሊወስደው ይችላል። ተከራካሪ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ምክክሮች አቤቱታ በቀረበበት ወገን ግዛት ውስጥ ሊደረግ ይችላል። ተከራካሪ ወገኖች ለመቀጠል ወይም ለማቋረጥ ካልተስማሙ በስተቀር ምክክሮች በስድሳ (60) ቀናት ጊዜ ውስጥ እንደተጠናቀቁ ይቆጠራል።

9. የሚበላሹ እቃዎችን ጨምሮ አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም፤

   (ሀ) የስምምነቱ አባል ሀገር ጥያቄዉ በደረሰው በበአስር (10) ቀናት ጊዜ ዉስጥ ወደ ምክክር መግባት አለበት፤

   (ለ) ተከራካሪ ወገኖች ጥያቄው በደረሳቸው በሀያ (20) ቀናት ውስጥ አለመግባባቶቻቸውን መፍታት ካልቻሉ አቤቱታ አቅራቢው ወገን ፓነል እንዲቋቋምለት ጉዳዩን ወደ አለመግባባቶች መፍቻ አካል ሊወስደው ይችላል።

(c) pursuant to the provisions of Annex 5 on Non-Tariff Barriers (Appendix 2: Procedures for Elimination and Cooperation in the Elimination of Non-Tariff Barriers), where a State Party fails to resolve an NTB after a mutually agreed solution was reached and after issuing the factual report, the requesting State Party shall resort to the dispute settlement panel stage. Notwithstanding the provisions herein, the above Parties to a dispute may agree to submit the matter to arbitration in accordance with the provisions of Article 27 of this Protocol; and

(d) the parties to the dispute, the DSB and the Panel and Appellate Body shall make every effort to expedite the proceedings to the greatest extent possible.

10. Where a State Party that is not party to a dispute considers that it has substantial trade interest in consultations, that State Party may, within ten (10) days of the circulation of the request for consultations, request the Parties to a dispute to be joined in the consultations.

11. Where the Parties to the dispute agree that the claim of substantial interest is well founded, the Third Party shall be so joined to the consultations. If the request to join the consultations is not accepted, the disputing State Party shall inform the DSB and in this event the applicant State Party shall be free to request consultation.

Article 8
Good Offices, Conciliation and Mediation

1. State Parties to a dispute may at any time voluntarily undertake good offices, conciliation, or mediation. Proceedings that involve good offices, conciliation, or mediation shall be confidential and be without prejudice to the rights of the State Parties in any other proceedings.

2. Good offices, conciliation or mediation may be requested at any time by any State Party to a dispute. They may begin at any time and be terminated at any time by any of the State Parties to the dispute. Once procedures for good offices, conciliation or mediation are terminated, a Complaining Party may then proceed with a request for the establishment of a panel.

(ሐ) ቀረጥ ባልሆኑ የንግድ እንቅፋቶች አባሪ 5 መሰረት (ተቀጽላ 2፡ ቀረጥ ባልሆኑ የንግድ እንቅፋቶች ሰለማስወገድና ስለመተባበር ስነስርአቶች) አንድ የስምምነቱ አባል ሀገር ቀረጥ ያልሆኑ የንግድ እንቅፋቶች ስምምነት ከተደረሰና የፍሬነገር ሪፖርቱ ከወጣ በኋላ መፍትሄ ሊሰጥ ካልቻል አቤቱታውን ያቀረበው አባል ሀገር ወደ ፓነል ሊሄድ ይችላል። እዚህ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ቢኖሩም ከላይ የተገለፁት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩን በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 27 መሰረት ጉዳዩን ለሽምግልና ለማቅረብ ይችላሉ፤ እና

(መ) አለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገሮች፤የአለመግባባቶች መፈቻ አካል፤ ፓነሉና የይግባኝ ሰሚው አካል ሂደቱ በሚቻለው ከፍተኛ ፍጥነት እንዲከናወን ማንኛውንም ጥረት ማድረግ አለባቸው።

10. አንድ የአለመግባባቱ ተሳታፊ ያልሆነ የስምምነቱ አባል ሀገር በምክክሮች ላይ ከፍተኛ የሆነ የንግድ ጥቅም ሲኖረው የምክክሮች ጥያቄዎች በተሰራጩ በአስር(10) ቀናት ውስጥ የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባላት ሀገራትን ምክክሮች ለመቀላቀል ሊጠይቅ ይችላል።

11. የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባላት ሀገራት የቀረበው ከፍተኛ የሆነ የንግድ ጥቅም ተገቢ ምክንያት እንዳለው ሲስማሙ ሶስተኛው ወገን ምክክሩን እንዲቀላቀል ይደረጋል። ምክክሩን ለመቀላቀል የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያላገኘ ሲሆን ጥያቄውን ያቀረበው ወገን ይህንኑ ለአለመግባባቶች መፍቻ አካል ማሳወቅ ይችላል። በዚህም ጊዜ አመልካቹ የስምምነቱ አባል ሀገር ምክክር ለመጠየቅ ይችላል።

አንቀፅ 8
ማስማማት, እርቅ እና ሽምግልና

1. የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገራት በማንኛዉም ጊዜ በፍላጎት ወደ ማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና መሄድ ይችላሉ። በማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና የሚደረጉ ሂደቶች በሚስጥር መያዝ ያለባቸው ሲሆን የስምምነቱ አባል ሀገራት በሌሎች የክርክር ሂደቶች ያላቸዉን መብቶች የሚሳጡ መሆን የለባቸውም።

2. ማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና በማንኛውም የአለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገር ሊጠየቁ ይችላሉ። በማንኛውም የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገር በማንኛዉም ጊዜ ሊጀመሩና በማንኛውም የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገር በማንኛዉም ጊዜ ሊቋረጡ ይችላሉ። ማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና ሂደቶች ሲቋረጡ አቤት ባዩ ወገን ፓነል እንዲቋቋምለት መጠየቅ ይችላል።

3. When good offices, conciliation or mediation are entered into after the date of receipt of a request for consultations, the Complaining Party must allow for a period of sixty (60) days after the date of receipt of the request for consultations before requesting the establishment of a panel. The Complaining Party may request for the establishment of a Panel during the sixty (60) day period, if the State Parties to the dispute jointly consider that the good offices, conciliation or mediation process has failed to settle the dispute.
4. State Parties participating in proceedings under this Article may suspend or terminate those proceedings, at any time, if they consider that the good offices, conciliation or mediation process has failed to settle the dispute.
5. If the State Parties to a dispute agree, the procedures for good offices, conciliation or mediation may continue while the Panel process proceeds.
6. The Head of the Secretariat may be requested by any State Party to a dispute to facilitate the process of good offices, conciliation or mediation, including offering the same. Such a request shall be notified to the DSB and the Secretariat.

Article 9
Establishment of Panels

1. Where an amicable resolution is not achieved through consultations, the Complaining Party shall, in writing refer the matter to the DSB and request for the establishment of a Panel. Parties to a dispute shall be informed promptly of the composition of the Panel.
2. The request referred to in paragraph 1 of this Article shall indicate whether consultations were held, identify the specific measures at issue and provide a summary of the legal basis of the complaint sufficient to present the problem clearly.
3. In case the applicant requests the establishment of a Panel with terms of reference other than the standard terms, the written request shall include the proposed text of special terms of reference.
4. A meeting of the DSB shall be convened within fifteen (15) days of the request to establish a Panel, provided that at least ten (10) days advance notice of the meeting is given to the DSB.
5. The Panel shall be constituted within ten (10) days of the meeting of the DSB referred to in paragraph 4 of this Article.

3. ማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና የምክክር ጥያቄ ከቀረበ በኋላ በሚጀመሩበት ጊዜ አቤት ባዩ ወገን ፓነል እንዲቋቋምለት ከመጠየቁ በፊት የምክክር ጥያቄው ከቀረበ በኋላ በስድሳ (60) ቀናት ማለፍ አለባቸው። የአለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገራት በአንድ ላይ ሆነው ማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና አለመግባባቱን ለመፍታት አልቻለም ብለው ሲወስኑ አቤት ባዩ ወገን በስድሳ (60) ቀናት ጊዜ ዉስጥ ፓነል እንዲቋቋምለት ሊጠይቅ ይችላል።

4. በዚህ አንቀፅ በተገለፀት ሂደቶች ተሳታፊ የሆኑ የስምምነቱ አባል ሀገራት ማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና አለመግባባቱን ለመፍታት አልቻለም ብለው ሲወስኑ ሂደቶችን በማንኛውም ጊዜ ማገድ ወይም ማቋረጥ ይችላሉ።

5. የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገራት ሲስማሙ የፓነል ሂደቱ እየተከናወነ እያለ ማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና ሊቀጥሉ ይችላሉ።

6. ማንኛውም የአለመግባባቱ ተሳታፊ የሆነ የስምምነቱ አባል ሀገር የጽህፈት ቤቱን ሀላፊ ማስማማት፤ እርቅ ወይም ሽምግልና እንዲያመቻች እንዲሁም እነዚህን አገልግሎቶች እንዲሰጥ ሊጠይቅ ይችላል። ጥያቄውን የአለመግባባቶች መፍጫ አካሉ እና ጽህፈት ቤቱ እንዲያዉቁት መደረግ አለበት።

አንቀፅ 9
ስለፓነሎች ምስረታ

1. በምምክክር ተቀባይነት ያለው መፍትሄ ሳይገኝ ሲቀር አቤቱታ አቅራቢው ወገን ጉዳዩን ለአለመግባባቶች መፍቻ አካል በፅሁፍ በመላክ ፓነል እንዲቋቋምለት መጠየቅ ይችላል። የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ስለ ፓነሉ አወቃቅር ወዲያዉኑ ሊገለፅላቸው ይገባል።

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ነ የተገለፀው ጥያቄ ምክክር መደረግ አለመደረጉን ማመልከት፤የጉዳዩ መነሻ የሆነውን እርምጃ እና ችግሩን በበቂ ሁኔታ ሊገልፅ በሚችል መንገድ የአቤቱታውን የህግ መሰረት ባጭሩ ማቅረብ ይኖርበታል።

3. አመልካቹ ከተለመደው ሌላ ቢጋር ያለው ፓነል እንዲቋቋም ሲጠይቅ የሚያቀርበው የፅሁፍ ጥያቄ የታሰበውን ልዩ ቢጋር ማካተት ይኖርበታል።

4. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የፓነል ምስረታ ጥያቄው በቀረበ በአስራ አምስት (15)ቀናት ውስጥ ስብሰባ ማድረግ ይኖርበታል። ሆኖም ከስብሰባው ቢያንስ በአስር (10) ቀናት ቅድሚያ ማስታወቂያ ለአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ መሰጠት ይኖርበታል።

5. ፓነሉ በንኡስ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ስብሰባ በተደረገ በአስር (10) ቀናት ዉስጥ ፓነሉ መመስረት አለበት።

Article 10
Composition of the Panel

1. The Secretariat shall, upon entry into force of the Agreement, establish and maintain an indicative list or roster of individuals who are willing and able to serve as Panellists.
2. Each State Party may annually nominate two (2) individuals to the Secretariat for the inclusion in the indicative list or roster, indicating their area (s) of expertise related to the Agreement. The indicative list or roster of individuals shall be submitted by the Secretariat for consideration and approval by the DSB.
3. Individuals listed on the indicative list or roster shall:
   (a) have expertise or experience in law, international trade, other matters covered by the Agreement or the resolution of disputes arising under international trade agreements;
   (b) be chosen strictly on the basis of objectivity, reliability and sound judgment;
   (c) be impartial, independent of, and not be affiliated to or take instructions from, any Party; and
   (d) comply with a code of conduct to be developed by the DSB and adopted by Council of Ministers.
4. The Panellists shall be selected with a view to ensuring their independence and integrity and shall have a sufficiently diverse background and a wide spectrum of experience in the subject matter of the dispute, unless the Parties to the dispute agree otherwise.
5. In order to ensure and preserve the impartiality and independence of the Panellists, nationals of the disputing State Parties shall not serve on a Panel concerned with that dispute, unless the Parties to the dispute agree otherwise.
6. The Secretariat, shall propose nominations for the Panel to the Parties to the dispute. The Parties to the dispute shall not oppose nominations except for compelling reasons.
7. If no agreement is reached on the composition of a Panel within thirty (30) days after the date of the establishment of a Panel, at the request of either Party, the Head of the Secretariat, in consultation with the Chairperson of the DSB and with the consent of the disputing State Parties, shall determine the composition of the Panel by appointing the Panellists considered to be most appropriate.

አንቀፅ 10
ስለፓነል ጥንቅር

1. ጽህፈት ቤቱ ስምምነቱ በሚፀናበት ጊዜ የፓነል አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሆኑና ችሎታ ያላቸዉን ግለሰቦች መነሻ ዝርዝር ወይም መዝገብ ማዘጋጀትና መያዝ አለበት።

2.. እያንዳንዱ የስምምነቱ አባል ሀገር በየአመቱ ሁለት(2) ግለሰቦችን ከስምምነቱ ጋር ይተገናኘ ሙያቸውን በማመልከት በእጩነት በተዘጋጀው መነሻ ዝርዝር ወይም መዝገብ እንዲካተቱ ለጽህፈት ቤቱ ማቅረብ ይችላል። የግለሰቦች መነሻ ዝርዝር ወይም መዝገብ በጽህፈት ቤቱ በኩል ለአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ዉሳኔ መቅረብ አለባቸው።

3. በመነሻ ዝርዝሩ ወይም መዝገቡ ላይ የሚካተቱት ግለሰቦች፤

   (ሀ) በህግ፤በአለምአቀፍ ህግ፤በሌሎች በስምምነቱ በተካተቱ ጉዳዮች ወይም በአለምአቀፍ የንግድ ስምምነቶች የሚነሱ አለመግባባቶችን በመፍታት ሙያ ወይም ልምድ ያላቸው፤

   (ለ) ፍጹም በሆነ ገለልተኝነት፤አስተማማኝነት እና በጥልቅ እይታ የተመረጡ፤ እና

   (ሐ) በአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀውን የሙያ ስነምግባር የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

4. የፓነሉ አባላት ነፃነታቸውንና ሀቀኝነታቸውን ባረጋገጠ መንገድ መመረጥ ያለባቸውን የአለመግባባቱ ተሳታፊዎች በሌላ አኳኋን ካልተስማሙ በስተቀር በአለመግባባቱ ጉዳይ ላይ በቂና መሰረት ሰፊ እውቀትና ሰፊ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል።

5. የፓነሊስቶችን ገለልተኝነትና ነፃነት ለማረጋገጥ የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገር ዜጎች የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር በአለመግባባቱ ላይ የፓነል አባል ሆነው ማገልገል አይችሉም።

6. ጽህፈት ቤቱ የፓነል አባል እጩዎችን ለአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገራት ማቅረብ አለበት። የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገራት የተለየ አሳማኝ ምክንያት ከሌላቸው በስተቀር የቀረቡትን እጩዎች መቃወም የለባቸውም።

7. ፓነሉ በተቋቋመ በሰላሳ(30) ቀናት ዉስጥ በፓነሉ ጥንቅር ላይ ስምምነት መድረስ ካልተቻለ በአንደኛው ወገን ጥያቄ የጽህፈት ቤቱ ሀላፊ ከአለመግባባቶች መፍቻ ተቋሙ ሰብሳቢ ጋር በመመካከርና በተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ከሁሉም አግባብነት ያላቸውን ግለሰቦች በመምረጥ የፓነሉን ጥንቅር ይወስናል።

8. The Chairperson of the DSB shall inform the State Parties of the composition of the Panel no later than ten (10) days after the date the Chairperson receives such a request.
9. Where there are two (2) disputing State Parties, the Panel shall comprise three (3) members. Where there are more than two (2) disputing State Parties, the Panel shall comprise five (5) members.
10. Panellists shall serve in their individual capacities and not as Government representatives, nor as representatives of any organisation.
11. Panellists shall not receive instructions or be influenced by any State Party when considering matters before them.

Article 11
Terms of Reference of the Panel

1. Panellists shall have the following terms of reference unless the Parties to a dispute agree otherwise, within twenty (20) days from the establishment of the Panel:
   (a) to examine, in the light of the relevant provisions in the Agreement, cited by the Parties to the dispute, the matter referred to the DSB by the Complaining Party; and
   (b) to make such findings as will assist the DSB in making the recommendations or in giving the rulings provided for in the Agreement.
2. Panels shall address the relevant provisions in the Agreement cited by the Parties to the dispute.
3. In establishing a Panel, the DSB may authorise its Chairperson to draw up the terms of reference of the Panel in consultation with the State Parties to the dispute, subject to the provisions of paragraph 1. The terms of reference thus drawn up shall be circulated to all State Parties. If other than standard terms of reference are agreed upon, any State Party may raise any point relating thereto in the DSB.

Article 12
Functions of a Panel

1. The principal function of a Panel is to assist the DSB in discharging its responsibilities under the Agreement.

8. የአለመግባባቶች መፍቻ ተቋሙ ሰብሳቢ ጥያቄ በቀረበለት አስር (10) ቀን ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ ስለ ፓነሉ ጥንቅር ለስምምነቱ አባል ሀገራት ማሳወቅ አለበት።

9. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገራት ሁለት ሲሆኑ የፓነሉ አባላት ሶስት(3)መሆን አለባቸው። የአለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገራት ከሁለት በላይ ሲሆኑ የፓነሉ አባላት አምስት(5) መሆን አለባቸው።

10. የፓነሉ አባላት የሚያገለግሉት እንደግለሰብ እንጅ እንደመንግስት ተወካይ ወይም የማንኛውም ድርጅት ተወካይ በመሆን አይደለም።

11. የሚያዩትን ጉዳይ በተመለከተ የፓነሉ አባላት ትእዛዝ መቀበል ወይም በማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ተፅእኖ ስር መውደቅ የለባቸውም።

አንቀፅ 11
የፓነሉ የስራ ዝርዝር

1. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ፓነሉ በተቋቋመ በሀያ (20) ቀናት ውስጥ በሌላ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የሚከተለው የስራ ዝርዝር ይኖረዋል፤

   (ሀ) በአቤቱታ አቅራቢው ለአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የቀረበውን ጉዳይ አግባብነት ካላቸውና በአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች በተጠቀሱ የስምምነቱ ድንጋጌዎች መሰረት ይመረምራል፤ እና

   (ለ) የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ በስምምነቱ መሰረት የዉሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ወይም ዉሳኔ እንዲሰጥ የሚያግዙ ግኝቶቹን ያሳዉቃል።

2. ፓነሎች በአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች የተጠቀሱ አግባብነት ያላቸው የስምምነቱ ድንጋጌዎችን መርምረው መወሰን አለባቸው።

3. ፓነሉን ሲያቋቁም የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ሰብሳቢ የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖችን በማማከርና የንኡስ አንቀጽ ነ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የፓነሉን የስራ ዝርዝር እንዲያዘጋጅ ሊያዝ ይችላል። የተዘጋጀው የስራ ዝርዝር ለሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት መተላለፍ አለበት። ስምምነት የተደረሰበት የስራ ዝርዝር ከተለመደው የተለየ ሲሆን ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ከስራ ዝርዝሩ ጋር በተገናኘ ማንኛውንም ጉዳይ ሊያነሱ ይችላሉ።

አንቀፅ 12
የፓነሉ ተግባራት

1. የፓነሉ ዋነኛ ተግባር የአለመግባባቶች መፍቻ አካል በዚህ ስምምነት የተጣለበትን ሀላፊነት እንዲወጣ ማገዝ ነው።

2. In performing this function, a Panel shall make an objective assessment of the matter before it, including an objective assessment of the facts of the case and the applicability of and conformity with the relevant provisions of the Agreement and make findings to assist the DSB in making recommendations and rulings.
3. The Panel shall consult widely and regularly with the Parties to a dispute and give them an adequate opportunity to develop a mutually satisfactory solution.

Article 13
Third Parties

1. The interests of all Parties to a dispute including Third Parties shall be taken into account during the Panel process.
2. A Third Party shall, after notification of its substantial interests to the Panel through the DSB, provided that disputing parties agree that the claim of substantial interest is well founded, have an opportunity to be heard and to make written submissions to the Panel.
3. Copies of the submissions shall be served on the Parties to the dispute and shall be reflected in the report of the Panel.
4. If a Third Party considers that a measure already the subject of a Panel proceeding impairs or nullifies benefits accruing to it under the Agreement, that Third Party may have recourse to normal dispute settlement procedures under this Protocol. Such a dispute shall be referred to the original Panel wherever possible.
5. Third Parties shall receive the submissions of the Parties to a dispute at the first meeting of the Panel.

Article 14
Procedures for Multiple Complaints

1. Where more than one (1) State Party requests for the establishment of a Panel related to the same matter, a single Panel may be established to examine these complaints, taking into account the rights of all State Parties concerned. A single Panel shall be established to examine such complaints whenever feasible.

2. ፓነሉ ተግባሩን ሲያከናውን የጉዳዩን ፍሬ ነገር እና አግባብነት ካላቸው የስምምነቱ ድንጋጌዎች ጋር ተፈፃሚነትና መጣጣምን ጨምሮ የቀረበለትን ጉዳይ ተጨባጭ በሆነ መልኩ መርምሮ የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የዉሳኔ ሀሳብ እንዲሰጥ ወይም ዉሳኔ እንዲሰጥ የሚረዳውን ግኝት ይሰጣል።

3. ፓነሉ ከአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ጋር በስፋትና በቋሚነት ምክክር ማድረግና የሚያግባባቸው የጋራ መፍትሄ እንዲያመነጩ በቂ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።

አንቀፅ 13
ሶስተኛ ወገኖች

1. በፓነል አሰራር ሶስተኛ ወገኖችን ጨምሮ የሁሉም የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ጥቅም ግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል።

2. ሶስተኛ ወገን ያለውን ከፍተኛ ጥቅም በአለመግባባቶች መፍቻ አካል በኩል ለፓነሉ ካስታወቀ በኋላ እና የአለመግባባት ተሳታፊ ወገኖች የከፍተኛ ጥቅም መሰረት ያለው መሆኑን ሲስማሙ የመሰማት እና ሀሳቡንም በፅሁፍ ለፓነሉ የማቅረብ መብት ይኖረዋል።

3. በፅሁፍ የቀረቡ ቅጂዎች ለአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች መሰጠትና በፓነል ሪፖርትም መካተት አለበት።

4. አንድ ሶስተኛ ወገን በፓነሉ እየታየ ያለው እርምጃ በስምምነቱ ያገኘውን ጥቅም ጎድቷል ወይም ዉድቅ አድርጓል ብሎ ሲያስብ በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት ወደመደበኛው የአለመግባባቶች መፍቻ ስርአት ሊገባ ይችላል። እንዲህ አይነቱ አለመግባባት በተቻለ መጠን ቀደም ሲል ወደነበረው ፓነል መመራት ይኖርበታል።

5. ሶስተኛ ወገኖች የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖችን ያቀረቡትን በመጀመሪያው የፓነሉ ስብሰባ ጊዜ ሊሰጡ ይገባል።

አንቀፅ 14
በርካታ ቅሬታዎች ሲኖሩ ስለሚኖር ስነስርአት

1. ከአንድ በላይ የሆኑ የስምምነቱ አባል ሀገራት በአንድ አይነት ጉዳይ ላይ ፓነል ሲጠይቁ የጠየቁትን ወገኖች መብቶች ግምት ዉስጥ በማስገባት ጉዳዩን ለመመርመር አንድ ፓነል ሊቋቋም ይችላል። በዚህ ጊዜ የሚቻል እስከሆነ ድረስ አንድ ፓነል መቋቋምና ጉዳዩን መመርመር ይኖርበታል።

2. The single Panel shall organise its examination and present its findings to the DSB in such a manner that the rights, which the Parties to the dispute would have enjoyed had separate Panels examined the complaints, are in no way impaired. If one of the Parties to the dispute so requests, the Panel shall submit separate reports on the dispute concerned. The written submissions by each of the Complaining Parties shall be made available to the other Complaining Parties, and each Complaining party shall have the right to be present when any one of the other Complaining Party presents its views to the Panel.
3. If more than one Panel is established to examine the complaints related to the same matter, to the greatest extent possible the same persons shall serve as Panellists on each of the separate Panels and the timetable for the Panel process in such disputes shall be harmonised.

Article 15
Procedures for the Panel

1. The procedures of the Panel shall provide sufficient flexibility to ensure an effective and timely resolution of disputes by the Panels.
2. After consulting the Parties to a dispute, the Panellists shall, within seven (7) days after the composition of the Panel and the determination of its terms of reference, fix the timetable for the proceedings of the Panel. The timetable thus drawn up shall be circulated to all State Parties.
3. In determining the timetable for the proceedings of the Panel, the Panel shall, within ten (10) working days, upon the expiry of the seven (7) days referred to in paragraph 2, set precise time limits for written submissions by the Parties to a dispute. Parties to a dispute shall comply with the set time limits.
4. The period in which the Panel shall conduct its business, from the date of establishment of the Panel to the date of issuance of the final report to the Parties to a dispute, shall not exceed five (5) months and in cases of urgency, including cases of perishable goods, the period shall not exceed one and a half (1½) months.
5. Where the Parties to the dispute have failed to develop a mutually satisfactory solution, the Panel shall submit its findings in the form of a written report to the DSB. In such cases, the report of the Panel shall set out the findings of the fact, the applicability of the relevant provisions and the basic rationale behind any findings and recommendations that it makes.

2. የሚቋቋማው ፓነል የተለያዩ ፓነሎች ጉዳዩን ቢመረምሩት ኖሮ የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ሊኖራቸው የሚችለውን መብቶች በምንም አይነት በማይገድብ መልኩ ምርመራውን ማደራጀትና ግኝቱን ለአለመግባባቶች መፍቻ አካል ማቅረብ ይኖርበታል። ከአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች አንዱ ሲጠይቅ ፓነሉ በተጠቀሰው አለመግባባት የተለያዩ ሪፖርቶችን ማቅረብ ይኖርበታል። በጽሁፍ የቀረበው የእያንዳንዱ አቤቱታ አቅራቢ (ሰነድ) ለሌሎች አቤቱታ አቅራቢዎች መሰጠት አለበት። እያንዳንዱ አቤቱታ አቅራቢ ለሌላኛው አቤቱታ አቅራቢ ሀሳቡን ለፓነል ሲያቀርብ የመገኘት መብት አለው።

3. አንድ አይነት ጉዳይ ለማየት ከአንድ በላይ ፓነል ሲቋቋም በተቻለ መጠን ተመሳሳይ ሰዎች በእያንዳንዱ ፓነል ላይ እንዲያገለግሉ ማድረግ እና የፓነሎቹ አካሄድ የጊዜ ሰሌዳ መጣጣም አለባቸው።

አንቀፅ 15
የፓነሉ የስነስርአት አካሄድ

1. የፓነሉ የስነስርአት አካሄድ ፓነሎቹ ዉጤታማና በጊዜው አለመግባባቶችን መፍታት የሚያስችል በቂ ተለማጭነት መስጠት አለበት።

2. ፓነሉ የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖችን ካማከረ በኋላ እና ፓነሉ በተቋቋመና የስራ ዝርዝሩ በተወሰነ በሰባት (7) ቀናት ውስጥ የፓነሉን አካሄድ የጊዜ ሰሌዳ መወሰን አለበት። የተወሰነው የጊዜ ሰሌዳ ለሁሉም የስምምነቱ አባል ሀገራት መሰራጨት ይኖርበታል።

3. የፓነሉን አካሄድ የጊዜ ሰሌዳ ሲወስን ፓነሉ በንኡስ አንቀጽ ፣ የተጠቀሰው የሰባት (7) ቀን ጊዜ ባለቀ በአስር (10) ቀናት ዉስጥ የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖችን የፅሁፍ ክርክር የሚያቀርቡበትን ትክክለኛ የጊዜ ገደብ መወሰን አለበት። የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖችን የተወሰንውን የጊዜ ገደብ መከተል አለባቸው።

4. ፓነሉ ስራውን ለመከናወን የሚወስድበት ጊዜ ከተመሰረተበት ቀን አንስቶ የመጨረሻውን ሪፖርቱን ለአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች እስከሚያሳውቅበት ድረስ ከአምስት(5) ወር መብለጥ የለበትም። የሚበላሹ እቃዎችን ጨምሮ አስቸኳይ ለሆኑ ጉዳዮች ጊዜው ከአንድ ወር ተኩል(፣ 1/2) መብለጥ የለበትም።

5. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ሁሉንም የሚያስማማ መፍትሄ ማምጣት ካልቻሉ ፓነሉ ግኝቱን በፅሁፍ ለአለመግባባቶች መፍቻ አካል ሪፖርት ማቅረብ አለበት። በዚህ ጊዜም የፓነሉ ሪፖርት የፍሬነገር ግኝቱን፤አግባባነት ያላቸው ድንጋጌዎችን ተፈፃሚነት እና ለግኝቶቹና ላቀረባቸው የዉሳኔ ሀሳቦች መሰረታዊ ምክንያታዊነቶችን ማሳየት አለበት።

6. Where a settlement of the matter among the Parties to the dispute has been found, the report of the Panel shall be confined to a brief description of the case and to reporting that a solution has been reached.
7. Where a Panel determines that it cannot issue its report within five (5) months, or within one and a half (1½) months in cases of urgency, the Panel shall immediately inform the DSB in writing of the reasons for the delay together with an estimation of the period within which the Panel shall be ready to issue its report. Where a Panel cannot issue a report within the period specified in paragraph 4 of this Article, the Panel shall issue the report within nine (9) months from the date of its composition.
8. The reports of the Panel shall be drafted in the absence of the Parties to the dispute and shall be based on information and evidence provided by the parties and any other person, expert or institution in accordance with this Protocol.
9. The Panel shall produce a single report reflecting the views of the majority of the Panellists.
10. Without prejudice to the provisions of this Article, the Panel shall follow the working procedures specified in the Annex on Working Procedures of the Panel unless the Panel decides otherwise after consulting the Parties to the dispute.
11. The Panel shall, at the request of both Parties to a dispute, suspend its work at any time for a period agreed by the Parties not exceeding twelve (12) months and shall resume its work at the end of this agreed period at the request of the Complaining Party. If the Complaining Party does not request the resumption of the Panel's work before the expiry of the agreed suspension period, the procedure shall be terminated. The suspension and termination of the Panel's work are without prejudice to the rights of either Party to a dispute in another proceeding on the same matter.

Article 16
Right to Seek Information

1. The Panel shall have the right to seek information and technical advice from any source that it deems appropriate, after informing the relevant authorities of State Parties to the dispute.
2. The Panel shall have the right to seek information and technical advice from any State Party provided that the State Party is not a Party to the dispute.

6. በአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች መካከል ስምምነት ሲገኝ የፓነሉ ሪፖርት ጉዳዩን ባጭር በመግለፅና መፍትሄ ላይ መደረሱን በመግለፅ ብቻ መገደብ ይኖርበታል።

7. ፓነሉ ሪፖርቱን በአምስት(5) ወራት ወይም በአስቸኳይ ጊዜ በአንድ ወር ተኩል(1 1/2) ማዉጣት እንደማይችል ሲወስን ፓነሉ ለመዘግየቱ ምክንያቱን እና ሪፖርቱን ሊያቀርብበት የሚችልበትን ጊዜ ግምት በመግለፅ ወዲያውኑ ለአለመግባባቶች መፍቻ አካል ማሳወቅ አለበት። ፓነሉ ሪፖርቱን በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 4 ላይ በተገለፀው ጊዜ ዉስጥ ማዉጣት ካልቻለ ከተቋቋመበት ቀን አንስቶ በዘጠኝ(9) ወራት ዉስጥ ሪፖርቱን ይፋ ማድረግ አለበት።

8. የፓነሉ ሪፖርቶች የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች በሌሉበት መዘጋጀት እና በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት ተከራካሪ ወገኖች፤ሌላ ማናቸው ሰው፤ ባለሙያ ወይም ተቋም በሰጡት መረጃና ባቀረቡት ማስረጃ ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል።

9. ፓነሉ የአብዛኛውን የፓነል አባላት ሀሳብ የያዘ አንድ ሪፖርት ማዉጣት አለበት።

10. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖችን አማክሮ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር ፓነሉ በፓነል የስራ ስነስርአትን የሚደነግገውን ተቀጽላ መከተል አለበት።

11. ፓነሉ በሁለቱ የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ጥያቄ በማንኛውም ጊዜ ከአስራ ሁለት(12) ወራት ጊዜ ላልበለጠ ጊዜ አግዶ ሊቆይ ይችላል፤በአቤቱታ አቅራቢው ወገን ጥያቄ ስምምነት የተደረገበት ጊዜ ሲያበቃ ፓነሉ ስራዉን መቀጠል ይኖርበታል። አቤቱታ አቅራቢው ወገን ፓነሉ ስራዉን እንዲቀጥል ስምምነት የተደረሰበት ታግዶ የሚቆየበት ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ካልጠየቀ ጉዳዩን የመመልከቱ ስርአት መቋርጥ ይኖርበታል። የፓነሉ ስራ መታገድ እና መቋረጥ የአንደኛው ወገን በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ሌላ ክስ የማቅረብ መብት የሚከለክል አይሆንም።

አንቀፅ 16
መረጃ የመጠየቅ መብት

1. ፓነሉ አግባብነት ያላቸውን የአለለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገሮችን ባለስልጣኖች በማስታወቅ አግባብነት አለው ብሎ ከሚያስበው ማንኛዉም ምንጭ መረጃና ቴክኒካዊ ምክር የመጠየቅ መብት አለው።

2. ፓነሉ የአለመግባባቱ ተሳታፊ ካልሆነ ማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር መረጃና ቴክኒካዊ ምክር የመጠየቅ መብት አለው።

3. Where a Panel seeks information or technical advice from a State Party, such State Party shall, within the time set by the Panel, respond to the request made for such information.
4. Confidential information that is provided shall not be disclosed without formal authorisation from the source providing the information.
5. Where a Party to a dispute raises a factual issue concerning a scientific or other technical matter, the Panel may request for an advisory report in writing from an expert review group with relevant qualifications and experience on the issue.
6. Rules for the establishment of the expert review group and its procedures are set forth in the Annex on Expert Review.
7. The Panel may seek information from any relevant source and may consult experts to obtain their opinion on any matter that may be brought before it.

Article 17
Confidentiality

1. The deliberations of the Panels shall be confidential.
2. A Party to a dispute shall treat as confidential any information submitted to a Panel and designated as such, by another Party to a dispute.
3. Nothing in this Protocol shall preclude a Party to a dispute from disclosing statements of its own positions to the public.
4. The reports of the Panels shall be drafted without the presence of the parties to the dispute in light of the information provided and the statements made.
5. Opinions expressed in the Panel report by the individual panellists shall be anonymous.

Article 18
Reports of a Panel

1. A Panel shall consider the rebuttal submissions and arguments of the Parties to a dispute and issue a draft report containing descriptive sections of the facts and arguments of the dispute, to the Parties to a dispute.
2. The Parties to a dispute shall submit their comments on the draft report in writing to the Panel, within a period set by the Panel.

3. ፓነሉ የስምምነቱ አባል ሀገር ከሆነ ሀገር መረጃና ቴክኒካዊ ምክር ሲጠይቅ አባል ሀገሩ ፓነሉ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ዉስጥ ለጥያቄው መልስ መስጠት ይኖርበታል።

4. የተሰጠ ሚስጥራዊ መረጃ የመረጃው ምንጭ በይፋ ፈቃድ ሳይሰጥ ይፋ መደረግ የለበትም።

5. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገን ሳይንሳዊ ውይም ሌላ ቴክኒካዊ ጉዳይን የሚመለከት የፍሬ ነገር ክርክር ሲያንሳ ፓነሉ በጉዳዩ ላይ አግባብነት ያለው የሙያ ብቃትና ልምድ ካለው የኤስክፐርት መርማሪ ቡድን የምክር ሪፖርት በፅሁፍ መጠየቅ ይችላል።

6. የኤክስፐርት መርማሪ ቡድን ማቋቋሚያ ደንቦችና የስነስርአት አካሄዱ በኤክስፐርት ምርመራ ተቀጽላ ላይ ተዘርዝሯል።

7. ፓነሉ ከማንኛውም አግባብነት ካለው ምንጭ መረጃ መጠየቅ እና በቀረበለት ማንኛዉም ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን ለማግኘት ኤክስፐርቶችን ማማከር ይችላል።

አንቀፅ 17
ስለሚስጥራዊነት

1. የፓነሉ ውይይቶች ምስጢራዊ መሆን አለባቸው።

2. የአለመግባባቱ ተሳታፊ በሌላ የአለመግባባት ተሳታፊ ለፓነሉ የተሰጠንና በዚሁ ተሳታፊ ምስጢራዊ ተብሎ የተወሰነ መረጃን ምስጢራዊነት መጠበቅ አለበት።

3. ይህ ፕሮቶኮል የአለመግባባት ተሳታፊ የራሱን አቋም ለህዝብ ይፋ እንዳያደርግ አይከለክልም።

4. የፓነሉ ሪፖርቶች በቀርቡት መረጃዎችና ሀሳቦች መሰረት የአለመግባባት ተሳታፊ ወገኖች በሌሉበት መዘጋጀት ይኖርበታል።

5. የፓነሉ አባላት በፓነሉ ሪፖርት የገለፁት ሀሳብ ስም አልባ መሆን አለበት።

አንቀፅ 18
የፓነሉ ሪፖርቶች

1. ፓነሉ የአለመግባባት ተሳታፊዎችን መቃወሚያዎችን እና ክርክሮችን በመመርመር ፍሬነገሮችንና ክርክሮችን የሚዘረዝር ክፍል የያዘ ሪፖርት ለአለመግባባቱ ተሳታፊዎች ማቅረብ አለበት።

2. የአለመግባባቱ ተሳታፊዎች ፓነሉ በወሰነው ጊዜ ዉስጥ በፓነሉ ረቂቅ ሪፖርት ላይ አስተያየታቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ።

3. Taking into account any comments received under paragraph 2 of this Article, or on the expiration of the time set for the receipt of comments from the Parties to a dispute, the Panel shall issue an interim report to the Parties to a dispute, containing descriptive sections and its findings and conclusions.
4. Within a period set by a Panel, any Party to a dispute may submit a written request for review of specific aspects of the interim report prior to the issuance and circulation of the final report to the Parties to a dispute.
5. At the request of any Party to a dispute, the Panel shall hold a meeting with the Parties to a dispute on the review of specific aspects of the interim report.
6. Where no comments are received by the Panel within the period set for the receipt of comments on the interim report, the interim report shall be deemed to be the Panel's final report and it shall be promptly circulated to the Parties to a dispute and any interested parties and shall be forwarded to the DSB for consideration.
7. The final report of the Panel shall include a discussion of the arguments made at the interim review stage.

Article 19
Adoption of Report of a Panel

1. In order to provide sufficient time for the State Parties to consider the reports of the Panel, the reports shall not be brought up for consideration by the DSB before the expiration of twenty (20) days from the date on which the Panel circulated the report.
2. State Parties having objections to a Panel report shall give written reasons to the DSB, explaining their objections, which may include discovery of new facts, which by their nature have decisive influence on the decision provided that:
    (a) such objections must be notified to the DSB within ten (10) days prior to a meeting of the DSB at which the Panel report will be considered; and
    (b) the objecting party shall serve a copy of the objection with the other parties to the dispute and to the Panel that made the report.
3. Parties to a dispute shall have the right to participate fully in the consideration of the Panel reports by the DSB and their views shall be fully recorded.

3. በንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የቀረቡ አስተያየቶችን ግምት ዉስጥ በማስገባት ወይም ለአስተያየት ማቅረቢያ የቀረበው የጊዜ ገደብ ሲያበቃ የጉዳዩን ዝርዝር እና ግኝቶችንና ማጠቃለያዎችን የያዘ ጊዜያዊ ሪፖርቱን ለአለመግባባቱ ተሳታፊዎች ማሳወቅ ይኖርበታል።

4 ፓነሉ በወሰነው ጊዜ ዉስጥ እና የመጨረሻው ሪፖርት ለአለመግባባቱ ተሳታፊዎች ከመሰጠቱ በፊት ማንኛውም የአለመግባባት ተሳታፊ የጊዜያዊ ሪፖርቱ የተወሰነ ክፍል እንደገና እንዲታይ በፅሁፍ መጠየቅ ይችላል።

5. በማንኛውም የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገን ጥያቄ ፓነሉ የጊዜያዊ ሪፖርቱ የተወሰነ ክፍል እንደገና ማየትን አስመልክቶ ከአለመግባባቱ ተሳታፊዎች ጋር ስብሰባ ማድረግ አለበት።

6. በጊዜያዊ ሪፖርቱ ላይ አስተያየት ለመስጠት በተወሰነው ጊዜ አሰተያየት ለፓነሉ ካልቀረበ ጊዜያዊ ሪፖርቱ እንደመጨረሻ የፓነሉ ሪፖርት ተቆጥሮ ወዲያውኑ ለአለመግባባቱ ተሳታፊዎች እና ጥቅም ላላቸው ወገኖች መሰራጨትና እንዲመለከተው ለአለመግባባት መፍቻ አካሉ መቅረብ ይኖርበታል።

7. የፓነሉ መጨረሻው ሪፖርት በጊዜያዊ ሪፖርቱ ምርመራ ጊዜ የተደረጉ ክርክሮችን ማካተት ይኖርበታል።

አንቀፅ 19
የፓነሉን ሪፖርት ስለማፅደቅ

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት የፓነሉን ሪፖርቶች ለመመርመር በቂ ጊዜ ለመስጠት ፓነሉ ሪፖርቱን ካሰራጨ ሀያ (20) ቀናት ከማለፉ በፊት ሪፖርቶች የአለመግባባት መፍቻ አካሉ እንዲመለከታቸው መቅረብ የለባቸውም።

2. በፓነሉ ሪፖርት ላይ ተቃዉሞ ያላቸው የስምምነቱ አባል ሀገራት በውሳኔው ላይ ወሳኝ ተፅእኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ አዲስ የተገኙ ፍሬነገሮችን ጨምሮ ተቃውሟቸውን በማብራራት ምክንያታቸውን በፅሁፍ ለአለመግባባት መፍቻ አካሉ ማቅረብ ይችላሉ። ይሁንና፤

   (ሀ) ተቃውሞው የፓነሉ ሪፖርት ከሚታይበት የአለመግባባት መፍቻ አካሉ ስብሰባ አሰር(10) ቀናት በፊት ለአለመግባባት መፍቻ አካሉ መታወቅ አለበት፤እና

   (ለ) ተቃውሞውን ያቀረበው ወገን የተቃውሞውን ቅጂ ለሌላኛው ወገንና ሪፖርቱን ላዘጋጀው ፓነል መስጠት አለበት።

3. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች የፓነሉ ሪፖርት በሚታይበት የአለመግባባት መፍቻ አካሉ ስብሰባ በሙሉ የመሳተፍ መብት አላቸው፤ የሚያቀርቡት ሀሳብም በሙሉ መመዝገብ አለበት።

4. Within sixty (60) days from the date the final Panel report is circulated to the State Parties, the report shall be considered, adopted and signed at a meeting of the DSB convened for that purpose, unless a Party to the dispute formally notifies the DSB of its decision to appeal or the DSB decides by consensus not to adopt the report. If a Party to a dispute has notified its decision to appeal, the report by the Panel shall not be considered for adoption by the DSB until after completion of the appeal. The decision of the DSB shall be final except as otherwise provided for in this Article.
5. The Parties to the dispute shall be entitled to a signed copy of the adopted report within seven (7) days of its adoption.
6. An appeal on the report of the Panel shall be lodged with the DSB within thirty (30) days from the date of communication of the decision to appeal by the State Party to the DSB.

Article 20
Appellate Body

1. A standing Appellate Body (AB) shall be established by the DSB. The AB shall hear appeals from panel cases.
2. The AB shall be composed of seven (7) persons, three (3) of whom shall serve on any one case.
3. Persons serving on the AB shall serve in rotation. Such rotation shall be determined in the working procedures of the AB.
4. The DSB shall appoint persons to serve on the AB for a four-year term, and each person may be reappointed once. Vacancies shall be filled as they arise. A person appointed to replace a person whose term of office has not expired shall hold office for the remainder of the predecessor's term.
5. The DSB shall appoint a person to fill the vacancy within two (2) months from the date the vacancy arose.
6. Where the DSB fails to appoint a person to fill the vacancy within two (2) months, the Chairperson of the DSB in consultations with the Secretariat shall within a period of one (1) month fill the vacancy.
7. The AB shall comprise of persons of recognised authority, with demonstrated expertise in law, international trade and the subject matter of the Agreement generally.

4. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገን በይፋ ይግባኝ ለማለት መወሰኑን ለአለመግባባት መፍቻ አካሉ ካላሳወቀ ወይም የአለመግባባት መፍቻ አካሉ በስምምነት ሪፖርቱን ላለማፅደቅ ካልወሰነ በስተቀር የመጨረሻው የፓነል ሪፖርት ለስምምነቱ አባል ሀገራት ከተሰራጨ ከስድሳ (60) ቀናት በኋላ ሪፖርቱ የአለመግባባት መፍቻ አካሉ ለዚሁ ጉዳይ በሚያደርገው ስብሰባ መታየት፤መፅደቅና መፈረም አለበት። የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገን ይግባኝ ለማለት መወሰኑን ካሳወቀ ይግባኙ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የፓነሉ ሪፖርት ለመፅደቅ መታየት የለበትም። በዚህ አንቀፅ በሌላ ሁኔታ ከተገለፀው ዉጭ የአለመግባባት መፍቻ አካሉ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

5. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ሪፖርቱ በፀደቀ በሰባት (7) ቀናት ውስጥ የፀደቀውን ሪፖርት የተፈረመ ቅጂ የማግኘት መብት አላቸው።

6. በፓነሉ ሪፖርት ላይ የሚቀርብ ይግባኝ ይግባኝ የማለት ዉሳኔው ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (30) ቀናት ጊዜ ዉስጥ ለአለመግባባት መፍቻ አካሉ መቅረብ ይኖርበታል።

አንቀፅ 20
ይግባኝ ሰሚ አካል

1. ቋሚ የይግባኝ ሰሚ አካል በአለመግባባት መፍቻ አካሉ ይቋቋማል። ይግባኝ ሰሚው አካል ከፓነል ጉዳዮች የሚቀርቡ ይግባኞችን ይሰማል።

2. ይግባኝ ሰሚ አካሉ ሰባት (7) ሰዎችን የሚይዝ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ሶስቱ ለአንድ ጉዳይ ያገለግላሉ።

3. ይግባኝ ሰሚ አካሉ ላይ የሚያገለግሉ ሰዎች በዝውውር ያገለግላሉ። ዝውውሩ በይግባኝ ሰሚ አካሉ የአሰራር ስነስርአት ደንብ ይወሰናል።

4. የአለመግባባት መፍቻ አካሉ በይግባኝ ሰሚ አካሉ የሚያገለግሉ ሰዎችን ለአራት አመት የጊዜ ዘመን ይሾማል፤እያንዳንዱ ሰው ለአንድ ተጨማሪ የጊዜ ዘመን እንደገና ሊሾም ይችላል። ክፍት የስራ ቦታዎች ሲኖሩ እንዲሞሉ መደረግ ይኖርባቸዋል። አንድ የጊዜ ዘመኑ ያላለቀ ሰዉን ተክቶ የተሾመ ሰው ቦታውን የሚይዘው የተካው ሰው ለቀረው የጊዜ ዘመን ብቻ ነው።

5. የአለመግባባት መፍቻ አካሉ ክፍት ቦታ ሲኖር በሁለት (2)ወራት ዉስጥ መሙላት አለበት።

6. የአለመግባባት መፍቻ አካሉ ከፍት ቦታውን በሁለት (2) ወራት ዉስጥ ሳይሞላ ሲቀር የአለመግባባት መፍቻ አካሉ ሰብሳቢ ከጽህፈት ቤቱ ጋር በመመካከር ክፍት ቦታውን በአንድ (1) ወር ጊዜ ዉስጥ መሙላት አለበት።

7. ይግባኝ ሰሚ አካሉ አባላት እውቅናን ያተረፉ፤በህግ፤አለምአቀፍ ህግ እንዲሁም በስምምነቱ በአጠቃላይ ግልፅ የሆነ እውቀት ያላቸውን ሰዎች መያዝ አለበት።

8. Members of the AB shall not be affiliated to any government. The AB shall broadly represent the membership within the AfCFTA. All persons serving on the AB shall be available at all times and on short notice, and shall stay abreast of dispute settlement activities and other relevant activities of the AfCFTA. They shall not participate in the consideration of any disputes that would create a direct or indirect conflict of interest.

Article 21
Appeals

1. Only Parties to the dispute, may appeal a Panel report. Third Parties which have notified the DSB of a substantial interest in the matter pursuant to paragraph 2 of Article 13 of this Protocol, may make written submissions to, and be given an opportunity to be heard by, the AB.
2. As a general rule, the proceedings shall not exceed sixty (60) days from the date a party to the dispute formally notifies its decision to appeal, to the date the AB circulates its report. In fixing its timetable the AB shall take into account the provisions of paragraph 9 (d) of Article 7 of this Protocol if relevant. Where the AB considers that it cannot provide its report within sixty (60) days, it shall inform the DSB in writing of the reasons for the delay together with an estimate of the period within which it will submit its report. In no case shall the proceedings exceed ninety (90) days.
3. An appeal shall be limited to issues of law covered in the Panel report and legal interpretations developed by the Panel.
4. The AB shall be provided with appropriate administrative and legal support as it requires.
5. The expenses of persons serving on the AB, including travel and subsistence allowance, shall be met from the AfCFTA budget in accordance with the financial rules and regulations of the AU.

Article 22
Procedures for Appellate Review

1. Working procedures shall be drawn up by the AB in consultation with the Chairperson of the DSB and communicated to the State Parties for their information.
2. The proceedings of the AB shall be confidential.
3. The conduct of an appeal under this Article shall not exceed ninety (90) days.

8. ይግባኝ ሰሚ አካሉ አባላት ከማንኛውም መንግስት ጋር የተቆራኙ መሆን የለባቸውም።ይግባኝ ሰሚ አካሉ በአጠቃላይ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና አባላትን መወከል አለበት። በይግባኝ ሰሚ አካሉ የሚያገለግሉ ሰዎች ሁልጊዜና በአጭር ጊዜ ለስራ መገኘት እና የአለመግባባት መፍታት እና በአጠቃላይ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣናን የሚመለከቱ ጉዳዮችን መከታተል ይኖርባቸዋል። በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ የጥቅም ግጭት በሚፈጥርባቸው ውሳኔ ላይ መሳተፍ የለባቸውም።

አንቀፅ 21
ስለ ይግባኞች

1. በፓነል ሪፖርት ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችሉት የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ብቻ ናቸው። በጉዳይ ላይ ከፍተኛ ጥቅም እንዳላቸው ለአለመግባባት መፍቻ አካሉ በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 13 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ያስታወቁ ሶስተኛ ወገኖች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የማቅረብና በይግባኝ ሰሚው አካል የመሰማት እድል ሊኖራቸው ይገባል።

2. በመርህ ደርጃ የክርክር ሂደቶች የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገን ይግባኝ ለማለት መወሰኑን ካስታወቀበት ቀን ጀምሮ ይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርቱን ይፋ እስካደረገበት ድረስ ከስድሳ (60) ቀናት በላይ መውሰድ የለባቸውም። የጊዜ ሰሌዳዉን ሲያወጣ ይግባኝ ሰሚ አካሉ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው የዚህን ፕሮቶኮል አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 9(መ) ድንጋጌዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። ይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርቱን በሰድሳ (60) ቀናት ጊዜ ውስጥ ማዉጣት እንደማይችል ሲወስን ይግባኝ ሰሚ አካሉ ለመዘግየቱ ምክንያቱን እና ሪፖርቱን ሊያቀረብበት የሚችልበትን ጊዜ ግምት በመግለፅ ወዲያውኑ ለአለመግባባቶች መፍቻ አካል ማሳወቅ አለበት። የክርክር ሂደቱ በማናቸውም ምክንያት ከዘጠና (90) ቀናት በላይ መውሰድ የለበትም።

3. ይግባኙ በፓነል ሪፖርቱ በተካተቱ የህግ ጉዳዮች እና ፓነሉ በተከተለው የህግ ትርጉም ላይ ብቻ የተገደበ መሆን ይኖርበታል።

4. ይግባኝ ሰሚ አካሉ የሚያስፈልጉት አስተዳደራዊና የህግ ድጋፍ ሊሰጠው ይገባል።

5. ጉዞና ቀለብን ጨምሮ በይግባኝ ሰሚ አካሉ የሚያገለግሉ ባለሙያዎች ወጪዎች በአፍሪካ ህብረት የገንዘብ ህጎችና ደንቦች መሰረት ከአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና በጀት መሸፈን አለበት።

አንቀፅ 22
የይግባኝ ምርመራ ስነስርአቶች

1. የአሰራር ስነስርአቶች ከአለመግባባቶች መፍቻ አካል ሰብሳቢ ጋር በመመካከር በይግባኝ ሰሚ አካሉ መዘጋጀትና ለመረጃ ለስምምነቱ አባል ሀገራት መገለፅ ይኖርበታል።

2. የይግባኝ ሰሚ አካሉ ጉዳዩን የማየት ስርአት ምስጢራዊ መሆን አለበት።

3. በዚህ አንቀፅ የተገለፀው የይግባኝ ስርአት ከዘጠና (90) ቀናት በላይ መውሰድ አይኖርበትም።

4. The reports of the AB shall be drafted without the presence of the Parties to the dispute and in the light of the information provided and the statements made.
5. Opinions expressed in the AB report by individuals serving on the AB shall be anonymous.
6. The AB shall address each of the issues raised in accordance with paragraph 3 of Article 21 of this Protocol, during the appellate proceeding.
7. The AB may uphold, modify or reverse the legal findings and conclusions of the Panel.
8. The AB shall produce a single report reflecting the views of the majority of its members.
9. An AB report shall be adopted by the DSB and unconditionally accepted by the Parties to the dispute unless the DSB decides by consensus not to adopt the AB report within thirty (30) days following its circulation to the State Parties. This adoption procedure is without prejudice to the right of State Parties to express their views on an AB report.

Article 23
Panel and Appellate Body Recommendations

Where the Panel or the AB concludes that a measure is inconsistent with the Agreement, it shall recommend that the State Party concerned bring the measure into conformity with the Agreement. In addition to its recommendations, the Panel or the AB may suggest ways in which the State Party concerned could implement the recommendations.

Article 24
Surveillance of Implementation of Recommendations and Rulings

1. State Parties shall promptly comply with recommendations and rulings of the DSB.
2. A State Party concerned shall inform the DSB of its intentions in respect of the implementation of the recommendations and rulings of the DSB, at a meeting of the DSB which shall be held within thirty (30) days after the date of adoption of the report by the Panel or the AB.

4. የይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርቶች በቀርቡት መረጃዎችና ሀሳቦች መሰረት የአለመግባባት ተሳታፊ ወገኖች በሌሉበት መዘጋጀት ይኖርበታል።

5. በይግባኝ ሰሚ አካሉ የሚያገለግሉ ግለሰቦች በይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርት የገለፁት ሀሳብ ስም አልባ መሆን አለበት።

6. ይግባኝ ሰሚ አካሉ ጉዳዩን ሲመለከት በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 21 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በአያንዳንዳቸው የተነሱ ጉዳዮች ማየት ይኖርበታል።

7. ይግባኝ ሰሚ አካሉ የፓነሉን የህግ ግኝቶች እና መደምደሚያዎች ሊያፀና፤ሊያሻሽል ወይም ሊገለብጥ ይችላል።

8. ይግባኝ ሰሚ አካሉ የአብዛኛውን አባላት ሀሳብ የያዘ አንድ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት።

9. የአለመግባባቶች መፍቻ አካል የይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርት ለስምምነቱ አባል ሀገራት በተሰራጨ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ሪፖርቱን ላለማፅደቅ በስምምነት ካልወሰነ በቀር የይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርት አለመግባባቶች መፍቻ አካሉ መፅደቅና የአለመግባባቱ ተሳታፊ የስምምነቱ አባል ሀገራት ያለምንም ቅድመሁኔታ ሊቀበሉት ይገባል። ይህ የማፅደቅ ስነስርአት የስምምነቱ አባል ሀገራት በይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርት ላይ ያላቸውን ሀሳብ የመግለፅ ሙብታቸውን አያሳጣም።

አንቀፅ 23
የፓነልና የይግባኝ ሰሚ አካሉ የዉሳኔ ሀሳቦች

ፓነሉ ወይም ይግባኝ ሰሚ አካሉ አንድ የተወሰደ እርምጃ ከዚህ ስምምነት ጋር አንደማይጣጣም ከወሰነ የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር እርምጃውን ከስምምነቱ ጋር እንዲያስማማ የዉሳኔ ሀሳብ መስጠት አለበት። ከውሳኔ ሀሳቡ በተጨማሪ ፓነሉ ወይም ይግባኝ ሰሚ አካሉ የስምምነቱ አባል ሀገር የዉሳኔ ሃሳቡን ስራ ላይ ሊያዉልባቸው የሚችልባቸውን መንገዶች ሊጠቁም ይችላል።

አንቀፅ 24
የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎች መተግበራቸውን መከታተል

1. የስምምነቱ አባል ሀገራት የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎች ወዲያዉኑ መተግበር ይኖርባቸዋል።

2. የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎችን ስለመተግበር ያለውን ሀሳብ የፓነሉ ወይም የይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርት ከፀደቀ በኋላ በሰላሳ (30) ቀናት በሚደረገው የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ስብሰባ ላይ ማሳወቅ ይኖርበታል።

3. Where a State Party concerned finds it impracticable to comply immediately with the recommendations and rulings of the DSB, the State Party concerned shall be granted a reasonable period in which to comply on the following basis:
   (a) period of time proposed by the State Party concerned provided that the DSB approves the proposal; or
   (b) in the absence of such approval a period mutually agreed by the Parties to a dispute within forty-five (45) days of the date of adoption of the report of the Panel and the AB and recommendations and rulings of the DSB; or
   (c) in the absence of such agreement, a period of time determined through binding arbitration within ninety (90) days after the date of adoption of the recommendations and rulings. In such arbitration, a guideline for the arbitrator should be that the reasonable period of time to implement Panel or AB recommendations should not exceed fifteen (15) months from the date of adoption of a Panel or AB report. However, that time may be shorter or longer, depending upon the particular circumstances.
4. If the parties cannot agree on an arbitrator within ten (10) days after referring the matter to arbitration, the arbitrator shall be appointed by the Secretariat in consultation with the DSB within ten (10) days, after consulting the Parties.
5. The Secretariat shall keep the DSB informed of the status of the implementation of decisions made under this Protocol.
6. Except where the Panel or the AB has extended, pursuant to Paragraph 7 of Article 15 or Paragraph 2 of Article 21 of this Protocol, the time of providing its report, the period from the date of establishment of the Panel by the DSB until the date of determination of the reasonable period of time shall not exceed fifteen (15) months unless the Parties to the dispute agree otherwise. Where either the Panel or the AB has extended the time of providing its report, the additional time taken shall be added to the fifteen (15) month period; provided that unless the Parties to the dispute agree that there are exceptional circumstances, the total time shall not exceed eighteen (18) months.

3. የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎችን ወዲያውኑ መተግበር የማይቻል መሆኑን ሲያውቅ የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር ከዚህ በታች በተገለፀው መሰረት እንዲተገብር ተገቢ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል፤

    (ሀ) የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ሲያፀድቀው የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር የጠየቀው ጊዜ፤ወይም

    (ለ) የፀደቀ ጊዜ በማይኖርበት ጊዜ የፓነሉ እና የይግባኝ አካሉ ሪፖርትና የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎችን በፀደቁ በአርባ አምስት (45) ቀናት ውስጥ በአለመግባባቱ ተሳታፊዎች ስምምነት የሚወሰን ጊዜ፤ ወይም

    (ሐ) የዚህ አይነት ስምምነት በማይኖርበት ጊዜ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎችን በፀደቁ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ በአስገዳጅ የግልግል ዳኝነት የተወሰነው ጊዜ። በዚህ የግልግል ዳኝነት ጊዜ የግልግል ዳኞች መመሪያ የፓነል ወይም የይግባኝ ሰሚ አካሉ ዉሳኔ ሀሳቦችን ለመተግበር ተገቢ ጊዜ የፓነል ወይም ሪፖርት ከፀደቀበት ቀን አንስቶ ከአስራ አምስት (15) ወራት ሊበለጥ እንደማይችል ነው። ነገር ግን ጊዜው እንደእያንዳንዱ ጉዳይ ሁኔታ ሊያጥር ወይም ሊረዝም ይችላል።

4. የአለመግባባቱ አባል ሀገራት ጉዳዩን ወደግልግል ዳኝነት ከወሰዱ በኋላ በአስር(10) ቀናት ውስጥ በግልግል ዳኛ ላይ ካልተስማሙ ሀገራቱን በማማከር የግልግል ዳኛው የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉን በማማከር በጽህፈት ቤቱ በአስር 10 ቀናት ውስጥ ይሾማል።

5. ጽህፈት ቤቱ በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት የተሰጡ ዉሳኔዎች አተገባበር ሁኔታን ለአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ በየጊዜው ማሳወቅ አለበት።

6. ፓነሉ ወይም የይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርት የሚያወጡበትን ጊዜ በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 15 ንኡስ አንቀጽ 7 ወይም በአንቀፅ 21 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ካላራዘመ በስተቀር የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ፓነል ካቋቋመበት ጊዜ ቀን አንሰቶ የአፈፃፀም ተገቢ ጊዜ እስከሚወሰንበት ያለው ጊዜ በአለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገራት በሌላ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ከአስራ አምስት (15) ወራት መብለጥ የለበትም። ፓነሉ ወይም የይግባኝ ሰሚ አካሉ ሪፖርት የሚያወጡበትን ጊዜ ሲያራዝሙ የተራዘመው ጊዜ በአስራ አምሰት (15) ወሩ ላይ መደመር አለበት። ይሁንና የአለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገራት የተለዩ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ካልተስማሙ በስተቀር ጠቅላላ ጊዜው ከአስራ ስምንት (18) ወራት መብለጥ አይኖርበትም።

7. Where there is disagreement as to the existence or consistency with the agreement of measures taken to comply with the recommendations and rulings, such disagreement shall be decided through recourse to these dispute settlement procedures, including wherever possible resort to the original Panel. The Panel shall circulate its report within ninety (90) days after the date of its establishment. Where the Panel considers that it cannot circulate its report within this time frame, it shall inform the DSB in writing of the reasons for the delay together with an estimate of the period within which it will circulate its report.
8. The DSB shall keep under surveillance the implementation of adopted recommendations or rulings. The issue of implementation of the recommendations or rulings may be raised at the DSB by any State Party at any time following their adoption. Unless the DSB decides otherwise, the issue of implementation of the recommendations or rulings shall be placed on the agenda of the DSB meeting after six (6) months following the date of establishment of the reasonable period of time pursuant to paragraph 3 of this Article, and shall remain on the DSB's agenda until the issue is resolved.
9. At least ten (10) days prior to each such DSB meeting, the State Party concerned shall provide the DSB with a detailed status report which shall contain among others:
    (a) the extent of the implementation of the ruling(s) and recommendation(s);
    (b) issues if any, affecting the implementation of the rulings and recommendations;
    (c) the period of time required by the State Party concerned to fully comply with implementation of the ruling(s) and recommendation(s).

7. የዉሳኔ ሀሳቦችንና ዉሳኔዎችን ለመተግበር የተወሰዱ እርምጃዎች ስለመኖራቸው ወይም ከስምምነቱ ጋር ስለመጣጣማቸው አለመግባባት ሲፈጠር በአለመግባባቶች መፍቻ ስነስርአቶች መሰረት እና ቢቻል ወደዋናው ፓነል በመሄድ መወሰን ይኖርበታል። ፓነሉ በተመሰረተ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ሪፖርቱን ማሰራጨት ይኖርበታል። ፓነሉ ሪፖርቱን በዚህ ጊዜ ውስጥ ማሰራጨት እንደማይችል ሲወስን ለመዘግየቱ ምክንያቱን እና ሪፖርቱን ሊያሰራጭ የሚችልበትን ጊዜ ግምት በመገለፅ ወዲያውኑ ለአለመግባባቶች መፍቻ አካል በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።

8. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የተሰጡ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎች መተግበራቸውን መከታተል አለበት። የተሰጡ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎች አተገባበር ጉዳይ ከፀደቁ በኋላ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም የስምምነቱ አባል ሀገር ለአለመግባባቶች መፍቻ አካል ሊነሳ ይችላል።የአለመግባባቶች መፍቻ አካል በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር የተሰጡ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎች አተገባበር ጉዳይ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት ተገቢው የትግበራ ጊዜ ከተወሰነበት ቀን አንስቶ ከስድስት(6) ወራት በኋላ በአለመግባባቶች መፍቻ አካል አጀንዳ ላይ መቀመጥና ጉዳዩ እስኪፈታ ድረስ በአጀንዳው ላይ መቆየት አለበት።

9. ከአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ እያንዳንዱ የዚህ አይነት ስብሰባ አስር (10) ቀን ቀደም ብሎ የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ የሚከተሉትን የያዘ ዝርዝር ሪፖርት መስጠት ይኖርበታል፤

   (ሀ) የዉሳኔዎችና የዉሳኔ ሀሳቦች የአፈፃፀም ደረጃ፤

   (ለ) የዉሳኔዎችና የዉሳኔ ሀሳቦች አተገባበር ላይ ተፅእኖ እያሳደሩ ያሉ ጉዳዮች ካሉ፤

   (ሐ) ዉሳኔዎችንና የዉሳኔ ሀሳቦችን ሙሉ በሙሉ ለመተግበር የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር የሚፈልገው ጊዜ።

Article 25
Compensation and the Suspension of Concessions or any other Obligations

1. It is the duty of the State Parties to fully implement the recommendations and rulings of the DSB. Compensation and the suspension of concessions or other obligations are temporary measures available to the aggrieved Party in the event that the accepted recommendations and rulings of the DSB are not implemented within a reasonable period of time. Provided that neither compensation nor the suspension of concessions or other obligations is preferred to full implementation of the accepted recommendations. However, compensation is voluntary and, if granted, shall be consistent with the Agreement.
2. The suspension of concessions or other obligations shall be temporary and shall only be applied in as far as it is consistent with this Agreement and shall subsist until such a time as the inconsistency with the Agreement, or any other determined breach is removed, or that the State Party implements recommendations, or provides a solution to the injury caused, or occasioned by the non-compliance, or that a mutual satisfactory solution is reached.
3. In the event that the rulings and recommendations of the DSB are not implemented within a reasonable period of time, the aggrieved Party may request the DSB to impose temporary measures which include compensation and the suspension of concessions.
4. If the State Party concerned fails to bring the measure found to be inconsistent with the Agreement into compliance therewith or otherwise comply with the decisions and rulings within the reasonable period of time determined pursuant to Paragraph 3 of Article 24 of this Protocol, such State Party shall, if so requested, enter into negotiations with a Complaining Party, with a view to developing mutually acceptable compensation. If no satisfactory compensation has been agreed upon within twenty (20) days, a Complaining Party may request authorisation from the DSB to suspend the application to the State Party concerned of concessions or other obligations under the Agreement.
5. In considering what concessions or other obligations to suspend, the Complaining Party shall apply the following principles and procedures:
    (a) the general principle is that the Complaining Party should first seek to suspend concessions or other obligations with respect to the same sector(s) as that in which the Panel or AB has found a violation or other nullification or impairment;

አንቀፅ 25
ሰለካሳና የተሰጡ ጥቅሞችን ወይም ሌሎች ግዴታዎችን ስለማገድ

1. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉን የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎች ሙሉ በሙሉ መተግበር የስምምነቱ አባል ሀገራት ግዴታ ነው። ካሳ እና የተሰጡ ጥቅሞችን ወይም ሌሎች ግዴታዎችን ማገድ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎች በተገቢው ጊዜ ሳይተገበሩ ለተጎዳው ወገን የሚኖሩ ጊዜያዊ እርምጃዎች ናቸው። ካሳ ወይም የተሰጡ ጥቅሞችን ወይም ሌሎች ግዴታዎችን ማገድ ዉሳኔዎቹን ሙሉ በሙሉ ከመተግበር የሚመረጡ አይደሉም።ይሁንና ካሳ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረት ሲሆን ሲፈቀድም ከስምምነቱ ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።

2. የተሰጡ ጥቅሞችን ወይም ሌሎች ግዴታዎችን ማገድ ጊዜያዊ እና ከዚህ ስምምነት ጋር እስከተጣጣመ ድረስ ብቻ የሚፈፀም እንዲሁም ከስምምነቱ ጋር አለመጣጣሙ ወይም ሌላ የተወሰነ ጥሰት እስከተወገደ ድረስ ወይም የስምምነቱ አባል ሀገር የዉሳኔ ሀሳቦችን እስኪተገብር ድረስ ወይም ባለመፈፀሙ ምክንያት ወይም ካለመፈፀሙ ጋር ተያይዞ ለደረሰው ጉዳት መፍትሄ እስከሚሰጥ ድረስ ወይም የጋራ መፈትሄ እሲኪገኝ ድረስ ብቻ መተግበር ያለበት ነው።

3. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎች በተገቢው ጊዜ ሳይፈፀሙ ሲቀሩ ተጎጅው ወገን የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ካሳ እና የተሰጡ ጥቅሞችን ማገድን ጨምሮ ጊዜያዊ እርምጃዎችን እንዲወስድለት ሊጠይቅ ይችላል።

4. የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር ከስምምነቱ ጋር እንደማይጣጣም የተወሰነውን እርምጃ ወዲያዉኑ እንዲጣጣም ካላደረገ ወይም የዉሳኔ ሀሳቦችና ዉሳኔዎችን በዚህ ስምምነት አንቀፅ 24 ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት በተወሰነው ተገቢ ጊዜ ካልተገበረ ይሄው የስምምነቱ አባል ሀገር ጥያቄ ሲቀርብለት ከአቤት ባዩ ወገን ጋር በጋራ ተቀባይነይ ያለው ካሳ ለመወሰን ያለመ ድርድር መጀመር አለበት። በሀያ (20) ቀናት ዉስጥ ተቀባይነት ያለው ካሳ ላይ ስምምነት ካልተደረሰ አቤት ባዩ ለሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር የተሰጡ ጥቅሞችን ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ማገድ እንዲችል የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ትእዛዝ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል።

5. የሚያግዳቸውን የተሰጡ ጥቅሞችን ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ለመወሰን አቤት ባዩ ወገን የሚከተሉትን መርሆችና ስነስርአቶች መከተል ይኖርበታል፤

    (ሀ) በመርህ ደረጃ አቤት ባዩ ወገን በመጀመሪያ ፓነሉ ወይም ይግባኝ ሰሚ አካሉ ጥሰት ወይም ዋጋ አልባነት ወይም ገደብ ባገኘበት ተመሳሳይ ዘርፍ ላይ የተሰጡ ጥቅሞችን ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ማገድ፤

(b) if that Party considers that it is not practicable or effective to suspend concessions or other obligations with respect to the same sector(s), it may seek to suspend concessions or other obligations in other sectors under the Agreement;

(c) if that Party considers that it is not practicable or effective to suspend concessions or other obligations with respect to other sectors under this agreement, and that the circumstances are serious enough, it may seek to suspend concessions or other obligations under the Agreement; and

(d) if that Party to a dispute decides to request authorisation to suspend concessions or other obligations pursuant to subparagraphs (b) or (c), it shall state the reasons thereof in its request to the DSB.

6. In applying the above principles that party shall take into account:

(a) the trade in the sector under which the Panel or Appellate Body has found a violation or other nullification or impairment, and the importance of such trade to that party; and

(b) the broader economic elements related to the nullification or impairment and the broader economic consequences of the suspension of concessions or other obligations.

7. The level of the suspension of concessions or other obligations authorised by the DSB shall be equivalent to the level of the nullification or impairment.

8. When the situation described in paragraph 4 of this Article occurs, the DSB, shall grant authorisation to suspend concessions or other obligations within thirty (30) days from the date of request unless the DSB decides by consensus to reject the request. However, if the State Party concerned objects to the level of suspension proposed, or claims that the principles and procedures set forth in paragraph 5 have not been followed where a complaining party has requested authorisation to suspend concessions or other obligations pursuant to paragraph 5(b) or (c) of this Article, the matter shall be referred to arbitration. Such arbitration shall be carried out by the original Panel, if Panellists are available, or by an arbitrator appointed by the chairperson of the DSB and shall be completed within sixty (60) days from the date of appointment of the arbitrator. Concessions or other obligations shall not be suspended during the course of the arbitration.

(ለ) አቤት ባዩ ወገን ተመሳሳይ ዘርፍ (ዘርፎች) ላይ የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ማገድ ተፈፃሚ መሆን የማይችል ወይም ውጤታማ የማይሆን መሆኑን ካመነ በስምምነቱ በተሸፈኑ ሌሎች ዘርፎች ላይ የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ማገድ ይችላል፤

(ሐ) አቤት ባዩ ወገን በሌሎች ዘርፎች ላይ የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ማገድ ተፈፃሚ መሆን የማይችል ወይም ውጤታማ የማይሆን መሆኑን ካመነ በስምምነቱ ላይ የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ማገድ ይችላል፤

(መ) የአለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገር በንኡስ ፓራግራፍ (ለ) ወይም (ሐ) መሰረት የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ለማገድ ትእዛዝ እንዲሰጠው የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉን ሲጠይቅ ምክንያቶቹን አብሮ ማቅረብ ይኖርበታል።

6. ከላይ የተገለፁትን መርሆዎች ሲፈፅም እርምጃውን የሚወስደው ወገን የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፤

(ሀ) ፓነሉ ወይም ይግባኝ ሰሚ አካሉ ጥሰት ወይም ዋጋ አልባነት ወይም ገደብ ባገኘበት ዘርፍ ያለው ንግድ እና ንግዱ የሚሰጠው ጥቅም፤እና

(ለ) ከዋጋ አልባነቱ ወይም ገደቡ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች እና የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ማገድ የሚያስከትለውን ጠቅላላ የኢኮኖሚ ዉጤቶች፡

7. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉን የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎች ላይ የሚያዘው የገደብ መጠን ከዋጋ አልባነቱ ወይም ገደቡ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይኖርበታል።

8. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 4 ላይ የተገለፀው ሁኔታ ሲያጋጥም የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ጥያቄውን ላለመቀበል በስምምነት ካልወሰነ በስተቀር ጥያቄው በቀረበ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ለማገድ ትእዛዝ መስጠት ይኖርበታል። ነገር ግን የሚመለከተው የስምምነቱ አባል ሀገር የቀረበውን የእገዳ መጠን ሲቃወም ወይም አቤት ባዩ ወገን በንኡስ አንቀጽ 5 (ለ) ወይም (ሐ) መሰረት የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ለማገድ ትእዛዝ እንዲሰጠው ሲጠይቅ በንኡስ አንቀጽ 5 የተገለፁት መርሆችና ስነስርአቶች አልተሟሉም ብሎ ሲከራከር ጉዳይ ወደግልግል ዳኝነት መመራት ይኖርበታል። ግልግሉም የፓነሉ አባላት የሚገኙ ሲሆን በመጀመሪያው ፓነል ወይም በአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ሰብሳቢ በሚሰየም ገላጋይ መከናወን እና ገላጋዩ በተሾመ በስድሳ (60) ቀናት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርበታል። ግልግሉ እየተደረገ ባለበት ጊዜ የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎች መታገድ አይኖርባቸውም።

9. The arbitrator acting pursuant to paragraph 7 of this Article, shall not examine the nature of the concessions or other obligations to be suspended but shall determine whether the level of such suspension is equivalent to the level of nullification or impairment. The arbitrator may also determine if the proposed suspension of concessions or other obligations is allowed under the Agreement. However, if the matter referred to arbitration includes a claim that the principles and procedures set forth in paragraph 3 of this Article, have not been followed, the arbitrator shall examine that claim. In the event the arbitrator determines that those principles and procedures have not been followed, the complaining party shall apply them consistent with paragraph 5 of this Article. The Parties to a dispute shall accept the arbitrator's decision as final and the parties concerned shall not seek a second arbitration. The DSB shall be informed promptly of the decision of the arbitrator and shall upon request, grant authorisation to suspend concessions or other obligations where the request is consistent with the decision of the arbitrator, unless the DSB decides by consensus to reject the request.

Article 26
Costs

1. The DSB shall determine the remuneration and expenses of the Panellists, arbitrators and experts in accordance with the financial rules and regulations of the AU.
2. The remuneration of the Panellists, arbitrators and experts, their travel and lodging expenses, shall be borne in equal parts by the Parties to a dispute, or in proportions determined by the DSB.
3. A Party to a dispute shall bear all other costs of the process as determined by the DSB.
4. Parties to the dispute shall be required to deposit their share of the Panellists' expenses with the Secretariat at the time of establishment, or composition of the Panel.

Article 27
Arbitration

1. Parties to a dispute may resort to arbitration subject to their mutual agreement and shall agree on the procedures to be used in the arbitration proceedings.

9. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 7 መሰረት የሚሰራ ገላጋይ የገደቡ መጠን ከዋጋ አልባነቱ ወይም ገደቡ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን እንጂ የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ባህሪ መመርመር አይኖርበትም። ገላጋዩ የተጠየቀው የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎች እገዳ በስምምነቱ የተፈቀደ መሆን አለመሆኑን ሊወስን ይችላል። ለግልግል ዳኝነት የተመራው ጉዳይ በንኡስ አንቀጽ 3 የተገለፀት መርሆችና ስነስርአቶች አልተሟሉም የሚለውን ጥያቄ የሚጨምር ሲሆን ገላጋዩ ይህንንም ጉዳይ መመርመር ይኖርበታል። ገላጋዩ የተገለፀት መርሆችና ስነስርአቶች አልተሟሉም ብሎ ከወሰነ አቤት ባዩ ወገን ከንኡስ አንቀጽ 5 ጋር በተጣጣመ መንገድ ሊተገብራቸው ይገባል። የአለመግባባቱ ተሳታፊ ሀገራት የገላጋዩን ዉሳኔ እንደ መጨረሻ ዉሳኔ ሊቀበሉትና የሚመለከታቸው ወገኖችም ሁለተኛ የግልግል ዳኝነት መፈለግ አይኖርባቸዉም። የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ የገላጋዩን ዉሳኔ ወዲያዉኑ እንዲያውቀው መደረግ ይኖርበታል። ሲጠየቅና ጥያቄዉም ከገላጋዩ ዉሳኔ ጋር የተጣጣመ ሲሆንና ጥያቄውን ላለመቀበል በስምምነት ካልወሰነ በስተቀር የተሰጡ ጥቅሞች ወይም ሌሎች የስምምነቱ ግዴታዎችን ለማገድ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል።

አንቀፅ 26
ወጭዎች

1. የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ በአፍሪካ ህብረት የገንዘብ ህጎችና ደንቦች መሰረት የፓነል አባላት፤ ገላጋዮችና ኤክስፐርቶችን ክፍያና ወጭዎችን ይወስናል።

2. የፓነል አባላት፤ ገላጋዮችና ኤክስፐርቶች ክፍያና የጉዞና የመቆያ ወጭወቻቸው በእኩል ወይም የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ በሚወስነው ድርሻ መሰረት በአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ይሸፈናል።

3. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገን ሌሎች ከሂደቱ ጋር የተገናኙ ወጭወችን የአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ በሚወስነው መሰረት ይሸፍናል።

4. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች የፓነሉ አባላትን ወጭ ድርሻቸውን ፓነሉ በሚመሰረትበት ወይም አባላቱ በሚሰየሙበት ጊዜ በፅህፈት ቤቱ እንዲያሲይዙ መደረግ ይኖርበታል።

አንቀፅ 27
ስለግልግል ዳኝነት

1. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች በስምምነት ወደ ግልግል ዳኝነት ሊሄዱና የግልግል ዳኝነቱን ስነስርአት በስምምነት ሊወስኑ ይችላሉ።

2. Parties to a dispute who may have referred a dispute for arbitration pursuant to this Article shall not simultaneously refer the same matter to the DSB.
3. Agreement by the Parties to resort to arbitration shall be notified to the DSB.
4. Third Parties shall be joined to an arbitration proceeding only upon the agreement of the Parties to the arbitration proceedings.
5. The Parties to an arbitration proceeding shall abide by the arbitration award and the award shall be notified to the DSB for enforcement.
6. In the event of a Party to a dispute refusing to cooperate, the Complaining Party shall refer the matter to the DSB for determination.
7. Arbitration awards shall be enforced in accordance with the provisions of Articles 24 and 25 of this Protocol *mutatis mutandis*.

Article 28
Technical Co-operation

1. Upon request from a State Party, the Secretariat may provide additional legal advice and assistance in respect of dispute settlement, provided that this shall be done in a manner that ensures the continued impartiality of the Secretariat.
2. The Secretariat may organise special training courses for interested State Parties concerning dispute settlement procedures and practices to enable State Parties to develop expert capacity on the Dispute Settlement Mechanism.

Article 29
Responsibilities of the Secretariat

1. The Secretariat shall have the responsibility of assisting Panels, especially on legal, historical and procedural aspects of the matter dealt with and of providing secretarial support.
2. The Secretariat shall facilitate the constitution of Panels in accordance with this Protocol.
3. In order to accomplish the functions under Article 28 of this Protocol, the Secretariat shall avail experts with extensive experience in international trade law to assist the Panellists.
4. The Secretariat shall undertake such other functions and duties as may be required under the Agreement and in support of this Protocol.

2. በዚህ አንቀፅ መሰረት አለመግባባታቸውን ወደግልግል ዳኝነት የወሰዱ የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ያንኑ ጉዳይ በተመሳሳይ ጊዜ ወደ አለመግባባቶች መፍቻ አካሉ መውሰድ የለባቸውም።

3. የአለመግባባቱ ተሳታፊ ወገኖች ወደግልግል ዳኝነት ለመሄድ ያደረጉትን ስምምነት ለአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ ማሳወቅ አለባቸው።

4. ሶስተኛ ወገኖች የግልግል ዳኝነቱን ሊቀላቀሉ የሚችሉት የግልግል ዳኝነቱ ተሳታፊ ወገኖች ሲስማሙ ብቻ ነው።

5. የግልግል ዳኝነቱ ተሳታፊ ወገኖች በግልግሉ ዉጤት መገዛት ይኖርባቸዋል። የግልግሉ ዉጤትም እንዲያስፈፅመው ለአለመግባባቶች መፍቻ አካሉ መታወቅ አለበት።

6. አንደኛው ወገን ለመተባበር ፈቃደኛ ካልሆነ ቅሬታ አቅራቢው ወገን ለዉሳኔ ጉዳዩን ወደ አለመግባባቶች መፍቻ አካሉ መውሰድ ይኖርበታል።

7. የግልግል ዳኝነቱ ዉጤት በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 24 እና 25 መሰረት አስፈላጊው ለውጥ ተደርጎበት መፈፀም አለበት።

አንቀፅ 28
ስለ ቴክኒካዊ ትብብር

1. በስምምነቱ አባል ሀገር ጥያቄ መሰረት ፅህፈት ቤቱ ከአለመግባባቶች አፈታት ጋር በተገናኘ ተጨማሪ የህግ ምክርና ርዳታ ሊሰጥ ይችላል። ይሁንና እርዳታው የጽህፈት ቤቱን ቀጣይ ኢወገንተኛነት ባረጋገጠ መንገድ መሆን አለበት።

2. ጽህፈት ቤቱ የስምምነቱ አባል ሀገራት በአለመግባባቶች መፍቻ መንገድ ላይ አቅም እንዲገነቡ ለማድረግ በአለመግባባቶች መፍታት ላይ ልዩ የስልጠና ትምህርቶችን ሊዘጋጅ ይችላል።

አንቀፅ 29
የጽህፈት ቤቱ ሃላፊነቶች

1. ጽህፈት ቤቱ በተለይ በመታየት ላይ ያሉትን ጉዳዮችን ህጋዊ፣ ታሪካዊ እና ስነስርአታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ፓነሎችን የመርዳት እና የጽህፈት ቤት ርዳታ የመስጠት ሀላፊነት አለበት።

2. ጽህፈት ቤቱ በዚህ ፕሮቶኮል መሰረት የፓነሎችን ምስረታ ያመቻቻል።

3. በዚህ ፕሮቶኮል አንቀፅ 28 የተዘረዘሩትን ተግባራት ለማከናወን ጽህፈት ቤቱ የፓነሉን አባላት ለማገዝ በአለም አቀፍ ንግድ ህግ ሰፊ ልምድ ያላቸውን ኤክስፐርቶች መጠቀም ይኖርበታል።

4. ጽህፈት ቤቱ በዚህ ስምምነት የተደነገጉና ይህን ፕሮቶኮል የሚያግዙ ሌሎች ተግባራትን እና ሀላፊነቶችን ማከናወን አለበት።

5. The Secretariat shall be responsible for all relevant notifications to and from the DSB and State Parties.

Article 30
Rules of interpretation

The Panel and the AB shall interpret the provisions of the Agreement in accordance with the customary rules of interpretation of public international law, including the Vienna Convention on the Law of Treaties, 1969.

Article 31
Amendment

This Protocol shall be amended in accordance with Article 29 of the Agreement.

IN WITNESS WHEREOF, WE the Heads of State and Government or duly authorised representatives of the Member States of the African Union have signed and sealed this Agreement in four original texts in Arabic, English, French, and Portuguese languages, all texts being equally authentic.

SIGNED at Kigali, on this 21st day of March in the year 2018.

5. ጽህፈት ቤቱ ከ/ወደ አለመግባባቶች መፍቻ አካሉ እና የስምምነቱ አባል ሀገራት ለሚመጡ እና ለሚሄዱ ማስታወቂያዎች ሀላፊነት አለበት።

አንቀፅ 30
የአተረጓጎም ስርአቶች

ፓነሉና ይግባኝ ሰሚ አካሉ የዚህን ስምምነት ድንጋጌዎች እኤአ የ1969ኙን የቬና የስምምነቶች ህግ ስምምነትን ጨምሮ በአለም አቀፍ ህግ ልማዳዊ የአተረጓጎም ህጎች መሰረት መተርጎም ይኖርባቸዋል።

አንቀፅ 31
ስለማሻሻል

ይህ ፕሮቶኮል በስምምነቱ አንቀፅ 29 መሰረት ይሻሻላል።

ከላይ የተገለፀውን በመመስከር እኛ የሀገርና መንግስት መሪዎች ወይም የአፍሪካ ህብረት አባል ሀገራት ህጋዊ ተወካዮች በአረብኛ፤በእንግሊዝኛ፤ በፈረንሳይኛና በፖርቱጋል ቋንቋዎች ሁሉም እኩል ህጋዊነት ባላቸው በአራት ኦሪጅናል ቅጅዎች የተዘጋጅውን ስምምነት በፊርማና በማህተም አረጋግጥናል።

በኪጋሊ እኤአ በማርች 21 ቀን 2018 ዓ.ም ተፈረመ።

Printed in Addis Ababa, Ethiopia by the ECA Printing and Publishing Unit.
ISO 14001:2015 certified. Printed on chlorine free paper.